# ትግላችን

አለም አቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር

ወርሃዊ መፅሄት

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር የተዘጋጀ

---

" የኢት ዮጵ ያ ሕዝባዊ አብ ዮታዊ ፓር ቲ "
በሰፊው ሕዝብ ትግል ውስጥ ያለው ቦታ::

---

የመፅሄት አዘጋጅ ቦርድ፣
P.O.BOX 3198
103 64 STOCKHOLM 3
SWEDEN

ቁጥር 1 ጥቅምት 1969



ጓድ

# ፍቅሬመርዕድ

---

የአንተ መሞት የአንተ ቀይም መጸዋእት መሆን ለእና ጥንካሬና ትምህርት ይሰጠናል፡፡ ያንተ በአድሃሪዎቹ መገደል የማያቋመጡን ትግል በማፋፋም ቀጥለን ግቡን እንደመታ እናደርገዋለን፡፡ በዚህም የአንተን የተቀደሰ ደም እንበቀሳለን፡፡

ይህ መጽሄት ያንተ የጓደኞችን መታሰቢያ ይሁን፡፡

---

<u>መግቢያ</u>

ይህንን ""ትግላችን"" በምናዘጋጅበት ሰዓት የኢትዮጵያ ህዝቦች ከመደብ ጠላቶቻቸው ጋር ከፍተኛ ትግል በማድረግ ላይ ይገኛሉ፡፡በየካቲት አቢዮታዊ እንቅስቃሴ የገረሰሱትን ፊውዳል ቡርዣ አስተዳደር እስከመጨረሻው ለመቀበር ሃይላቸውን እያስተባበሩና ትግላቸውን መስመር እያስያዙ ናቸው፡፡በዚህ መጠን ደግሞ የሰፊው ህዝብ ትግል ወደፊት እንዳይገፋ አድሃሪያች በየፊናቸው በከፍተኛ ደረጃ ወጥመድ በመደርደር ይገኛሉ፡፡

ሰሞኑን በአገራችን ያለው አካባቢ ሁኔታ ከዚህ ሌላ ምንም ትርጉም ሊሰጠው አይቻልም፡፡

በተለይ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ፣ ማለትም ባለፈት ወራት ውስጥ የተደረገው ከፍተኛ የፊዩት አለም ትግል ሰፊውን ህዝብ ወደ ተከበለናው የነፃነት ጉዳና ካስማራው ወዲህ፣ አድሃሪያች የመቃብር ቀናቸው በይበለጥ እየተቃረበባቸው ሄዷል፡፡

ከየካቲት ወራት በፊት፣ ቢቻል ቀስ በቀስ ካለዚያም በመፈንቅለ መንግስት አቢዮቱን ሊቀለበሱ የሚችሉ የመሰላቸው፣ ዛሬ ህዝቡ ንቃቱን ድርጅቱንና ትጥቁን እያጠነከረ በመጣበት ጊዜ ተስፋ ወደ መቁረጡ ተቃርበዋል፡፡

በአርቆ መንግስት ወይንም በጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስት ህዝቡ እንደማይደለለ ገብቷቸው ሰፊው ሕዝብ በነቃ በተደራጀና በታጠቀ ህዝባዊ አመፅ ህዝባዊት ኢትዮጵያን ለመገንባት እንደተነሳ ሲገለጽላቸው የቀናቸው መቃረብ ይታያቸው ጀምሯል፡፡

ስለዚህም አለቀት ባይ ተጋዳይ ነው እንዳሉ ሰሞኑን ባገሪቷ ውስጥ በከፍተኛ ደረጃ ብጥብጥ ፈጥረው የመጨረሻ እድላቸውን በመሞከር ላይ ይገኛሉ፡፡በተራማጅ ግለሰቦች ላይ ፣ በሠራተኞች ላይ የሚያደርሱት አደጋ ከዚሁ ጥረት ጋር የተያያዘ ነው፡፡አላማቸው ሽብር ፈጥሮ በግርግር ቀለበጣ ለማካሄድ እንደሆነ ሊካድ የማይቻል ግልፅ ሃቅ ሆኗል፡፡

ይሁንና አሁንም እንደ የካቲት የኢትዮጵያ ጭቁን ህዝቦች ለነዚህ አድሃሪ ሃይሎች መፍጨርጨር ተከበለናውን መልስ ሊሰጥዋቸው ቻለዋል ፡፡ አድሃሪ ሃይሎች እንደገመቱት በፈጠሩት ሁካታ ሰፊው የኢትዮጵያ ህዝብ አልተሸበረም፡፡እንዲያውም አድሃሪ ጢቱን ቀና ባደረገ ቁጥር ሰፊው ህዝብ ከበረት የጠነከረ አንድነት በተመሳሳይ ቀለጥፍና ቁጣውን እያሰማ ለፀረ አብዮት ፍጹም በር እንደማይከፍት በማሳየት አብዮታዊነቱን በሚገባ እያሳየ ነው፡፡ሰሞኑን በየከተማውና በየክፍለ ሃገሩ አድሃሪያችንና ቀለባሹን ኢህአፓ በመቃወም የተደረጉት ሰልፎች ለዚህ የማያወላውሉ ምስክሮች ናቸው፡፡በዚህ ትንንቅ ውስጥ አድሃሪው ወገን ከጊዜ ወደ ጊዜ ተስፋ እየቆረጠና ተከታይ እያጣ እንደሚሄድና ሰፊው ህዝብ ሃይሉን ድርጅቱንና ትጥቁን እያጠነከረ እንደሚራመድ ለደቂቃም አንጠራጠርም፡፡ነገር ግን በዚህ መጠን ይህ ከፍተኛ የትግል ወቅት ተጋትና ብርታትን፣ ቀለጥፍናና ጥንቃቄን እንደሚጠይቅ ደግሞ ለሁላችንም ግልፅ ሊሆን ይገባል፡፡



ስለሆነም በዛሬው የትንንቅ ጊዜ ከሰፊው ህዝብ ወገን ቆመን ለትግሉ ፈንታችንን በማበርከትም ሆነ፣ የሰፊው ህዝብ ትግል የያዘውን አቅጣጫ እንዲቀጥልበት በመጣር የሚጠበቅብንን ሚና ማሟላት የኖርብናል፡፡ይህ ማለት ደግሞ ከሰፊው ህዝብ ጎን ቆመን የአድሃሪያችን ሚና ማጋለጥ፣ ተራማጅ መስለው የሚቀርቡትን አወናባጆች መጠቆምና የሰፊው ህዝብ ትግል የመስመር ጥራት እንዲኖረው መጣር አለብን ማለት ነው፡፡

ከዚህም በመነሳት በዚህ የትግላችን እትም ኢህአፓ የተበለውን የአድርባዮች ጉትራ የሚተች ጽሑፍ አቅርበናል፡፡

በዚህ ጽሑፍ የኢህአፓን ምንነት ለማሳየት እንደቻልን ተስፋ እናደርጋለን፡፡ በዚሁም መጠን ይህ ጽሑፍ ኢህአፓን ለማጋለጥ መሳሪያ የሚሆነውን ያህል፣ በኢህአፓ ለተታለሉት የዚህን ድርጅት እውነተኛ መልኩን የሚያሳይ ጽሑፍ እንደሆን እንመኛለን፡፡

የሆነው ሆኖ ዛሬ የኢትዮጵያ ህዝቦች ትግል ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደርሶ ቀጥተኛ ጠላቶቹን ከመጋፈጥ አልፎ ቀለባሹና አወናባጅ ""የትግል""መስመሮችን እየፈለፈለ አውጥቶ ለማውደም የተነሳበት ሰዓት ስለሆነ እንደዚህ አይነት ጽሑፍ ከፍተኛ ሚና አለው ብለን እንገምታለን፡፡

ለማጠቃለል ያህል የኢትዮጵያ ህዝቦች አድርባዮችንና ተከታዮቻቸውን ደምስሰው በነቃ በተደራጀና በታጠቀ ህዝባዊ አመጽ ህዝባዊት ኢትዮጵያ ለመመስረት በሚያደርጉት የነፃነት ትግል ማህበራችን ድርሻውን ሊያበረክት የሚችለው በየጊዜው የመስመር ጥራትን ይዞ የኢትዮጵያ ህዝቦች እንዲደራጁ ቀስቀሳ የሚያደርገውን ያህል ፀረ ህዝብ ድርጅቶችን በማጋለጥ ስለሆነ ፣ ዛሬ በኢህአፓ ላይ የጀመረውን ትችት እንደሚቀጥልበት በዚህ አጋጣሚ ያስታውቃል፡፡

<u>ትግላችን</u>

ከመስከረም 1968 ወዲህ የኢትዮጵያ ፖለቲካ መድረክ በአንድ ተጨማሪ የፖለቲካ ድርጅት የበለጸገና ያጌጠ ይመስላል። ይኸውም የወዛደሩ ፓርቲ ነኝ በማለት ራሱን ባስተዋወቀው 'የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ' በሚባለው ድርጅት። ይህ አርምኝ የፊውዳል ፋሽስቶች ጎተራ የሆነው 'የኢትዮጵያ ዲሞክራቲክ ማኅበር' መደራጀቱን ካበሰረን ወዲህ በተከታታይ ሁለተኛው የመደራጀት ሙከራ መሆኑ ነው። ሁሉም በየፊናው ለመደራጀት ይሯሯጣል፣ በውነትም የመደራጀት ወረርሽኝ።

እንግዲህም ሁለቱ የተለያዩ የመደራጀት ሙከራዎች፣ የተለያዩ የመደብ ዝንባሌዎችን ቢያንፀባርቁም፣ የሚገናኙበት አንድ ነጥብ አለ ሁለቱም ለድርጅቶቻቸው ተራማጅ ስያሜ በመስጠት፣ የሕዝቡ ወገን በመምሰል መሞከራቸው ነው እያ ጎደለ ሰሳሱ ከወደቀ ወዲህ ያገ ሱፍ ጥሉ በተቶ መልበስ ብርቅ ሆኗል። ለምሳሌ የዲሞክራሲ ሽታ እንኳ የማያውቀው ፊውዳል ፋሽስቶች ጥርቅም የሆነው ድርጅት ራሱን 'ዲሞክራቲክ' ብሎ ይጠራል። ለምን?

ምክንያቱም የኢትዮጵያ ሕዝቦች የሚያካሂዱት አብዮት ሕልውና ሕያው / **reality** / በመሆኑ አድርባዮችና አድሀሪያን እንኳ ሳይቀሩ እንዲያውቁት ስለተገደዱ ነው። ባሁኑም ወቅት የሚበቅት 'ለውጥ' እስከመጣ ድረስ፣ ለአድርባዮችና ለአድሀሪያን የሚያዋጣው የሕዝቡን ወገን በመምሰል አብዮትን መታገል ነው። የኢትዮጵያ ሕዝቦች የነዚሁ የተቋቋሙት ወይም በመቋቋም ላይ የሚገኙት የፖለቲካ ድርጅቶች ምንነት፣ የፖለቲካ ዘዴና ዓላማ አበጥረው ማወቅ ይኖርባቸዋል። በዚሁ አቢያ ወሳኝን ከወዳጅ፣ ሰንዴውን ከገለባው ለመለየትና የወዳጅ መስሉ ጠላትን ረቂቅ ሤራ ለማክሸፍ እንዲቻል፣ የነቁ ተራማጆች እነዚሁ ድርጅቶች የተሸፋፈኑበትን ጭንብል ወረቀት በማጋለጥ፣ የመደብ ዝንባሌያቸውንና ምንነት ሰፊው ሕዝብ እንዲገነዘበው ማድረግ፣ ከተጣለባቸው ኃላፊነት አንዱ ነው።

በዚሁ ጽሁፍ ራሱን 'የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ' ብሎ የሚጠራውን ድርጅት ፕሮግራም በመመርመር፣ ይህ የፖለቲካ ድርጅት እንደሚመኘው የወዛደሩ ፓርቲ እንዳልሆነ እናሳያለን። የኢትዮጵያ ወዛደርም ከዚሁ መጥፎ ምሳሌ፣ ተገቢውን ጥሩ ትምህርት እንደሚቀስም፣ ማለትም አንድ የወዛደር ፓርቲ ምን መሆን እንደሌለበት፣ እንደሚረዳ ጽኑ እምነታችን ነው።

<u>የወዛደሩ ፓርቲ ምን ማለት ነው?</u>

በካፒታሊስት ሕብረተሰብ ሥርዓት ውስጥ በምርት መስክ በቀጥታ የሚሠማራው ወዛደር፣ የሚደርስበትን በዝበዛና ጭቆና ለመቋቋም እያሌ የኢኮኖሚ ትግሎች ያካሂዳል። በነዚሁ ትግሎች ውስጥ በሙያ ማኅበራት አባባል እየተደራጀ በሥራ ማቆም አድማ ሆነ በተለያዩ የትግል ዘዴዎች የኢኮኖሚ፣ ኑሮው እንዲሻሻል ቀረ ቁዝ፣



የሥራ ሰዓት እንዲገደብ፣ ወዘተ .. ይሞክራል። የነዚህ የኢኮኖሚ ትግሎች ፍቺ የካፒታሊስትን ሕብረተሰብ ሥርዓት አሽቀንጥሮ ጥሎ፣ በሶሺያሊስት ሕብረተሰብ ሥርዓት ለመተካት ሳይሆን፣ ወዛደሩ በካፒታሊስት ሕብረተሰብ ውስጥ ያለው ቦታ የበለጠ እንዳይወድቅ ለመከላከል፣ ከተቻለም በመጠኑ ቢሆን የኑሮውን ሁኔታ ለማሻሻል ነው።

በዚሁ ደረጃ፣ ማለትም የእለት ጉርሻውን ለማግኘት የሚያካሂደው ትግል በሌኒን "የሙያ ትግል"/ **trade unionism** / ተብሎ ይጠራ ነበር። የሙያ ትግሉ ጥረት የካፒታሊስትን ሕብረተሰብ ለመደምሰስ ሳይሆን፣ በዚሁ ሕብረተሰብ ውስጥ ያለውን ኑሮ ሁኔታ ለማሻሻል ስለሆነ፣ ትግሉ በመሠረቱ ሪፎርሚስት ነው። የንቃት ደረጃውም የሙያ ትግል ንቃት እንጂ የካፒታሊስት ሕብረተሰብ መደምሰስና በሶሺያሊዝም የመተካቱ አስፈላጊነት የሚያውቅ የፖለቲካ ንቃት የለውም። ወዛደሩም በሚያካሂዳቸው የኢኮኖሚ ትግሎች፣ ይህን የፖለቲካ ንቃት ሊያገኝ አይችልም።

ይህ የፖለቲካ ንቃት ማለትም የሶሺያሊስት ቲዎሪ፣ የሚፈልቀው ከወዛደሩ ኢኮኖሚክ ትግል ሳይሆን፣ ለወዛደሩ የቆሙ ተራማጅ ምሁራን፣ የካፒታሊስትን ሕብረተሰብ ሥርዓት ሕጋጋትን በመመርመር ከሚያገኙት ሳይንሳዊ እውቀት ነው። ስለዚሁ ሌኒን ሲጽፍ የሚከተለውን ይላል።

"We have said that there could not have been social-Democratic consciousness among the workers. It would have to be brought to t hem from without. The history of all countries shows that the working class, exclusively by its own effort, is able to develop only trade-union consciousness, i.e. the conviction that it is necessary to combine in union, fight the employers, and strive to compel the government to pass necessary labouor legislation, etc. The theory of socialism, however, grew out of the philosophic, historical and economic theories elaborated by educated representatives of the propertied classes, by intellectuals. By their social status, the founders of modern scientific socialism, Marx and Engels, themselves belonged to the bourgeois intelligentia."(Coll. Works Vol. 5, p.375)

እንደዚሁም <u>ካውትስኪ</u> ማርክሲስት በነበረበት ጊዜ፣

"...socialism, as a doctrine, has its roots in modern economic relationships just as the class of the proletariat has, and, like the latter, emerges from the struggle against the capitalist-created poverty and misery of masses. But socialism and the class struggle arise side by side and not one out of the other; each arises under different conditions. Modern socialist consciousness can arise only on the basis of profound scintific knowledge.... The vehicle of science is not the proletariat, but

the bourgeois intelligentia: it was in the minds of individual members of this stratum that modern socialism originated, and it was they who communicated it to the more intellectually developed proletarians who, in their turn, introduce it into the proletarian class struggle where conditions allow that to be done. Thus socialist consciousness is something introduced into the proletarian class struggle from without and not something that arose within it spontaneously." (Lenin, Coll. Works, Vol. 5, p. 383-384)

በላይ ከቀረቡት ጥቅሶች ለማየት እንደሚቻለው ወዝ አደሩ ይህን አብዮታዊ የፖለቲካ ንቃት የሚያገኘው ለርሱ ተገለ በቆሙት አብዮታዊያን ምሁራን አማካኝነት ነው:: እነዚሁ አብዮታዊ ምሁራን በወዝ አደሩ ትግል ውስጥ በመግባት፣ ከርሱም ጋር በመዋሃድ ሳይንሳዊ ሶሺያሊዝም ያመጡለታል:: በዚሁም ባቢያ የአብዮታዊ ሳይንሳዊ ሶሺያሊስት ቲዎሪና የወዝ አደሩ እንቅስቃሴ ተዋሕደው የወዝ አደሩን ፓርቲ ይወልዳሉ:: <u>እንዲያውም በማርክሲስት ሌኒኒስት ቋንቋ የወዝ አደሩ ፓርቲ ማለት የሳይንሳዊ ሶሺያሊዝምና የወዝ አደሩ እንቅስቃሴ ሕብረት ማለት ነው::</u> የጀርመን ማርክሲስቶች አባባል በመከተል ሌኒን

"Social Democracy represents <u>the combination</u> of socialism and the working class movement." (Vol. 4, p.217)

የዚህን ሕብረት፣ የወዝ አደሩን ፓርቲ፣ አፈጣጠር ጕርሰን እንመልከት:: በወዝ አደሩ እንቅስቃሴ ጋር በመዋሃድ ምሁራን በየቦታው የወዝ አደሮች የጥናትና የፕሮፓጋንዳ ክበቦች ያቋቁማሉ:: እነዚሁ የጥናት ክበቦች ወዝ አደሩ አብዮታዊ ቲዎሪ የሚገበዩበትና እንደዚሁም ትግሎችን በሚያካሂዱበት ወቅት፣ በራሪ ወረቀቶች፣ ወዘተ.. በመጻፍና በማውጣት ይረዷታል:: አብዛኛውን ጊዜ እነዚሁ ጥናት ክበቦች በኅቡዕነት የተመሠረቱ፣ በመሀናቸው ግንኙነት የሌላቸው፣ በተበጣጠረ አኳያን ትግሉን የሚያካሂዱና እንዲሁም የተለያዩ የንቃት ደረጃ ያላቸው ናቸው:: ምንምእንኳ በመጀመሪያው የትግል ደረጃ ለወዝ አደሩ የፖለቲካ ንቃት በመስጠት ጠቃሚ ሚና ቢጫወቱም፣ የወዝ አደሩ እንቅስቃሴ እያደገ ወደፊት ሲራመድ፣ የነዚሁ ክበቦች መበታተን፣ መበጣጠር ወዘተ.. ለትግሉ እንቅፋት መሆን ይጀምራል:: ትግሉ እየዳበረ፣ እየሰፋ ሲሄድ፣ እነዚሁን ጥናት ክበቦች አስወግደ፣ በፈንታቸው ወዝ አደሩ በየቦታው የሚካሄዱትን ትግሎች የሚጠቀልልና የሚያቀነባብር የትግል ድርጅት አስፈላጊነት ግልጽ እየሆነ ይሄዳል:: <u>ይህም የሚያስፈልገው ድርጅት የወዝ አደሩ ፓርቲ ነው::</u> ሌኒን በራሺያ ውስጥ የወዝ አደሩ ፓርቲ አስፈላጊነት ሲያስረዳ



"የሶሺያል ዲሞክራቲክ እንቅስቃሴ ዘሮች በራሺያ ውስጥ በጠቅላላው ተሠራጭተዋል:: የወዝ አደር በራሪ ወረቀቶች የመጀመሪያዎቹ የሶሺያል ዲሞክራቲክ ጽሁፍ ዓይነቶች ከሴንት ፒተርስበርግ እንስቶ እስከ ክራስኖያርስክ፣ ከካውካሰስ እንስቶ እስከ ዑራል ሳሉት ወዝ አደሮች እውቅ ናቸው:: ባሁኑ ጊዜ የሚጎድለው፣ <u>ይህን ሁሉ የአካባቢ ሥራ</u> /all this local work / <u>በአንድ ፓርቲ ሥራ ውስጥ ማጠቃለሉ ነበር</u> / ከአጣዳፊ ተግባራችን vol.4 p 217 /

<u>ይህን ሁሉ ያካባቢ ሥራ የሚያጠቃልለው ፓርቲ የሚፈጠረው፣</u> ይህን ያካባቢ ሥራ ያካሄዱ የነበሩት የወዝ አደሩ ጥናትና ፕሮፓጋንዳ ክበቦች <u>ሲዋሃዱና</u> አንድ ድርጅት ሲፈጥሩ ነው:: <u>እነዚሁ ክበቦች</u> ፓርቲውን የሚገነቡ ጡቦች ይሆናሉ ማለት ነው:: ይህም በክበቦች መሀል የሚኖረው ሕብረት በአዋጅ የሚመሠረት፣ ወይም በቀጥታ የሚፈጠር ሳይሆን፣ መታገል አለበት:: የአቋንት ደረጃቸውና በፖለቲካ ንቃታቸው የተለያዩትን የወዝ አደር ጥናትና ፕሮፓጋንዳ ክበቦች መሰብሰብና፣ አንድ የፖለቲካ መስመር መዋሃድ ቀላል ተግባር አይደለም:: የዚሁ ዓይነት ድርጅታዊ ሕብረት፣ መሠረቱ የፖለቲካና የርዕዮተ ዓለም አስተሳሰብ አንድነት እንደመሆኑ መጠን፣ አለበለዚያማ መዋሃድ አይቻልም፣ የወዝ አደሩን ትግልና አብዮት በሚመለከቱ አንኳር የሆኑ አለማዊ ጥያቄዎች ላይ ስምምነት ያስፈልጋል:: ይህም ስምምነት ሊገኝ የሚችለው በነዚሁ ጥያቄዎች ላይ በሚደረግ ውይይት ከፍተኛ ክብሳለቶና ጥራት ተገኝቶባቸው፣ አብዮታዊ መሥመር ሲረጋገጥባቸው ነው:: በነዚሁ የወዝ አደር ጥናት ክበቦች መሀል የርዕዮተ ዓለም ስምምነት ካልተደረሰ፣ ጠቅላላውን የወዝ አደር እንቅስቃሴ የሚያቅፍ፣ የሚጠቀልልና የሚመራ የወዝ አደር ፓርቲ ሊፈጠር አይችልም:: ይህም ውይይት ሊካሄድ የሚችለው የተለያዩትን የጥናት ክበቦችን አንድ <u>ፖስታ</u> በሚያገናኟቸው የጋራ ጽሁፎች ጋዜጦች፣ መጽሔቶች፣ ወዘተ... አማካኝነት ነው:: ምንም እንኳ የኢትዮጵያ ወዝ አደር ፓርቲ የሚደራጅበት አኳኋን የኢትዮጵያን ልዩ ተጨባጭ ሁኔታ ቢያንፀባርቅም፣ የዓለም ወዝ አደር ፓርቲዎች በተጓዙበት በዚሁ የመደራጀት ጎዳና መራመዱ የማይቀር ነው::

ወደ የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ /ኢ.ሕ.አ.ፓ./ እንምጣ:: እንዴት ነው የተደራጀው? ስለራሱ መደራጀት በፕሮግራሙ መቅድም የተጻፈው እንደሚከተለው ይላል::

"በሳብ አደሩ መሪነት ሰፊውን ሕዝብ በማደራጀት ሕዝቡ እላይ ከተጠቀሰው የሚያንገፈግፍ ብዝበዛና ጭቆና ራሱን ነጻ የሚያወጣበት ጠቅላላ አድማም <u>የሚያፈጥንበት ዘዴ ለመቀየስና በሥራቸውም ለመታገል የዛሬ ሰባት ዓመት ተኩል ተቋቋመ</u>::

ይህ ፓርቲ የተደራጀው የዛሬ ሰባት ዓመት ተኩል ነው:: ትብለናል:: መልካም ነው:: ነገር ግን የኢትዮጵያ ወዝ አደር እንኳ ቀርቶ የኢትዮጵያ ሕዝቦች ይህን ፓርቲ መኖሩን የሚያውቁት ያው የዛሬ አራት ወር በአዲስ አበባና

እንዲሁም በሌሎች ከተሞች ፕሮግራሙን በማሠራጨት ራሱን ባስተዋወቀበት ወቅት ነበር:: ማለትም ባለፉት ሦስት ዓመታት ተኩል /ይህን በምንጽፍበት ወቅት 4 መሆኑ ነው::/ ይህ ፓርቲ ከመንግስቱ የጭቆና መሣሪያዎች ብቻ ሳይሆን፣ ከወዝ አደሩና ከሰፊውም ሕዝብም ጭምር ተደብቆ 'ይታገል' ነበር::

ከፍ ብለን የወዝ አደሩ ፓርቲ የሚከብበት ቲዎሪና የወዝ አደሩ እንቅስቃሴ አንድነት፣ ተዋህደ መሆኑን ገልጸን ነበር:: በዚሁ አንጻር መቼም ከወዝ አደሩ የተደበቀ፣ ወዝ አደሩ መኖሩንም እንኳ የማያውቀው፣ በወዝ አደሩ ትግሎች ተሳትፎ ኮሚኒስት ፕሮፓጋንዳና ቅስቀሳ ያላደረገ፣ ባጭሩ ከወዝ አደሩ እንቅስቃሴ የተገነጠለ ኮሚኒስት ፓርቲ ሊኖር አይችልም::

እንዲሁም የኮሚኒስት ፓርቲ አስፈላጊነት በገለጽንበት ወቅት፣ የተለያዩትን የወዝ አደር ጥናት ክበቦች በማዋሃድ መሆኑን ተናግረናል:: የኢ.ሕ.አ.ፓ. የወሰዱነው እንደሆነ ግን፣ ወደ ዛሬ 4 ዓመት ወደኋላ መመለሱን ትተን የአሁኑን የፖለቲካ ሕልውና በገመለከት፣ በሀገሪቱ ውስጥ ከሚገኙት የማርክሲስት ጥናት ክበቦችን አብዛኛዎችን እንኳ ሊጠቀለል አልቻለም:: እንዴትስ አድርጎ ይችላል? ከወዝ አደሩ የተደበቀ ቡድን፣ ከወዝ አደሩ ጋር በመቀላቀል ላይ ከሚገኙትም የማርክሲስት ጥናት ክበቦችም መደበቅ አይቀርም:: በተረፈም በነዚሁ በየቦታው ተሰበጣጥረው በሚገኙት የጥናትና የፕሮፓጋንዳ ክበቦች መሀል ሰፊ ርዕዮተ ዓለም ውይይት ተከፍቶ፣ የሀሳብ አንድነት ካልተደረሰ፣ እንዴትስ አድርጎ ነው እነዚሁን ባንድ ፓርቲ ለማደራጀት የሚቻለው?

በውነቱ የዚሁ ፓርቲ አፈጣጠር ታሪክ የአንዳንድ ንዑስ ከበርቴዎች በወዝ አደሩ ስም የመመጻደቅ ታሪክ ነው:: /በስታሪክ ማንሣታችን ካልቀረ፣ ጋይፈት የኢ.ሕ.አ.ፓ ታሪክ በሚጻፍበት ወቅት፣ ቢያንስ በለመጀመሪያዎቹ ሁለት 'የትግል' ዓመታት የሚጻፍ ነገር በለሌለ፣ ባዶ ቦታ ተተ ከመሀል መጀመር ሊያስፈልግ ነው/ ይህም ንዑስ ከበርቴነት ስለ የኢ.ሕ.አ.ፓ አደረጃጀት በዲፉትና ላይ በጠቀስነው ጎልቶ ይታያል:: በዑንጋሚ ለመጥቀስ

"በሳብ አደሩ መሪነት በፊውን ሕዝብ በማደራጀት ሕዝቡ እሳይ ከተጠቀሰው የሚያንገፈግፍ በዝበዛና ጭቆና ራሱን ነጻ የሚያወጣበት ጠቀሳሳ አድገተንም የሚያቶጥንበት ዘዴ ለመቀየስና በመሠረቱም ለመታገል የዛሬ በስት ዓመት ተቋቋመ"

እንግዲህ ይህ ፓርቲ፣ ማለትም ራሱን ኢ.ሕ.አ.ፓ ብሉ የሚጠራው፣ የተቋቋመው በፊውን ሕዝብ በሳብ አደሩ መሪነት በማደራጀት፣ ሕዝቡ ራሱ ነጻ የሚወጣበትን አቅጣጫ ለመቀየስና ለዚሁም ለመታገል ነው:: እንደ ንዑስ ከበርቴዎች 'ሕዝብ' 'ሕዝብ' በሚለው ቃል ካልደነዘዘን፣ ጥያቄውን ከማርክሲስት ሌኒኒስት አንጻር ከተመለከትነው፣ ላይ የቀረቡት ነጥቦች የማርክሲስት ፓርቲ መደራጀት ምክንያትና ዓላማ ሊሆኑ አይችሉም::እናብራራ::



በመጀመሪያ ነገር የማርክሲስቶች ዓላማ ሕዝቡን በወዝ አደሩ መሪነት በማደራጀት ሕዝቡ ራሱ ነጻ የሚወጣበትን መንገድ መቀየስና ለዚሁም መታገል ሊሆን የማይችለው፣ በአንድ የመደብ ሕብረተሰብ ውስጥ የሚኖር ሕዝብ በመደቦች፣ በገበሬው ንዑስ ከበርቴው፣ ወዝ አደር ወዘተ.. የተከፋፈለ በለሆነ ነው::

አንድ ኮሚኒስት ፓርቲ የሚደራጀው ሕዝቡ ግለት ከበርቴውን፣ ወዝ አደሩም ወዘተ:...ነጻ የሚወጣበት መንገድ ለመቀየስና ለዚሁም ለመታገል ሳይሆን፣ የሚቀመጡና የሚታገለው ለወዝ አደሩ መደብ ነው:: እሳማውም የወዝ አደሩን መደብ ታሪካዊ ትግል በማደራጀትና በመምራት እርሱን ከመደብ ጭቆና ብዝበዛ ነጻ ለማውጣት ነው:: ይሄ የኢ.ሕ.አ.ፓ ገና ያልጨበጠው የማርክሲዝም ሀ ሁ ነው:: የኢ.ሕ.አ.ፓ 'ሕዝቡና' ነጻ ለማውጣት ቢነሣሣም፣ ከወዝ አደሩ የፈለገው ለመጻደቅ የሚችልበት ሥምና አርማ ብቻ ነው::

ይህ በወዝ አደሩ ትግል መሰለቅ፣ መቀለዱ፣ ሚፌዝ ሲሆን፣ በጠቅላላው የወዝ አደሩ ትግልና እንቅስቃሴ የሚፈጸመው ፎንጀል ቀላል አይደለም:: ዉርብ ፎንጀል ነው::

ሀ/ 'ሕዝቡን ነጻ' ለማውጣት በሚለው መለስተኛ ሕዝባዊ /ፓፑሊስት/ አስተሳሰብ ተነስቶ፣ ለዚሁም ግብ በወዝ አደሩ እንቅስቃሴ መመዳደቁ በወዝ አደሩ ሠልፍ መሃል ከፍተኛ ውዥንብር መፍጠር ነው:: የወዝ አደሩም ትግል አቅጣጫ ለማሳሳት መሞከር ነው::

ለ/ የኢትዮጵያ ውስጥ የእውነተኛ ኮሚኒስት ፓርቲ መፈጠርም የሚያደናቅፍ፣ በዚሁ አቅጣጫ የሚደረገውን ትግል ለማስናከል የሚበጅ ነው:: በተለይ ባሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ገራ መሃል ስለወዝ አደሩ ፓርቲ ምንነት ከመቼውም የበለጠ ርዕዮተ ዓለማዊ ጥራት በሚያስፈልግበት ጊዜ የዚሁን ዓይነቱ ፓፑሊስት፣ ጥሬዝ ነጠቅ ግምት ማሠራጨቱ ይህን የጥሬት ፕሮሰስ ለማጨናገፍ እንደመሞከር ነው::

## የወዝ አደር ፓርቲ ፕሮግራም ምንድን ነው? ይዘቱስ?

የኢ.ሕ.አፓ ፀረ ወዝአደርነትን በሚገባ ጥልቀት ለመረዳት፣ የአንድ ወዝ አደር ፓርቲ ፕሮግራም ምንነት በመተንተን፣ ከዚያ በኋላ ከኢ.ሕ.አ.ፓ ፕሮግራም ጋር ማነጻፀሩ ተገቢውና ተከበለኛው መንገድ ይመሠለናል:: የዚሁ አካሄድ ጥቅም የወዝ አደር ፓርቲ ፕሮግራም ይዘት የሚያበረዳ ብቻ ሳይሆን፣ ተያይዞም የኢ.ሕ.አ.ፓ. ፕሮግራም ለመመርመር የምንችልበት መነሻ በለሚሆንም ነው:: እንዲሁም ከሙን አቅጣጫ ተነሥተን ሂስ እንደምና ቀርበም ያሳያል::

አንድ የወዝ አደሩ ፓርቲ ፕሮግራም፣ የወዝ አደሩ ትግል ምንነትና መሠረታዊ ምክንያቶቹ፣ ትግሉ የሚመራባቸውን መሠረተ ነገሮች /principles/ የዚሁ ትግል ደረጃዎችና የመጨረሻ ዓላማ የሚዘረዝርና የሚያበረዳ መሆን አለበት:: በአጠቃላይ ሌኒን በለዚሁ ሲናገር የሚከተለውን ይላል::

"We have stated that the essence of this programme is to organize the class struggle of the proletariat and lead this struggle, the ultimate aim of which is the conquest of political power by the proletariat and the establishment of a socialist society" (Coll. Works, Vol. 4, p.212).

ይህ ሃሳብ በአጠቃላይ የተገለፀ ክፍሉ፣ ፕሮግራሙ የሀገሪቷን ኢኮኖሚክ ሥርዓት መሠረታዊ ነጥቦች መዘርዘር አለበት፤ ይህ የፕሮግራሙ ዋና ነጥብ ነው:: ከዚህም ጋር በማያያዝ ፕሮግራሙ የካፒታሊስት ሕብረተ ሰብ ሥርዓት ታሪካዊ እድገትና አዝማሚያዎች በመግለፅ፣ ይህ ሕብረተ ሰብ በቅራኔዎች መከረር የተነሣ ወዳቂ መሆኑንና በሶሺያሊዝም የሚተካ ታሪካዊ አስፈላጊነት መገለጽ ይኖርበታል:: ለጥቆም የዛሬይቱ በካፒታሊስት ሕብረተ ሰብ ሥርዓት ያለውን የተበዝባዡና የበዝባዡን ቦታ በመግለጽ፣ ከዚህ ምዝበራና ጭቆና ነጻ ሊወጣ የሚችለው በወዝ አደሩ አብዮት አማካኝነት መሆኑን አስረድቶ፣ የዚሁን አብዮት መሪረኛ ግብ መ ተለም አለበት:: በተረፈም ወዝ አደሩ ይህን ታሪካዊ ግብ ለመታ የሚችልበትንም የወዝ አደሩን አብዮት አፈፉ ነጥቦች መዘርዘር ያስፈልጋል:: ባጭሩ በፕሮግራሙ አጠቃላይ ክፍል የካፒታሊስት ሕብረተ ሰብ <u>እድገት አዝማሚያና ጉድፋቶች፣ የወዝ አደሩ ትግል ዓላማና፣ ይህን ዓላማ ለመድረስ የሚያስችለው መንገድ ይገለጻል</u>::

በአጠቃላይ ክፍሉ በመንተራስ የፕሮግራሙ ሁለተኛ ክፍል ደግሞ፣ የወዝ አደሩ ትግል ያለበትና ወደ ዋናው ግብ ለመድረስ ማለፍ የሚኖርበትን የትግል ደረጃ በመጥቀስ፣ ለዚሁም ዝግጁ፣ የዚሁ የቅርብ ትግል ደረጃ፣

ሀ/ ዓላማ፣

ለ/ የሚበጀውን የትግል ኀይሎች፣

ሐ/ በዚሁ የትግል መድረክ መቀረብ ያለባቸውን ጠቢቅ የፖለቲካ ጥያቄዎችን ያዘላል:: ይህ ፕሮግራሙ ዝቅተኛው ደረጃ **/minimum program** / ነው:: ባገራችን በኢትዮጵያ ባሁኑ ሰዓት የወዝ አደሩ ዝቅተኛ ፕሮግራም ኢምፔሪያሊዝምንና ፊውዳሊዝምን ደምስሶ አዲሱን ዲሞክራሲ አብዮት ድል ገሎ ማድረስ ነው:: የአንድ ወዝ አደር ፓርቲ ከፍተኛና ዝቅተኛ ፕሮግራም በቅርብ የተያያዙ፣ ዝቅተኛው በከፍተኛው የተመሠረተና እርሱንም የሚያገለግል ሲሆን፣ ሁለቱም የማይነጣጠሉ አንድነት ናቸው:: ሆኖም በሁለቱ መሀል ያለውን አንድነት ብቻ አይቶ፣ ለልዩነታቸው ቦታ መሆን፣ ለተለያዩ የትግል ደረጃዎች የሚበጁ መሆናቸውን መዘንጋትና እነርሱንም ማምታታት አይገባም::



ከፍ ብለን የነጸፍናቸው የማርክሲስት ፓርቲ ፕሮግራም መሠረተ ነገሮችና የአከፋፈል ዘዴ፣ እርእዮተ ዓለማቸው ከዓለም ዓቀፍ ወዝ አደር ፓርቲ ፕሮግራሞች የመነጩ ናቸው:: ከነዚህ ጥሩዎቹ፣ ኮሚኒስት ማኒፌስቶ፣ ኤርፈርተር ፕሮግራም፣ የሩሲያ ሶሺያል ዲሞክራቶች ፕሮግራም /1903/፣ ከሌኒን የፕሮግራም ማሻሻያ ነጥቦች /1917/ እና ከሩሲያ ኮሚኒስት ፓርቲ ፕሮግራም /1919/

ከላይ በዘረዘርነው አንጻር የኢ.ሕ.አ.ፓ ፕሮግራም ስንመለከት ይዘቱ ስንዴት ነው? በእርግጥ የአንድ ማርክሲስት ፕሮግራም መደበኛ ነጥቦች ያዘላል ወይ? እቅጩን ለመናገር፣ በውነቱ በመደመሪያው ገጽ ላይ ከተሰጠሩት የመደበኛ ማጥያ አርማ በስተቀር፣ ይህን ፕሮግራም ከእውነተኛ የወዝ አደር ፓርቲ ፕሮግራም ጋር የሚያገናኘው አንዳችም ነገር የለም:: እናስረዳ፡-

የሶሺያሊዝም መሠረት የካፒታሊስት ሕብረተ ሰብ ቅራኔዎችና ወዝ አደሩ የሚያካሂዳቸው ፀረ ካፒታሊስት ትግሎች እንደሆኑ የማርክሲዝም፣ ሌኒኒዝም አሮጊዳ ነው:: በታሪክ ደረጃ የወዝ አደሩ ዋና ጠላትና አንገፋ የካፒታሊስት መደብ እንደመሆኑ መጠን፣ የወዝ አደሩ ፓርቲ ወዝ አደሩን በዚሁ ታሪካዊ ትግል በማደራጀት ድል ይመራዋል:: የማርክሲስት ፓርቲ ዋናም ዓላማ ወዝ አደሩን ከካፒታሊስት ምዝበራና ጭቆና ነጻ በማውጣት፣ ጠቅላላውን ሕብረተ ሰቡንም እንደዚሁ ከመደብ ጭቆና በዝብዝ ነጻ ለማውጣት፣ መደብ የሌለው ሕብረተ ሰብ ለመገንባት ነው:: ሆኖም የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲን ፕሮግራም በምናገላብጥበት ወቅት በኢትዮጵያ ወዝ አደሩ ላይ የሚረገጠው <u>አስከፊ ካፒታሊስት ብዝበዛና</u> ጭቆና፣ እንዲሁም የወዝ አደሩ ፀረ ካፒታሊስት ትግል <u>መገለጹ ቀርቶ፣ በገዴት ቃልም እንኳ አይጠቀስም</u>:: ምናልባት በሠራተኞች ሥቃዮች መለኪያዊ ተአምር ካልሆነ በስተቀር፣ በቋንቋዊ በሶሺያሊዝም አንጻር የወዝ አደሩን ፀረ ካፒታሊስት ትግል <u>የማያደራጅና</u> የማይመራ፣ ይህንን ፕሮግራሙ ይዞ በተቀዳሚ ደረጃ ያሰለፈ ማርክሲስት ሌኒኒስት ፓርቲ ፍጹም ሊኖር አይችልም:: አይደለምም:: የአንድ ኮሚኒስት ፓርቲ ወናር ምክንያት ይህ ነውና! በሌኒን ገምቱ፣

"The cardinal point of the programme should be the characterization of the basic features of the present-day economic system of Russia and its development.(cf. in the programme of the Emancipation of Labour group: "Capitalism has advanced tremendous success in Russia...."). This should be followed by an outline of the fundamental tendency of capitalism - the splitting of the people into a bourgeoisie and proletariat,the growth of "the mass of misery, oppression, slavery, degradation." (Coll. Works, Vol. 4, p. 233).

ሌኒን እንደሚለው የፖርቲው ፕሮግራም እንዝርቱ፣ ማዕከላዊ ነጥቡ፣ የካፒታሊዝም መለዮዎችንና የዕድገት አዝማሚያዎችን ማብጠልጠሉ ጭቆናውን መግለጽ ነው::

የኢ.ሕ.አ.ፓ ፕሮግራም ግን የወዝ አደሩ ጠላቶች ሦስት፣ ፊውዳሊዝምና ኢምፔሪያሊዝምና ካፒታሊዝም፣ መሆናቸውን ይዘነጋል:: እንደ ወዝ አደሩ ጠላቶች አድርጎ የሚያስቀምጠው ኢምፔሪያሊዝምና ፊውዳሊዝምን ብቻ ነው:: በኛ ግምት ደግሞ ፀረ ካፒታሊስት ያልሆነ በወዝ አደሩና በካፒታሊስቱ መሀል ያለውን ቅራኔና የመደብ ትግል ያልገለጸ ፕሮግራም፣ ከቶም ፈጽሞ የወዝ አደሩ ፓርቲ ፕሮግራም ሊሆን አይችልም:: የኛም ግምት ብቻ ሳይሆን፣ የማርክሲዝም፣ የሌኒኒዝም መሠረተ ሃሳብ ነው:: ከፍ ብለን እንደገለጸነው በፀረ ጉልተኛው ስርዓትና በፀረ ኢምፔሪያሊዝም ብቻ የተመሠረተ ፓርቲ፣ እንዲሁም በወዝ አደሩ ላይ የሚደርሰውን የካፒታሊስት ጭቆናና ብዝበዛ እታገላለሁኝ የማይል፣ እንዲያውም የዚህ ጭቆና መኖር እንኳ በፕሮግራሙ የማይገለጽ ፓርቲ ምንም ቢሆን ለሶሺያሊዝምና ለወዝ አደሩ አብዮት እቆማለሁኝ ሊል አይችልም::

ላይ እንዳበረዳነው ለወዝ አደሩ የኢትዮጵያ አብዮት ሁለት ደረጃዎች አሉት:: በመጀመሪያው ደረጃ <u>በጠቃላይ</u> የኢትዮጵያ ሕዝብ ጠላቶች የሆኑት ኢምፔሪያሊዝምና ፊውዳሊዝም ይደመሰሳሉ፣ በሁለተኛው የትግል ደረጃ <u>በተለይ</u> የወዝ አደር ጠላት የሆነው ካፒታሊስት መደብ በሶሺያሊስቱ አብዮት ይገለበጣል:: የኢ.ሕ.አ.ፓ ፕሮግራም ከላይ እስከታች የሚያወራው ስለ መጀመሪያው የትግል ደረጃ ብቻ ነው:: ስለ ፀረ ኢምፔሪያሊስቱ ስለ ፀረ ጉልተኛው ትግል ብቻ አውርቶ ስለ ፀረ ካፒታሊስቱ ትግል አንዲትም ቃል ሳይናገሩ ዓላማችን ሶሺያሊዝም ለመመስረት ነው ማለቱ በጣም ሜዳ እንደመፈራገጥ ያህል ነው::

የኢ.ሕ.አ.ፓ ፕሮግራም ስለ ፀረ ካፒታሊስቱ ትግል ስለማያነሣ በምንም አኳኋን ስለ ሶሺያሊስቱ አብዮት ሊናገር እንደማይችል ገልጸናል:: እንዲያውም በፕሮግራሙ ውስጥ የወዝ አደሩ አብዮት ለወጉ፣ ያውም በተወናበደ አኳኋን፣ ባንዲት ሀገር ብቻ ነው የሚጠቀሰው::ሐረጉን እንመልከት::

"የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ የላብ አደር መደብ ፓርቲ ነው:: ዓላማው የላብ አደሩንና የአርሶ አደሩን አንድነት በማጠናከር፣ <u>የላብ አደሩ መደብ ዲክታተርሽፕ</u> /ፍጹም ሥልጣን ለመመስረትና በሱም አማካኝነት አንድ ሰው በምንም ዓይነት ሌላውን ሰው የማይበዘብዝበት ሕብረተ ሰብ ያፈራው ሀብት ለመላው ሕብረተ ሰብ ጥቅም የሚውልበት ማንኛውም ዓይነት ጭቆና የማይታወቅበት ለሕብረተ ሰቡና ገብ ነጻና ጠቅላላ እድገት ዋስትና የሚገኝበት መደብ አልባ ሕብረተ ሰብን ለመገንባት ነው" / ገጽ 3 /

እቺ እንደ መና ከሰማይ ፕሮግራሙ ውስጥ ዱብ ያለች "የላብ አደሩ መደብ ዲክታተርሽፕ፣" ምንጯ ምንነቷና አስፈላጊነቷ ካልተዘረዘረ በፕሮግራሙ ውስጥ የርቧ መስፈር ለወጉ ካልሆነ ምን ፋይዳ ሊኖራት ይችላል? ይህን ፕሮግራም ያነበበ ወዝ አደር "የላብ አደሩ መደብ ዲክታተር ሺፕ ለምን?"



ብሎ ቢጠይቅ ፕሮግራሙ የሚሰጠው መልስ እጆቹን ኪሱ ውስጥ ከቶ፣ ትከሻውን በመነቅነቅ "አላውቅልህም" ነው:: ስለዚህ ወዝ አደሩ ፀረ ካፒታሊስት ትግል ምንም ሳይገለጽ፣ በፕሮግራሙ ውስጥ የወዝ አደሩን ዲክታተር ጥያቄ ባንዲት ሐረግ ሲሸኘን፣ ከዚህ የበለጠ መልስ መቼም ለመጠበቅም አይቻልም:: ይህ ብቻ ሳይሆን በጥቅሱ ስለዓላማ የተጻፈው / አንባቢያች ጥቅሱን እንደገና እንዲያነቡት እንጋብዛለን/ ፍጹም የተወናበደ ነው:: ከጥቅሱ ለማየት እንደሚቻለው የኢ.ሕ.አ.ፓ ባንድ ደረጃ የሚቆሙ በመሠረቱ ሁለት ዓላማዎች አሉት፣ እነርሱም

ሀ/ የላብ አደሩንና የአርሶ አደሩን አንድነት ለማጠናከር

ለ/ የላብ አደሩን ዲክታተርሽፕ መሥርቶ፣ በርሱ አማካኝነት ኮሚኒዝምን ለመመሥረት ነው::

በውነቱ እነዚህ እንደ ዓላማ የቀረቡት ሁለት ነጥቦች ፍጹም ተቃራኒ ናቸው:: የወዝአደሩ ፓርቲ ዓላማ የላብ አደሩንና የአርሶ አደሩን አንድነት ለማጠናከርና የላብ አደሩን ዲክታተርመሥርቶ በርሱ አማካኝነት ኮሚኒዝምን ለመገንባት ሊሆን አይችልም:: ትንሽ ሳብበት፣ ሁለቱ በጥምራ እንደ ዓላማ ሊቀርቡ እንደማይችሉ፣ በዚህም ደረጃ እንደማይጣጣሙ በቀላሉ ይረዳል:: ለምን? የወዝ አደሩ ዲክታተርሽፕ የወዝ አደሩ ፓርቲ ዓላማ ቢሆን፣ የወዝ አደሩንና የአርሶ አደሩን አንድነት ማጠናከር /በመጀመሪያ መፍጠር አለበት / ግን ዓላማው አይደለም ::አንድ ኮሚኒስት ፓርቲ በወዝ አደሩና፣ በአፈር ገፊው መሀል አንድነት እንዲፈጠር የሚታገለው፣ ይህ አንድነት ዓላማው በመሆኑ ሳይሆን፣ ይልቁን ፊውዳሊዝምና ኢምፔሪያሊዝም መደምሰስ የሚለውን ዓላማ ለመድረስ የሚበጀው የትግል መሣሪያ በመሆኑ ነው:: ሰዎች የሚተባበሩት፣ አንዱ ብቻውን ሊፈጽመው የማይችለውን ባንድነት ስለሚያገኙት ነው እንጂ በደፈናው "ለተባበር" ሲባል አይደለም:: ማለትም ሰዎች የሚተባበሩት ለአንድ የተወሰነ ዓላማ ነው እንጂ፣ ትብብሩ ራሱ ዓላማ ስለሆነባቸው አይደለም:: በመደብ ትግልም እንዲሁ አንዱ መደብ ከሌላ ጋር የሚደበለው ባንድነት ጠላቶቻቸውን ለማጥፋት ነው እንጂ ምናልባት በነርሱ መሀል "መጠናከር" ያለበት ፍቅር ኖሮ አይደለም:: በዚህ፡ጽሁፍ የኢ.ሕ.አ.ፓ ፕሮግራም የተዘፈዘፈበትን ውጥንብር ለማየት የሚያስቸግር አይደለም::

እንደዚሁም የወዝ አደሩን ትግል ታሪካዊ ምንነት ያልተረዳ፣ ይህን ትግል የማያደራጅና የማይመራ በዲሞክራቲክ ትግሉና ከሶሺያሊስት አብዮቱ መለየት የማይችል ፓርቲ፣ "በወዝ አደሩ ስም" የሚያቀርባቸው ጥያቄዎች ቀይጥና የተመሰቃቀሉ መሆናቸው አይቀርም:: የኢ.ሕ.አ.ፓ ፕሮግራም ካሸበረቀባቸው የዲሞክራቲክና የሶሺያሊስት አብዮቱን ተግባሮች ከማያሟሉ ጥያቄዎች የረካ ምሳሌ ለመሥጠት፣ በፕሮግራሙ ውስጥ የታዘለውን የሚከተለውን ጥያቄ እንመልከት:: በአዲሲቱ ዲሞክራቲክ ኢትዮጵያ ውስጥ የግል ካፒታል የሚኖረውን ቦታ ሲገልጽ

"በኢምፔሪያሊስቶች ጥገኛ ያልሆነ የግል ካፒታል ከሀገሪቷ መሠረታዊ የኢኮኖሚ እቅድ የሚጋጭ ካልሆነ / እስካልተቃረነ/ የሕዝብን ጥቅምና ፍላጎት እስካልተፃረረ ድረስ፣ በሀገሪቷ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ፣ በተለይም በኢንዱስትሪ ውስጥ ተሳትፎ አይከለከልም /ገጽ 14/ " ይላል:: በእንግሊዝኛው በወጣው ፕሮግራሙ ደግሞ

"To allow private business activities particularly in the industrial sector as long as they are not linked with imperialism and are not conflicting with either the national economic policy or the interests of the masses."(E.P.R.P.s programme, p.11)

በፕሮግራሙ ውስጥ ተገኘ ወረድ ብሎ ደግሞ በአዲሲቱ ዲሞክራቲክ ኢትዮጵያ ውስጥ ስለ ወዝ አደሩ ጥቅምና መብት በሚያወራበት ወቅት፣ የተቃረነውን ይናገራል::

"ፋብሪካዎችና ዘመናዊ የመንግሥት እርሻዎች በሠራተኛው ሕዝብ ቁጥጥርና አስተዳደር እንዲውሉ ማድረግ የምርት አያያዝና በሠራተኞች ቁጥጥር ስር ማዋል / ገጽ 18 / በእንግሊዝኛው ትርጉም ደግሞ

"To put factories and modern farms under the full control and direction of the working people, to bring <u>all</u> production and distribution activities under the control of the workers" (EPRP:s programme, p. 17)

የፈረደበት ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት ብንዱ በኩል የግል ካፒታልን ወረቀቷል፣ በሌላ በኩል ደግሞ ጨርሶ ይከለከላል:: በቀኝ እጁ የሠጠውን በግራው ይነጥቃል:: በግራ የነፈገውን በቀኝ እጁ ይለግሳል::ግሩም ዲያሌክቲክስ!

መቼም እነዚሁ ሁለት ነጥቦች ተቃራኒዎች እንደሆኑ፣ የዲሞክራቲክና የሶሺያሊስት <u>አብዮቶችን</u> ማዛመድን እንደሚያሳዩ ለመገንዘብ አስቸጋሪ አይደለም:: በቲዎሪ አንጻር በመለከተው በአዲሱ ዲሞክራቲክ አብዮት በተሳለቀ ኢንዱስትሪዎች የሚተፈሩና እንዲሁም ከኢምፔሪያሊስቶች ጋር የሚተባበረው ካፒታል ወደ መንግስት እጅ ይዞዋራል፣ የተቀረው ካፒታል አይነካም፣ እንዲነካም የሕብረተ ሰቡ እድገት ደረጃ አይፈቅድም:: ለዲሞክራቲክ አብዮት አስትም፣ ሕብረተ ሰቡ ወደ ሶሺያሊስት አብዮት ደረጃ የሚሸጋገርበት ወቅት ግን፣ የፖለቲካል ሥልጣን በቻው የጨበጠው ወዝ አደር፣ በአርቢታ መዛሪያዎች በሙሉ ያለውን የግል ንብረትነት ያጠፋል፣ እብርጆም የካፒታል እገዛዝን ይሸራል:: ሀሮሳ የጨበጠው ወዝ አደር የምርትና የማከፋፈል ተግባሮችን(production &distribution activities) ሙሉ በሙሉ ቁጥጥሩ ውስጥ ያስገባል::

የኢ.ሕ.አ.ፓ ፕሮግራም የተመለከተን እንደሆነ ግን እነዚሁ ሁለት የተለያዩ ፕሮግራሞች፣ የዲሞክራቲክ አብዮትና የሶሺያሊስት አብዮት ኢኮኖሚ ፖሊሲያቸ ተማትው ሊያሳ የወጣቸዋል:: የንዑስ ከበርቴው፣ ፓርቲ የሆነው 'የኢ.ሕ.አ.ፓ' በወዝ አደሩና በከበርቴው መሀል እንደሚንከባለለው ሁሉ፣ የሚከተለው ፖለቲካ በሁለቱም ይጣመናል:: የኢ.ሕ.አ.ፓ ወደ ቀኝ ወደ ከበርቴዉ ሲዞር፣ 'አይዞህ ፣ በዲሞክራቲክ ሕብረተ ሰብ ውስጥ የግል ካፒታልህን አንነካም' እያለ ይማማላል፣ ወደ ግራ ወደ ወዝ አደሩ ሲንከባለው ደግሞ 'እለንሁ፣ በዲሞክራቲክ ሕብረተ ሰብ ውስጥ ምርት አያያዝ በሙሉ / በእንግሊዝኛ ፕሮግራም ትርጉም(all production & distribution activities) ሳለ/ በቁጥጥር ስር እናደርጋለን' ማለትን ያስተምራል:: እዚሁ ላይ የኢ.ሕ.አ.ፓ ፓርቲ እራሱን ለመግለጽ ካርል ማርክስ ስለ ፕሮዱሆን / prodhoun/ ከተናገረው፣



**He wanted to be the synthesis of both** /የቡርዡና ወዝ አደሩ/ **and ended up as the composite error "** የተሻለ ያለ አይመስለንም::

እስከዛሁን ድረስ ስለ የኢ.ሕ.አ.ፓ ፕሮግራም የጻፍነውን ለማጠቃለል፣ በኛ ግምት ይህ ፕሮግራም ሁለት ነገሮችን ያመለክታል:: አንደኛ ይህን ፓርቲ የገነቡት ሰዎች፣ከወዝ አደሩ ሰባት ዓመት ተኩል ተደብቀው 'ይታገሉለት' የነበረት፣ በወዝ አደሩ ላይ ስለሚበኖነው አስቃቂ ካፒታሊስት ጭቆና፣ ስለ እርሮውና ብሶቱ እንዲትም ቀንጣት እንደ ማያውቁ ያሳያል፣ እንዲሁም የኢትዮጵያ ወዝ አደር እስከዛሬን ድረስ ስለ ያካሄዳቸው ፀረ ካፒታሊስት ትግሎች፣ ስለ መደብ ትግሉ፣ የሚያውቁትም በጎዘር እንደሌለ ይጠቁማል:: የወዝ አደሩን ልብ ተርታ ያወቁ፣ ብሶቱንና ትግሉን የተካፈሉ፣ እንዴት አድርጉ የትግሉ አቀጣጪና ምንነት ለስተው ይችላል? በመደብ ደረጃ የወዝ አደሩ ቁና ፀር፣ ቀን ተቀን የሚጋፈጠው ጠላት፣ ፋብሪካ በምትባለው እሥር ቤት ምጥጥ አድርጉ የሚበዘብዘው፣ ወዘተ.... ካፒታሊስት ሲሆን እንደሆነ የማያመለጠው ነገር ነው:: የኢ.ሕ.አ.ፓ በዚሁ ትግል ተባታፊ መሆን ቀርቶ፣ ገለጸተኛም ተመልካች አይደለም::ከሁለቱም ወጪ! -

ሁለተኛ የኢ.ሕ.አ.ፓ እንደም የወዝ አደሩን ትግል በሚመለከተው በኩል ንዑስ ከበርቴዎች ያሳቸውን እይታ በጥሩ አኳኋን ያንፀባርቃል:: አብረው በዲሞክራቲክ ትግል ጊዜ ከወዝ አደሩ ጋር የሚሰለፉት የከበርቴው ሥርስት አፈ ቀላጤዎች፣ ወዝ አደሩን ኢምፔሪያሊዝምንና ጉልተኛውን ሥርዓት በመፋጅት ላይ ብቻ እንዲያተኩር በመገፋፋት፣ የፀረ ካፒታሊስቱን ትግል እንዲዘነጋ እነርሱም የመደብ ጠላቶች እንደሆኑት ለማረጋጋትና እርሱን የሶሺያሊስቱን አብዮት ለማስተው ይሞክራሉ:: ይህም በታሪክ ብዙ ጊዜ ያየነው ነገር ነው:: ለምሳሌ በሩሲያ ውስጥ በ1895–1900 ጊዜ አካባቢ ውስጥ ማርክሲስትን ነን በማለት የከበርቴው አፈ ቀላጤዎች የሆኑት/**legal marxists** የተባሉት/ የተጫወቱትን ሚና መመልከት ይበቃል::

ይህ ፕሮግራም የወዝ አደሩ ፓርቲ ፕሮግራም እንዳልሆነ በበለጠ ለማብራት ምንጮችን /አንድ ነገር ማወቅ ከሥሩ / ማወጣጣት ባይጠቅምና አይቀርምና ወደ መሠርሠሩ እንሻገር:: በውነቱ ይህ ፕሮግራም በምንም አይነት የኢትዮጵያ ወዝ አደር ታሪካዊ ሁኔታ የትግል ኤክስፒሪያንስ /**experience**/ን ያንፀባርቅም፣ አንድ ማርክሲስት ፕሮግራም መሆን እንዳለበትም ይህን የወዝ አደሩን የትግል ኤክስፒሪያንስ ጨምቆ፣ አብሳለትና አስጥሮ ለወደፊት ትግል አቅጣጫ ጠቋሚ አላደረገውም:: እርሱ እንደ ቀርቶ ' የቡበት ዓመት ተኩል ' የትግል

ኢምፔሪያሊዝምን በፕሮግራሙ ውስጥ አለተጠቀለለም / ይህን የምንለው ከፕሮግራሙ ለማየት እንደምንችለው፣ ደርጉ የከተማ መሬት አዋጅ ካወጣ በኋላ ማለትም ከሰኔ/ከሐምሌ 1975 ወዲህ ስለተጻፈ ነው፡፡ ፓርቲው 1971 ቢቋቋም፣ ፕሮግራሙ የተነደፈው 1975 ላይ ነው፡፡ በዚህ መሀል ያለው "የትግል" ዘመን ውጤት ፕሮግራሙ ውስጥ አልተጠቀሰም ነው የምንለው/ ይህን ፓርቲ ፕሮግራም የነደፉት በኋላ የኢትዮጵያን ወዝ አደር ታሪካዊ ሁኔታ ትግል ሆነ፣ ሦስት ዓመት ተኩል ታግለናል የሚሉትን አባባል በንቀሰላቸውም የምናየው ይህንኑ የ3 ዓመት ተኩሉን "ትግል" እራሳቸው ከመጤፍ ሳይቆጥሩት፣ ፕሮግራማቸውን በሚቸከችኩበት ወቅት ከደቡብ ቬትናም ነጻ አውጪ ግንባር /natinal liberation front of s.Viet./ ፖለቲካ ፕሮግራም እንዳለው ቃል በቃል ጠብረጁን እንደ ወርጡ ነው፡፡ ቢያንስ 60 % የፕሮግራማቸው አካል ቃል በቃል የተገለበጠ ነው፡፡ ቬትናም በሚለበት ቦታ ኢትዮጵያ እያስቀመጡ፣ ለኢትዮጵያ ወዝ አደር ይኸውልህ፣ ላንተ የሚበጅ ፕሮግራም አወጣንልህ ይሉታል፡፡

ጦብረጁ ይጠቀማል ወይስ ይገዳል ወደሚለው ጥያቄ ከመነሣት በፊት ከዶንት ተብረዶ የሚለው ጥያቄ ስለሚቀድም፣ ስለ የደቡብ ቬትናም ነጻ ውጪ ፕሮግራም የተነደፈበት ሁኔታ፣ ምንነትና የትኞቹ ሕብረተ ሰባዊ ሀይሎች እንደነደፉት ማውቁ ያስፈልጋል፣ የነጻ አውጪ ግንባሩንም አፈጣጠር ታሪክ መግለጹም ይጠቅማል፡፡ የንጎ ዲንህ ዲያም / **Ngo Dinh Diem** / ፋሺስታዊ መንግስት የ1954ን የጀኔቭ ሰላም ውርውር አፍርሶ፣ የሀገሪን ሕዝብ በፀረ አብዮት አመጽ ሲገዛና ጭቆናው እየመረረ ቢሄድ፣ በዚሁም መጠን የደቡብ ቬትናም ሕዝብ ቁጣ እየሰፋ፣ ትግሉ ተፋፋመ፡፡በ1958 እና 1959 በቀድሞ የቬት ሚንህ አርበኞችና በመንግስቱ ወታደሮች መሀል ግጭቶች መካሄድ ጀመሩ፡፡ ትግሉን የሚያቀነባብር ድርጅት አስፈላጊነት በመረዳት በግንቦት 1960 "የናም ቦ. ቀድሞ አርበኞች ማህበር" ስለ ደቡብ ቬትናም ጊዜያዊ ሁኔታ መግለጫ አውጥቶ በዚሁ መግለጫ ውስጥ የንጎ ዲንህ ዲየም መንግሥት ተገለበጦ በቦታው ሕዝባዊ መንግስት መቋቋም እንዳለበት በማሳየት፣ ለወደፊቱ ትግል ጥሪ አደረገ፡፡ ይህንም በመከተል በታህሳስ 1960 የሚከተሉት ድርጅቶች በተገኙበት ጉባዔ የደቡብ ቬትናም ነጻ አውጪ ግንባር ተቋቋመ፣ 10 ነጥቦች ያሉትም ፕሮግራም ፀደቀ፡፡ በዚሁ ጉባዔ ላይ ተገኝተው የነበሩት ዋና ድርጅቶች

ሀ/ የናም ቦ. ቀድሞ አርበኞች ማኅበር

ለ/ **RADICAL SOCIALIST PARTY** / የንዑስ ከበርቴ ፓርቲ/

ሐ/ **DEMOCRATIC PARTY** / የብሔራዊ ከበርቴ ፓርቲ/

መ/ የተለያዩ አያሌ የሃይማኖትና የፖለቲካ ቡድኖች

ፕሮግራሙም ግንቦት 1960 "የናም ቦ. ቀድሞ አርበኞች ማኅበር" ባወጣው መግለጫ በመረከዙም፣ ጉባዔው ላይ በተገኙት ከበርቴ ኃይሎች አስባቢነት በርከት ያሉ ለውጦችና ማሻሻያዎች ተደርገውበት ነው የጸደቀው፡፡ እዚህ ላይ ማስታወስ ያለብን፣ የደቡብ ቬትናም ነጻ አውጪ ግንባር በተቋቋመበት ወቅት ማርክሲስት ፓርቲ እንዳልነበረ ነው፡፡ በዚሁ ግንባር ውስጥ ማርክሲስቶች የተሳተፉት በግለ ሰብ ደረጃእንጂበፓርቲ አባልነት አልነበረም፡፡ እንዲያውም የደቡብ ቬትናም ወዝ አደር ፓርቲ የተቋቋመው ነጻ አውጪ ግንባሩ ከተመሠረተ በሁለት ዓመት ማለትም በ1962 ነበር፡፡



እንግዲህ ለማጠቃለል ያህል ሀ/ ነጻ አውጪ ግንባሩ በተቋቋመበት ወቅት የማርክሲስት ሌኒኒስት ፓርቲ አልነበረም፣ ማርክሲስቶች ግንባሩ ውስጥ በግለ ሰብ ደረጃ ነው የተሳተፉበት

ለ/ የነጻ አውጪው ግንባር ፕሮግራም ሕብረት ግንባር /**UNITED FRONT** / ፕሮግራም፣ ከአገር ወዳድ ፊውዳሎች አንስቶ እስከ ኮሚኒስቶች ድረስ ባንድ ትግል መድረክ የሚያስተናግድ ፕሮግራም ነበር፡፡

ይህ ሁሉ ግን ለኢ.ሕ.አ.ፓ ሰያሜ ሰውር ነው፡፡ በደቡብ ቬትናም ለኮሚኒስቶች አብዮቱ አንዱ የተወሰነ ደረጃ የሚሰጠውን የዩናይትድ ፍሮንት / **UNITED FRONT** / ፕሮግራም በመሠረቱ እንዳለ ገለበጠው፣ ላይ ላዩን እንዴ ሁለት ሦስት የተወሰኑ "ስሺያሊስት ቃላቶች" / ከፍ ብለን አይተናቸዋል/ ነስንሰውበት፣ የኢትዮጵያን ወዝ አደር ወደ ኮሚኒዝም የሚመራው ፕሮግራም አወጣን ይላሉ፡፡

ይህ ዓይነቱ አሠራር ዘዴ የሚያሳየው የደቡብ ቬትናም ነጻ አውጭ ግንባር ታሪካዊ ፋይዳ አለመረዳታቸውን ብቻ ሳይሆን፣ በተደጋጋሚ የኢትዮጵያን ወዝ አደር ትግል ምንነትንም እንደማያውቁት ነው፡፡ የፖለቲካ ኪሳራነትም ምስክር ነው፡፡

ይህን ዓይነቱ የከበረ አሠራር ዘዴ በምንተቸበት ወቅት አብዮታዊያን ከሌሎች ሕዝቦች ትግል ታሪክ አይማሩ፣ አስፈላጊውንና ተገቢውን ትምህርት አይቀስሙ ለማለት አይደለም፡፡ ፈጽሞ! እንዲያውም የዓለም ሕዝቦች ፀረ ኢምፔሪያሊስት ትግል የተያያዘ በመሆኑ፣ መደጋገፍ፣ መተባበርና፣ የአንዱ ከሌላው መማር ምንም ጊዜ ቢሆን አስፈላጊ ነው፡፡ የሌሎች ሕዝቦች ትግል ኢምፔሪያሊዝምን በማጤን፣ የፈጸሟቸውን ስህተቶች በመጸግም እንጠብቃለን፣ የሚያዋጡንና የማያዋጡን የትግል ዓይነት በበለጠ ለማመዛዘን እንችላለን፣ የጋራ ጠላታችንም ድክመቶች የበለጠ እናውቃለን፣ ትግላችንንም በምንጀምርበት ወቅት በሌሎች ሕዝቦች ትግል ኢምፔሪያሊዝም ትከሻ ላይ የቆምን ስለሆንም፣ የትግሉ አቅጣጫውን በተሻለ አኳኋን ለመቀየስ እንችላለን፡፡ እኛ እምንቃወመው የሌሎች አብዮቶች ኢምፔሪያሊዝምን ሳይጤኑ፣ <u>የሁኔታና</u> የጊዜ ልዩነት ሳይለዩ፣ እንዳለ በደፈናው በኢትዮጵያ ሁኔታ ላይ መለጠፍ መሞከሩን ነው፡፡

ለምሳሌ የኢትዮጵያና የደቡብ ቬትናም አብዮቶች መሠረታዊ የሆኑ ልዩነቶች አሏቸው፡፡ የደቡብ ቬትናም ነጻ አውጪ ግንባር ፕሮግራም በተነደፈበት ወቅትና በትግሉ ዘመን የቬትናም ሕዝብ ዋና ጠላት የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ነበር፡፡ ይህ ፕሮግራም የወጣው በተቀዳሚ ደረጃ ፊውዳሊዝምን ሳይሆን ኢምፔሪያሊዝምን ለመዋጋት፣ ለዚሁም ዓላማ ኢምፔሪያሊዝምን ሊወጉ የሚችሉትን ኃይሎች በሙሉ / አገር ወዳድ ጉልተኞችንም ጭምር/ በአንድ የፖለቲካ መድረክ ለማሠለፍ ነበር፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ ግን ምንም እንኳ ኢምፔሪያሊዝምና ፊውዳሊዝም ሁለቱ የኢትዮጵያ ሕዝቦች መሠረታዊ ጠላቶች ቢሆኑም፣ ባሁኑ ወቅት ኢምፔሪያሊዝም በቀጥታ ባይሆን

/ለምሳሌ እንደ ቬትናም በወረራ ወቅት/ በተዘዋዋሪ ተጽዕኖውን በሚያሰማበት ጊዜ፣ ለሕዝቡ ትግል ይበልጡኑ የሚያተኩረው በጉልተኛውና ሥርዓትና በመንግሥት አውታሮች ነው:: ይህማለት የደቡብ ቬትናም ነፃ አውጪ ግንባር **united front** ፕሮግራም፣ ለኢትዮጵያ ፀረ አድር ኮሚኒስት ፕሮግራም መሆን መቻሉ ቀርቶ፣ ባሁኑ ወቅት ኢትዮጵያ ውስጥ ሊፈጠር ለሚችል ፀረ ኢምፔርያሊስትና ፀረ ፊውዳሊስት አንድነት ግንባር እንኳ ፕሮግራሙ ሊሆን አይችልም::

አንዷት ነገር ይገም:: የኢ.ሕ.አ.ፓ ፕሮግራም የነደፉት ሰዎች፣ የቬትናምን ሕዝብ አብዮታዊ ታሪክ ሳይ ሳዩን ባይሆን፣ ጠለቅ ብሉ ቢያውቁት ኖሮ፣ የቬትናም ተጋዮች በሌሎች ሕዝቦች ትግል ስለ መማር የተናገሩትን ልብ ብለው በተገነዘቡት ነበር:: የቬትናም ሕዝብ አባትና ታላቅ ኮሚኒስት ሆ.ቺ. ሚኒህ ስለዚህ ሲናገር "ከሌሎች አብዮታዊ እንቅስቃሴዎች መማር አለብን፣ ሆኖም ለኛ የሚበጀው ታክቲክ በቬትናም ተጨባጭ ሁኔታ መፍለቅ አለበት" ያሉትን ባስታወሱ ይበቃል::

<u>ዲሞክራሲና አብዮት</u>

በየአገሩ ያሉት ኮሚኒስቶች ግባቸውን ለመድረስ የሚጥሩት በአብዮት አማካኝነት ነው:: ለምን? ምክንያቱም ገዥ መደቦች ምንም ቢሆን የያዙትን የፖለቲካ ሥልጣን አሳልፈው ለወዝ አደሩና ለሰፊው ሕዝብ እንደማይሰጡ፣ ነጻነት በትግልና በአብዮት ኀይል ብቻ እንደሚገኝ ስለሚያውቁ ነው:: በመደብ ትግል ያሉኝት እንደሌለ፣ የመደብ ትግልና የፖለቲካ ሥልጣን ጥያቄዎች በመጨረሻ ደረጃ በጉልበት ብቻ እንደሚወሰኑ በደንብ አጽርገው ያውቃሉ:: ይህም በበንት ቪ እና ሚሊዮን ወዝ አደር ደም የተገኘ ትምህርት ነው:: ስለዚህም ነው በለ አብዮትም ያለው አይም፣ የአንድ ኮሚኒስት ፓርቲ "ኮሚኒስትነት" መፍተኛና ዋቸ ከሆኑት አንዱ የሆነው:: ይህ ሁሉ የማያስቢንቀው "ማርክሲስት ሌኒኒስቱ" የኢ.ሕ.አ.ፓ የሚከተለውን ቢል እናገኘዋለን:: "መንግሥ ያዘለ ይገዛህ የሚል ፈሊጥ አያውቁም" የዲሞክራሲያዊ መብቶች ከተጠበቁለት በዲሞክራሲያዊ መንገድ ይታገላል፣ ዲሞክራሲያዊ መብቶችን ከተነፈገም አብዮቱ ግቡን እንዲመታ አስፈላጊ የሚሆኑትን የትግል ዘዴዎች ሁሉ ይጠቀማል" / ገጽ 7 /

ለገዥ መደቦች ቃለ ቢዳንና ማስፈራሪያ! የዲሞክራቲክ መብቶች የጠበቃችሁልኝ / ማን ሊጠብቅለት ነው / እንደሆነ፣ "አብዮቴን" በዲሞክራቲክ መንገድ ግቡን እንዲደርስ የምታገል መሆኔን ቃሌን ሰጣለሁን! ነገር ግን ዲሞክራቲክ መብቶቼን ያልጠበቃችሁ እንደሆነ፣ ወዮላችሁ! አስፈላጊ በሆኑ በሌሎች /ገዢውን መደብ ምን ይመጣብኝ ይሆን በሚለው ለማርበትበት / የትግል ዘዴዎች እጠቀማለሁኝ ይላል የኢ.ሕ.አ.ፓ. ፕሮግራም

ለኢ.ሕ.አ.ፓ የዲሞክራቲክ መብቶች "የተጠበቁለት"/!!/ እንደሆነ፣ በዲሞክራቲክ መንገድ "አብዮቱን" ወደ ግቡ ለማድረስ ይታገላል:: እዚህ ላይ



የኢ.ሕ.አ.ፓ እንደተራ ኀውስ ከበርቴ የሚረሳው <u>አብዮት</u> ራሱ ማናቸውም ደንብና ሕግ የሚያውቅ፣ እንደናው ሕብረተ ሰብ ከፍል የሌላኛውን መብት የማይጠቀስትና የራሱን ፍላጎት በጠመንጃ ኃይል በተቃራኒው ላይ የሚጭንበት ድርጊት መሆኑን ነው:: ለዚሁም ነው እነ ሊቀመንበር ማኦ

"A revolution is not a dinner party, or writing an essay, or painting a picture, or doing embroidery;,it cannot be refined, so leisurely and gentle, so temperate, kind,courteous, restrained and magnanimous. A revolution is an insurrection, an act of violence by which one class overthrows another." (Sell. Works,Vol.I,P.28)

የዲሞክራቲክ መብቶች "ከተጠበቁለት" በዲሞክራቲክ መንገድ የአብዮትን ግብ ለመምታት እንታገላለን የሚል ወዝ አደሩንና ሰፊውን ሕዝብ እንዲሁም አብዮትን የከዳ፣ ጊዜን ጠቀለሉ ወደ ጠላት ሠፈር የገባ ብቻ ነው:: ይህ የአንድ ኮሚኒስት አቋም ሳይሆን፣ እነ በርንስታይንና ከውትስኪን የመሳሰሉትን ከሃዲዎች አቋም ነው:: በማርክሲዝም ሌኒኒዝም አንጻር ዲሞክራሲ ሁልጊዜ የመደብ ይዘት ያለው፣ ያንዱ የተወሰነ መደብ አገዛዝ ዘዴ ነው:: ለምሳሌ የቡርዧ ዲሞክራሲ የሚጠቅመው ከበርቴው ሲሆን፣ ለወዝ አደሩ የሚበጀው ደግሞ ሶሺያሊስት ዲሞክራሲ ነው:: ወዝ አደሩ ሥልጣን ባልጨበጠበት አገር፣ ተገዢ በሆነበት፣ ሊኖር የሚችለው ዲሞክራሲ የከበርቴው ዲሞክራሲ ሲሆን፣ የገዢው ከበርቴ መደብ ጥቅም የሚያስጠብቅ፣ በስመ ዲሞክራሲ አገዛዙን የሚያካሂድበት ሥርዐት ነው:: በዚሁ የከበርቴው አገዛዝ መሣሪያ በሆነው በቡርዧ ዲሞክራሲ አማካኝነት ወዝ አደሩ የፖለቲካ ሥልጣን ምንም ጊዜ ቢሆን ሊጨብጥ አይችልም::

እነ ማርክስና ኤንገልስ ወዝ አደሩ አብዮትን ለማካሄድ በቡርዧ ዲሞክራሲ መብቶች ሆነ በቡርዧ ዲሞክራቲክ ሥርዓት አማካኝነት የፖለቲካ ሥልጣን መጨበጥ እንደማይችል፣ ይህን ሥርዓት በአብዮታዊ አመጽ ሽሮ በሶሺያሊስት ዲሞክራሲና በወዝ አደሩ ዲክታቶርመንትነት እንዲተካ ያስተምሩናል:: በቡርዧ ዲሞክራሲ አማካኝነት የሶሺያሊስት አብዮትን ግብ ደርሳለሁኝ ማለት ዘበትም ብቻ ሳይሆን በሪፎርሚዝምና በከሓዲነት ማጥ መስመጥም ነው:: ኢትዮጵያም ውስጥ ሻሳቸነት ጣርሞት በኢ.ሕ.አ.ፓ አምሳል በዚሁ ማጥ ውስጥ በመንገዳገድ ይገኛል::

የኢ.ሕ.አ.ፓ እንደሚለው ሳይሆን ቡርዧ ዲሞክራቲክ መብቶች በሚከበሩባቸው አገሮች ኮሚኒስቶች በነዚሁ መብቶች እየተጠቀሙ፣ በሰፊው ሕዝብ መሀል ቀስቀሳና ፕሮፓጋንዳ በማድረግ ለመጪው የመደብ ጦርነት፣ በአብዮታዊ አመጽ የፖለቲካን ሥልጣን ለመጨበጥ ለሚደረገው ትግል፣ ሃይሎቻቸውን ይሰበስባሉ፣ ያዘጋጃሉ:: በሌላ አነጋገር አብዮታዊን አመጽ ይህና ሰንበት ለማለት ሳይሆን፣ አብዮታዊው አመጽ የተሳካ እንዲሆን አስፈላጊው ዝግጅት ለማድረግ ነው:: ይህ ግን ከሓዲዎችና ሪፎርሚስቶች የማይገባቸው ባዕድ ጉዳይ ነው::

ማን ይምራ?

አንድ ኮሚኒስት ፓርቲ ወዝ አደሩን በሚገባ ለመምራትና ድሉን ለመጎናጸፍ ከፈለገ በርሱና በወዝ አደሩ መሀል ያለውን ግንኙነት አበጥሮ ማወቅና መወሰን መቻል አለበት:: ማለትም ከወዝ አደሩ መደብ ጋር ያለውን ልዩነትና አንድነት፣ ወዝ አደሩን በሚመለከተው በኩል ያለበትን ተግባር አጣርቶ ማወቅ ይኖርበታል:: መሪ ተከታዩን፣ ተከታዩ የሚያስፈልገውን፣ ተከታዩ ከመሪው የሚጠብቀውን ካላወቀ የመሪነትን ተግባር በሚገባ ሊያገባድድ አይችልም:: ለዚህም ነው ለምሳሌ ካርል ማርክስ በኮሚኒስት ማኒፌስቶ ውስጥ ወዝ አደርና ኮሚኒስት በሚለው ምዕራፍ ሥር ይህን ጥያቄ አንስቶ በሚገባ የመለሰው:: በርሱ አባባል

"The communists, therefore, are on the one hand, particularly the most resolute section of the working class parties of every country, that section which pushes forward all others on the other hand, theoretically, they have over the great masses of the proletariat the advantage of clearly understanding the line of march, the conditions and the ultimate general results of the proletarian movement."

ማርክስ በወዝ አደሩና በኮሚኒስት ፓርቲ መሀል ያለውን ግንኙነት ሲያስረዳ፣ ኮሚኒስቶች በገቢር የወዝ አደሩ በጣም የተራመደና ታጋይ ክፍል፣ የቀረትንም ወደፊት የሚገፋፋ፣ በሐሳብ ንቃትም ከብዙው ወዝ አደር ከፍ ያለና የትግሉን አቅጣጫ ሁኔታንና ግብ በሚገባ የተረዳው ወገን ናቸው ይላል::ወደ የኢ.ሕ.አ.ፓ ፕሮግራም ዞር ብንመለስለዚሁ ጥያቄ የምናነበው ሌላ ነገር ነው:: እርሱም እንደሚከተለው ነው::

'የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ከጎንህ የቆመ ጠበቃ እንጂ አንተን የሚተካ ነገረፈጅ አይደለም፣ ከፊትህ የተሰለፈ መንገድ መሪ፣ የጠላትን ረቂቅ ሤራ በባዶ የቀኝ እጅህ አንጂ፣ ባንተ ፈንታ የቆመ የአብዮት መሪ፣ ባንተ ስም የሚመጻደቅ ፍከሪ አምባገነን ኃይል አይደለም:: አብዮትን መምራት ያንተ ፈንታ ነው:: ስለሆነም ጠበቃህን፣ ግንባር ቀደም አካልህን፣ ኢ.ሕ.አ.ፓን ደግፈው፣ አቋቁመው፣ ምራው፣ በትግሉ ጎዳና እንዳይዘነጋ አንድ ዓይንህ ብሌን ጠብቀው::' /ገጽ 29/

የኢ.ሕ.አ.ፓ ለወዝ አደሩ ከፊትህ የተሰለፍኩኝ መንገድ መሪ ነኝ እንዲል ምናልባት በድፍረት ከማፈርም ሊሆን ይችላል ትንሽ ወረድ ቢል ደግሞ ባንተ ስም የምመጻደቅ ፍከሪ አይደለሁም፣ አብዮትን መምራት ያንተ ፈንታ ነው ማለቱ ያስገኛል:: እንደገና ወደታች ደግሞ ሽር ተተ ይልና፣ ግንባር ቀደም የሆንኩትን አካልህን /ምን እንደሆንኩ አትርሳ ነው/ አንተው ወዝ አደር ተሸክመህ ምራኝ ይሆናል ነገሩ:: በውነቱ ይህን ሲነበብ ወዝ አደር ትልቅ ራስ ምታት የሚሆነው ጥያቄ ማን ማንን ይምራ? የሚለው ነው::መቼም 'እኔ ልምራህ አንተ ምራኝ' የሚለው ዉጥታ ፍቺ አለው ቢባል ሁለቱም ክብ ሠርተው የሚሯሯጡ እንደሆኑ ብቻ ነው::



በማርክሲስት ሌኒኒስት አንጻር ነገሩን የተመለከትነው እንደሆነ ግን ፓርቲው የወዝ አደሩ ተራማጅና የነቃ ክፍል እንደመሆኑ መጠን፣ የወዝ አደሩን መደብ ይመራዋል እንጂ በርሱ አይመራም::ወዝ አደሩም አብዮትን /የትኛው አብዮት እንደሆነ መግለጽ ነበረበት/ መራ ስንልም፣ በፓርቲው አማካኝነት አብዮትን መራ ለማለት ነው:: አብዮትን በአንተ ስም አስመራም፣ አብዮትን የመምራት ፈንታ ያንተ ነው የሚል 'ኮሚኒስት' ፓርቲ ፈጽሞ ሊኖር አይችልም::

አንድ ኮሚኒስት ፓርቲ በወዝ አደሩ ስም አብዮትን ለመምራት ካልታገለ፣ ወዝ አደሩንም ለዚሁ ዓላማ ካላሰለፈ፣ እሕዓት አይሮን አብዮትን የመምራት ፈንታ የወዝ አደሩ ነው ሊባል እንደሚቻል ፍጹም ስውር ነው::ይህቺም ሌላ የሠነቀ ሥላሴዎች ምሥጢር ባትሆን አትቀርም::

ደግሞስ የኢ.ሕ.አ.ፓ ነኝ እንደሚለው የኢትዮጵያ ወዝ አደር ጠበቃ ያስፈልገዋል ወይ? ማንስ ሊዳኝለት ነው? ኦገስት ቤበል፣ የጀርመን ወዝ አደር መሪ፣ ጠበቆች አውሀሪዎች ናቸው ሲል ትልቅ እውነት ተናገረል:: ምክንያቱም ጠበቆች የአረጀው ሥርዓት ሕግጋትን በመጠምዘዝ ስለሚኖሩ፣ እንዲሁም ጥቅማቸውም ከዚሁ ሥርዓት ጋር የተሣሠረ ነው:: ለኢትዮጵያ ወዝ አደር እንዲህ ዓይነት ተቆርቋሪ መመኘቱ፣ የኢትዮጵያን ወዝ አደር ለጠላቶቹ አሳልፎ መሥጠት ነው:: የኢትዮጵያ ወዝ አደር የሚፈልገው ጠበቃ ባይሆን፣ የመደብ ትግሉን የሚያደራጅለትን፣ የትግሉን አቅጣጫ የሚያሳየው ግንባር ቀደም የሆነ አብዮታዊ መሪ ነው::

ክፍል ሁለት

የኢ.ሕ.አ.ፓ ፕሮግራም ለወዝ አደሩ እንደሚያደላ፣ የአንድ ወዝ አደር ፓርቲ ፕሮግራም እንዳለሆነ ካረጋገጥን በኋላ፣ ኢትዮጵያ ውስጥ አሁን በመካሄድ ላይ ካለው ዲሞክራቲክ አብዮት ጋር ያለውን ወይም ሊኖር የሚችለውን ግንኙነት ወደ መመልከቱ እናምራ:: ይህ ነጥብ ከፍተኛ ግምት ሊሠጠው ይገባል:: ምክንያቱም የአንድ ፓርቲ ምንነት የሚታወቀው በአቋሞቹ፣ ለምሳሌ በሶሺያሊዝም ወዘተ.. በሚናገረውና በሚወጣቸው አጠቃላይ ግምቶች ብቻ ሳይሆን፣ ይበልጡኑ በሁኑ ወቅት በሚካሄደው እንቅስቃሴ ላይ ባለው አቋም፣ በዚህ እንቅስቃሴ ውስጥ ለወዝ አደሩ ጥቅም በሚያደርገው ትግልና በሚያነባቸው ጥያቄዎች አማካኝነት ነው:: ማለትም በዲሞክራቲክ እንቅስቃሴ የሚጫወተውን ሚና፣ ለዚሁ ትግል የሚሰጠውን ፕሮግራሙን መመልከት ያስፈልጋል:: በዚህ አኳያ የኢ.ሕ.አ.ፓ ፕሮግራም የሚያነሣውን ጥያቄዎች በማጤንና ከዲሞክራቲክ ትግል ያላቸውን ግንኙነት በመመርመር፣ የዚሁ ድርጅት ፀረ ወዝ አደርነትና አወናባጅነት ይበልጡኑ በር ሃን እንደሚያርፍበት እናምናለን::

የኢ.ሕ.አ.ፓ ፕሮግራም ጥያቄዎችን ከመርመራችን በፊት አንዳንድ አስተያየቶችን እናስቀድም:: የኢ.ሕ.አ.ፓ ፕሮግራም በየአደባባዩ ለሕዝብ በተበተነበት ወቅት፣ አንዳንድ አበይ ጥያቄዎች ገና ፀር ጊዜው ያለፈባቸው፣ የነፈበባቸው ጥያቄዎች ነበሩ:: ይህን እናስረዳ:: ከፕሮግራሙ ይዘት ለማየት እንደሚቻለው፣ ለምሳሌ "የመሬት አዋጅ ሥራ ለማዋል አስቸግሮአል" ወዘተ.. ከመጋበሱት አባባሎች ፕሮግራሙ ከ1975 አጋማሽ ወዲህ እንደተነደፈ ነው:: ይህ ሆኖ ባለ፣ ማለትም ደርጉ "የመሬት አዋጁ" ካወጣ ወዲህ፣ በመሠረቱም ከዚህ የተሻለ አዋጅ ሊጋጣ እንደማይቻል አውቀ ሆኖ ባለ፣ በኢ.ሕ.አ.ፓ ፕሮግራም ውስጥ የምናቋቁመው ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት /ወደፊት ማለት ነው/ የመሬት አዋጅ ያወጣል መባሉ ምን ፍቺ እንደሚኖረው ግልጽ አይደለም:: ከኢትዮጵያ አብዮት አፈገት በኋላ፣ እያን እንኳያውም ከደርጉ በኋላ፣ መቀረትን አያመለከትም? የጠ ተራማጅ የሆነ የመሬት አዋጅ አለ ከተባለ፣ ወደፊት የመሬት አዋጅ ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግስታችን ያወጣል ምን ለማለት ነው? ምናልባት የወጣውን ለመሻር፣ ለመቀልበስ? ባሁኑ ጊዜ የኢትዮጵያ ሁኔታ የሚጠይቀው ወደፊት የመሬት አዋጅን እናወጣለን ማለት ሳይሆን፣ ይህ ከኢትዮጵያ አብዮት ጋር አብሮ አለመራመዱን ያመለክታል፣ የወጣው አዋጅ የኢምፔሪያሊስቶች፣ ጉልተኞች፣ ቢሮክራቢውና ደርጉ ውስጥ ያሉትን ቀኝ ሀይሎች ተደምስሰው ሥራ ላይ የሚውለበትን መንገድ መጠቆም ነው::

የፕሮግራሙን ጥያቄዎች በሚመለከት የምናነሳው ነጥብ ደግሞ፣ እነዚህ ጥያቄዎች የአንድ መንግስት ማለትም "የጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግስት" ፕሮግራም መሆናቸውን ነው:: ከላይ እስከታች ማለትም ከረዳፍ አንድ እስከ አሥር፣ የፓርቲው ጥያቄዎች ናቸው ተብለው የቀረቡት ጥያቄዎች በሙሉ፣ በመቀጸበት ተቀይረው "የጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግስት" ተግባሮች ይሆናሉ:: ከፕሮግራሙ ቋንቋ እንኳ ይህን ለማየት ይቻላል፣ ለምሳሌ "መንግሥት አርሻን ያሻሽላል፣/ገጽ 11/፣ ሕብረተ ሰብ አርሻ ሠራተኞች መንግስት የሕክምና አገልግሎት ያቀርባል /ገጽ 11/ ወዘተ.. ማለትም "የኮሚኒስት" የኢ.ሕ.አ.ፓ ፕሮግራምና እነ እስፋው ወስን እንኳ ባይቀሮ ይቀምሳን የሚሉት "ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግስት" ፕሮግራም ሁለቱም አንድ ሁነው ቀሩ ይሰሉ

እንዲሁም ፕሮግራሙ የሚያነሣቸው ጥያቄዎች በትንቢት ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት እንደፈጸማቸው ተግባሮች ሆነው ስለተቀመጡ፣ ባሁኑ ወቀት፣ ባሁኑ ትግል ዘመንና በመካሄድ ላይ ባለው ዲሞክራቲክ አብዮት ጎዳና መፈጸም ያለባቸውን መፈጸም የሚቻሉትን ጥያቄዎች አያነሣም:: ምን ማለታችን እንደሆነ እናስረዳ:: ለምሳሌ ይኸው ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግስት፣ የብሔራዊ ዲሞክራሲ ኢኮኖሚ ለመገንባት በሚያደርገው ጥረት በፕሮግራሙ መሠረት፣

"የገጠር መሬት በድሀና በመለስተኛ አርስ አደሮች መሬት በገበር ወደ ሰፊው ሕዝብ እጅ እንዲገባ ማድረግና ወደ ቀደሞ ባለገበሮች እንዳይመለስ መታገል፣ ለዚህም ድሀና መለስተኛ አርሶ አደሮች እንዲደራጁ ማድረግና በሚገባ መሣሪያ ማስታጠቅና በየገበሬ ማኅበሮች ውስጥ ሕዝባዊ አብዮታዊ የትጥቅ ዘብ እንዲቋቋም ማድረግ" / ገጽ 10 / ይላል::



ነገር ግን የኢትዮጵያ ጊዜያዊ ተጨባጭ ሁኔታ በመለከት የገበሬዎች መታጠቅ ባሁኑ ጊዜ መከናወን ያለበት የአብዮቱ ዋና ተግባር ሲሆን፣ ይህን ተግባር ወደ "ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግስት እጅ ማስተላለፉ የጊዜውን ተግባር መሳት ብቻ ሳይሆን አርሱንም ማደናቀፍ አይደለም ወይ? ለምንስ ነው ይህ ጥያቄ "ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት" እስኪመሠረት መተላለፍ ያለበት? የኢትዮጵያ አብዮታዊ አፈር ገፊ ለመታጠቅ የሚፈልገው አሁን ነው:: እውነተኛ ተራማጆች እንደሚያደርጉት ይህ አብዮታዊ ጥያቄ አሁን እንዲሟላ ከመታገል ይልቅ፣ የሚነገረን በመጀመሪያ "ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግስት" ይምጣልን ነው::ወደ ጦር ሜዳ የሚዘምተውን አብዮታዊ ገበሬ "ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግስት" ከተቋቋመ ወዲህ መሣሪያ እሰጥሀሉን የሚለው አባባል ምንኛ ሊያጸናናው እንደሚችል ለአንባቢያችን ፍርዱ እንተወዋለን::

አንድ ሌላ ምሳሌ ደግሞ እንስጥ::በኢ.ሕ.አ.ፓ ፕሮግራም የሠራተኛው ሕዝብና ጥቅምና መብት ለመጠበቅ በሚለው አርእስት ሥር ይኸው "ጊዜያዊ መንግስት" የሠራተኛውን መደበኛ የሥራ ሰዓት በቀን ከ8 ሰዓት እንዳይበልጥ የሚያደርግ መሆኑን ይገልጿል:: እዚህ ላይ ፕሮግራሙን ሳነበበ ግልጽ የማይሆነው ነገር፣ / ምናልባትም አንደገና የሠነቀ ሥሳቢያች ምሥጢር ሊሆን ይችላል/ ለምን ወዘ አደሩ በሚካሄደው ፀረ ካፒታሊስት ትግል አማካኝነት፣ የኢ.ሕ.አ.ፓ ከሚመኘው "ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግስት" ከመመሥረቱ በፊት፣ የስምንት ሰዓት ሥራ ወሰን ሊያስከብር እንደማይችል ነው:: ምን የሚያግደውስ ነገር አለ? "ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግስት" ተመሥርቶ፣ ሠራተኛውን እስኪያገርሰው ድረስ መጠበቅ ነው ወይ የሚገባው? ላይ ከቀረቡት ምሳሌዎች ለማየት እንደሚቻለውም የኢ.ሕ.አ.ፓ ፕሮግራም የኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ትግል ለሚያነሣቸውና አሁን መሟላትና መፈጸም ላለባቸው አብዮታዊ ጥያቄዎች መልስ አይሠጥም:: ፕሮግራሙ መንግስት ሥልጣን ለመጨበጥ ለሚደረገው ትግል የሚረባ ባይሆን፣ አንድ የመንግስት ሥልጣን ጨብጦ ራሱን ለሚያደላድል ገዢ ከበርቴ መንግስት የተበፋ ይመስላል:: በኛ ግምት የአንድ ኮሚኒስት ፓርቲ ዘቀተኛ ፕሮግራም፣ ማለትም የዲሞክራቲክ ፕሮግራም፣ ለጠቅላላ የዲሞክራቲክ አብዮት የትግል ደረጃ፣ ማለትም ሥልጣን ከመጨበጡ በፊትና በኋላ፣ ለጠቅላላው ትግል ዘመን ብቁና የሚበጅ መሆን አለበት:: በዚሁ ትግል ደረጃ ለሚነሡት ጥያቄዎች መልስ መስጠትና የሚፈቱበትንም የትግል አቀጣጫዎች መጠቆም ይኖርበታል:: የኢ.ሕ.አ.ፓ ፕሮግራም ደግሞ ይህን አያደርገም:: የሚለውም እኛ የምንፈልገው "ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግስት" እንዲቋም ታገሉልንና ከዛ በኋላ የምትፈልጉትን እናደርግላችኋለን፣ ገበሬውንም እናስታጥቃለን፣ ለወዘ አደሩም የስምንት ሰዓት ሥራ ገደብ እናደርግለታለን የብሔርን ጥያቄ እንፈታለን ወዘተ.. እነ ፖለቲካ ሥልጣን ላይ ስወጣ፣ ወይም ስወጡኝና የፈለጋችሁትን አደርግላችኋለሁኝ የማይል አወናባጅ የት አለና? እውነተኛ ተራማጆች ግን የሚያደርጉት ባሁኑ ወቅት በሚካሄዱት አብዮታዊ ትግሎች እየተካተፉ፣ እነዚሁን ትግሎች ወደፊት እየገፉና እያፋፋሙ፣ ሰፊው ሕዝብ በእዲሱ ዲሞክራቲክ አብዮት ጎዳና ተራምዶ መሰናቶችን ደምስሶ፣ የፖለቲካ ሥልጣን እንዲጨብጥ መታገል ነው::

## አድርባዮችና የመሬት ጥያቄ

በቲዎሪ ደረጃ ብቻ ሳይሆን በገቢርም የኢትዮጵያ ዲሞክራቲክ አብዮት መሀከለኛ ጥያቄ፣ ፓወሰኛ ወይም ቁልፍ የመሬት ጥያቄ ነው:: የመሬት ጥያቄው አፈታት ዘዴ፣ ማለትም በአፈር ገፊውና በጉልተኛው መሀል የሚካሄደው የመደብ ጦርነት የዲሞክራቲኩ አብዮት ይዘትና ውጤት ይወስናል:: ባጭሩ የዲሞክራቲኩ አብዮት ሚዛን ነው:: ለዚህም ነው ተራማጆች ይህን ጥያቄ በሚገባ አጢነው፣ አብዮታዊ ታክቲክ በመቀየስ፣ ሽሁን ወቅት ኢትዮጵያ ውስጥ በገጠር የሚካሄደውን አብዮታዊ እንቅስቃሴ በተባባ አቧቧን ገቡን እንዲመታ መታገል ያለባቸው ለኢትዮጵያ አብዮት ቆመናል የሚሉትም ሀይሎች ተራማጅነት የሚመጠነው፣ የሚገመተው በዚሁ ጥያቄ ላይ በሚወስዱት አቋም፣ ከገበሬው እንቅስቃሴ ጋር ባላቸው ግንኙነት ነው::

ስለሆነም በዚሁ ጥያቄ ላይ የኢ.ሕ.አ.ፓ አቋም መመልከቱ ይበጃል:: ስለዚሁ ጥያቄ ፕሮግራሙ ሲያነሳ፣ ባገሪቷ ኢትዮጵያ ውስጥ በብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ ኢኮኖሚ እንገነባለን ካለ በኋላ፣

'የገጠርን መሬት ይዞታ፣ የእርሻ ይዞታንና ለማቀን በሚመለከት ረገድ መሬት በሙሉ የሕዝብ፣ የገጠር መሬት በድሃና በመለስተኛ አርሶ አደሮች መሬትነት በገቢር ወደ ሰፊው ሕዝብ እጅ እንዲገባ ማድረግና ወደ ቀድሞ ባለገበሬቶች እንዳይመለስ...' / ገጽ 9–10 / እንታገላለን ይላል

ወደ መተቸቱ ከመሄዳችን በፊት 'መሬት የሕዝብ ማድረግ' የሚለውን አባባል ትርጉም እንመርምር:: ምን ማለት ነው? በሌኒን አባባል 'መሬት የሕዝብን / **nationalization**/ድረግ' ማለት እንደሚከተለው ነው::

"... nationalization implies that all property rights in land are vested in the state, which the right of disposal of the land is vested in the local democratic institutions." (Coll. Works, Vol. 24, p. 478)

መሬት ናሽናላይዜሽን እንግዲህ ሁለት ነጥቦች አሉት ማለት ነው::

ሀ/ የመሬት ባለቤትነት የመንግስት መሆን

ለ/ መሬቱ በአካባቢ / ቀበሌ፣ ወረዳ፣ አውራጃ / ዲሞክራቲክ ባለሥልጣናት ቁጥጥር ስር መግባት::

ለነጥብ ሀ፣ መሬትን ባለቤትነት የመንግስት ለማድረግ፣ የመሬት ሺያጭና ግዢ የሚከለከል፣ መሬት የመንግስት ንብረት መሆኑን የሚያበስር ሕግ ይበቃል:: ከዚህ የበለጠ የሚያስፈልገው የገር የለም:: ደርጉም ይህን እርምጃ ወስዷል:: ባሁኑ ወቅት ባጠቃላይ ለመናገር ኢትዮጵያ ውስጥ መሬት የሚሸጥ ሰው ሊኖር አይችልም፣ መሬትም የሚገዛ ከቶ አይገኝም::



በጣም የሚያስቸግረውና አቢይ የመደብ ትግል የሚጠይቀው፣ ድሮ የነርሱ ከነበረው አሁን ግን የመንግስት ከሆነው መሬት ጉልተኞችን አባርሮ፣ መሬቱን በዲሞክራቲክ ድርጅቶችና ባለሥልጣናት / **institutions** / ቁጥጥር ሥር ማስገባቱ ማለትም ነጥብ 'ለ'ን ሥራ ላይ ማዋሉን ነው:: ይህ ተግባር ኢትዮጵያ ውስጥ ገና ፍጻሜው ላይ አልደረሰም፣ ወደፊት የአያሌ ዓመታት የመረረ መደብ ትግል ሳይጠይቅም አይቀርም:: እንግዲህ በኢትዮጵያ ውስጥ መሬትን የሕዝብ የሚያደርገውን የደርጉን አዋጅ ያየን እንደሆነ ላይ የጠቀስነው ነጥብ ሀ/ በሙሉ ኀይል ሥራ ላይ ቢውል፣ ለነጥብ ለ/ ትግል ገና እየተደረገለት ነው::

ይህ ሁሉ እውቅ ሆኖ ሳለ፣ የኢ.ሕ.አ.ፓ የኢትዮጵያ አብዮታዊ ገበሬ ለመሬቱና ለነጻነቱ እንዳልታገለ፣ ደሙን እንዳላፈሰሰ፣ በዚሁም ትግሉ ዓቢይ ድሎች እንዳልተጎናጸፈ እስካሁን ድረስ ምንም እንዳልተደረገ በመቁጠር፣ ወደፊት መሬት የሕዝብ ለማድረግ ማቀዱን ያበስርልናል:: በውነትም የተደረገውን እንዳልተደረገ፣ የታሪክን ጎማ ወደ ኋላ ለመመለስ የሚሞክር፣ በሕዝቦች ትግል የሚያላግጥ አድሀሪ ነው:: ኢትዮጵያ ውስጥ በመካሄድ ላይ ያለው አብዮታዊ እንቅስቃሴ ተራማጆች የሚናገሩት አቋም 'ጊዜያዊ መንግስት ከቆመ በኋላ ይህን ያደርግለታል' የሚለው ጠፍ አባባል ሳይሆን፣ ይህ እንቅስቃሴ ድል እንዲመታ ዘንድ፣ ገበሬዉ እንዲታጠቅ፣ የወዝ አደሩ የገበሬው አንድነት እንዲፈጠር፣ በተለይ በገጠር ያለው ፖሊሱና ቢሮክራሲ፣ እንዲደመሰሱ መታገሉ ነው:: በዚሁ አንጻር በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች 15ኛው ጉባዔ ስለታወጀው መሬት አዋጅ ያስተላለፈውን ውሳኔ መመልከቱ ይጠቅማል::

'ይህ አዋጅ በሚገባ ሥራ ላይ ሊውል የሚችለው አርሶ አደሩ ተደራጅቶ በመሳሪያ ትግል የጉልተኛውን መደብና የርሱን መንግሥት አውታሮች ሲደመስስ ማለትም የገጠር አብዮት ሲያካሄድ ብቻ ነው:: አዋጁን በገቢር ለመመንዘር የጉልተኞችን የፖለቲካ ሥልጣን ቀሽም በአብዮታዊ አመጽ መስበር ያስፈልጋል:: የገጠር አብዮት ለፖለቲካ ሥልጣንና ነጻነት ከሚደረገው ትግል ጋር ሊነጣጠል አይችልም:: ማለትም ከጠቅላላው ዲሞክራቲክ አብዮት ተገንጥሎ ሊታይና ሊካሄድ አይችልም::

ስለዚህም የመሬት አዋጅ አብዮታዊ ይዘቱ ተጠብቆ ሥራ እንዲውል ማኅበራችን

ሀ/ የገበሬ ማኅበራት በዲሞክራሲ መሠረት ከጉልተኞችና ቢሮክራሲው እንዲሁም ከደርጉ ተጽእኖ ፍጹም ነጻ በሆነ መንገድ እንዲደራጁ ይታገላል::

ለ/ የገበሬ ማኅበራት በአዋጁ ከተመጠነላቸው የተግባራት ዝርዝር አልፈው በተቀዳሚ ደረጃ ባለበት አካባቢ የመንግስት ሥልጣን ተሸካሚና የሕዝቡ አስተዳደር መሳሪያዎች እንዲሆኑ ይታገላሉ:: የተቀደሞ ሥርዓት አውታሮች በተለይ ፖሊስና ፍርድ ቤቶች ፈርሰው የፀጥታ ጥበቃ፣ የፍርድ ወዘተ.. ባጠቃላይ የአስተዳደር ጉዳይ የሚመለከቱ ተግባሮች ሁሉ በአብዮታዊ አፈር ገፊ ኮሚቴዎች እንዲካሄዱ ይታገላል::

ሐ/ ሰፊው አፈር ገፊ ሕዝብ በሙሉ እንዲታጠቅ ይጠይቃል፣ ይታገላልም::

የገጠር አብዮት በሚገባ ከፍጻሜው ሊደርስ የሚችለው በወዝ አደሩና በአፈር ገፊው ትብብር የተመሠረተ የገጠሬውና የከተሜው የትግል አንድነት ገንባር ሲፈጠር ነው' ገጸ 27, ትግሳችን ዜና ገጸ 3, ቁጥር 1

በኛ አስተሳሰብ የመሬትን አዋጅ ሥራ ለማዋል የሚደረገው ትግል፣ ማለትም የገጠር አብዮቱና፣ ሕዝቡ የፖለቲካ ሥልጣን ለመጨበጥ የማያደርገው ትግል በጣሙን የተያያዙና የተቆላለፉ፣ ሊነጣጠሉ የማይችሉ አንድነት ናቸው:: የገጠር አብዮት እስካልተደረገ ድረስ ሕዝቡ የፖለቲካ ሥልጣን ሊጨብጥ አይችልም፣ የፖለቲካ ሥልጣንም እስካልጨበጠ ድረስ የገጠር አብዮትን ወደ ፍጻሜው ሊያደርሰው አይችልም:: ለፖለቲካ ሥልጣን የሚደረገውን ትግል ዘንግቶ፣ በመሬትአዋጅ ሥራ ላይ መዋሉ ብቻ ማተኮሩ ፍጹም ሪፎርሚዝም፣ አድርባይነት ነው:: በሌላ በኩል እንደ የኢ.ሕ.አ.ፓ 'የጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግስት' ከቆመ በኋላ የመሬት ጥያቄ ይፈታል የሚለው አባባል ደግሞ ሺ ጊዜ ተራማጅ ይመስል፣ ባሁኑ ወቅት ጉልተኞች ጠቀም አቋም ነው::

እዚህ ላይ የፕሮግራሙን ትንተና አቋርጠን፣ የኢ.ሕ.አ.ፓ በገቢር በመሬት ጥያቄ ላይ የወሰዳቸውን አቋሞች መመልከቱ ባይበጅ አይቀርም:: ምክንያቱም የኢ.ሕ.አ.ፓ እውነተኛ አቋም ለማወቅ ከፈለግን በፕሮግራሙ ውስጥ የተለቀለቀውን ብቻ ሳይሆን፣ በገቢር፣ በቀን ተቀን ትግሉ የሚወስዳቸውን እርምጃዎችን መመልከት ያስፈልጋል:: የሁሉም መፈተኛ ድርጊት ነውና:: ከዚህ አንጻር ስንመለከተው፣ የኢ.ሕ.አ.ፓ ስያች በመሬት ጥያቄ ላይ ቢያነስ፣ ቢያንስ ሦስት የተለያዩ አቋሞች እንደወሰዱ ለማየት ይቻላል:: የመጀመሪያው አቋም የሚገለጸው፣ የኢ.ሕ.አ.ፓ አንደኛው ልሳን በሆነው በ 'በዲሞክራሲያ' አማካኝነት የደርጉ መሬት አዋጅ እንደወጣ፣ አዋጁን በመደገፍ በተወሰደው እርምጃ ነው:: የዘረጋን አያድርገውና፣ ያኔ፣ የደርጉን መሬት አዋጅ እሰለ ብለው ከተቀበሉት፣ እንደ የሕዝቡ ትግል አበይ ፍሬ ከቆጠሩትና ሥራ ላይም እንዲውል ከታገሉለት ሀይሎች መሀል 'ዲሞክራሲያም' ነበረበት:: በዚያን ወቅት 'ዲሞክራሲያ' የጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግስት ጥያቄ ማንሣቱን ትቶ እንደነበረ ማስታወሱ ይጠቅማል:: ሁለተኛው የኢ.ሕ.አ.ፓ ስያች አቋም ያው በፕሮግራሙ እንደተገለጸውም፣ 'ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግስት' ከቆመ ወዲያ፣ የመሬት ጥያቄ እንፈታለን የሚለው እጉል አባባል ነው:: ይህ አቋም መቼም አሁን ኢትዮጵያ ውስጥ በገጠር በሚካሄደው አብዮታዊ ትግል ተበልጦ መቀረጥን፣ ከትግሉ መሸሸን ያመለክታል:: ሦስተኛው አቋም ደግሞ 'በሳብ አደር' ቁጥር 16 የተገለጸ ሲሆን፣ የሚለውም የሶሺያሊስት መንግስት እስካልመጣ ድረስ ከባላባት መሬት 'መንጠቅ' ለሕዝቡ ምንም ጥቅም አይሠጥም ነው:: ይህ አባባል ተራማጅ ይመስል እንጂ ፍጹም አድሀሪ ነው:: የሚከው በሶሺያሊስት አብዮት እንጂ በአዲሱ ዲሞክራቲክ አብዮት ውስጥ የመሬት ጥያቄውን ለመፍታት አይቻልም ነው:: ማለትም ባሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ አርሶ አደር የሚያካሄደው አብዮታዊ ትግል ፋይዳ የለውም፣



ከባላባቱ መሬት መንጠቅ ጥቅም የለውም:: ከባላባት መሬት መንጠቅ የሚጠቀመው ምናልባት የዘረ ሃያ፣ ሠላሳ አርባ ወዘተ.. ዓመት ኢትዮጵያ ውስጥ የሶሺያሊስት መንግስት ሲቋቋም ነው::' ተራማጅ' መስሉ ለፊውዳ ፋሺስቶችም መከራከር እንዲሁም የለ!

ከዚህ ለጥቆ ስሞኑን የኢ.ሕ.አ.ፓ ዘማቶች ከየጣቢያቸው እንዲመለሱ ለማድረግ የሚያካሄደው ፀረ አብዮታዊ ዘመቻ አለ:: የዚሁ ጥረት ዋና ይዘት ገበሬውንና ዘማቾችን ለመነጣጠል፣ ገበሬውን አጋፍጦ ለጉልተኞች አሳልፍ ለመስጠት፣ ዘማቾች ከአብዮት መስኩ እንዲወገዱ ለማድረግ ነው:: ባሁኑ ወቅት የገበሬ ማኅበራት ሀይል የሚመሠረተው በአርሶ አደሩና ዘማቾች አንድነት እንደሆነ እውቅ ሆኖ ሳለ፣ ዘማቾች ይመለሱ ማለቱ ለምን ይሆን? ማንስ ይጠቀምበታል? ምሁርና ሰፊው ሕዝብ እንዳይገናኙ፣ እንዳያዋሁዱ የሚፍጨረጨሩት ጉልተኞች፣ ቢሮክራሲውንና የደርጉ ቀኝ ክንፍ አይደሉምን? የገበሬውንና የዘማቾችን አንድነት ለማፈራረስ በሚደረገው ከፍተኛ ፀረ አብዮት ዘመቻ የኢ.ሕ.አ.ፓ በጉልተኞች፣ ኢምፔርያሊስቶችና በደርጉ ውስጥ ካሉት ቀኝ ሀይሎች ጋር በአንድነት ይሰለፋል:: ባሁኑ ወቅት የተራማጆች ተግባር ዘማቶች ከጣቢያቸው እንዲመለሱ መቀስቀስ ሳይሆን፣ የበለጠውን ከአርሶ አደሩ ጋር እንዲዋሀዱ፣ ከገበሬው ጋር ባንድነት ሆነው ለዲሞክራቲክ መብቶች እንዲታገሉ፣ የደርጉ ተጸዕኖ እንዲነሣላቸው የተወበጣጠረውን ትግላቸውን በበሔር አቀፍ ደረጃ እንዲያደራጁ፣ ወዘተ.. መታገልና መቀስቀስ ነው:: በዚሁ አኳያ አብዮታዊያን ዘማቾች 'ከዘማች ለዘማች' በምትለዋ በራሪ ወረቀት የወሰዱት አቋምና ያቀረቧቸው ጥያቄዎች ሙሉ በሙሉ የሚደገፉ ናቸው::

በተረፈ እዚህ ላይ መጠቀስና ፈጽሞ መታለፍ የማይቻለው ነገር ቢኖር በውጭ አገር የኢ.ሕ.አ.ፓ 'አምባሳደሮች' የሆኑት የኢዜና / ዓለም አቀፍ ተማሪዎች ፌዴሬሽን መሪዎች የሆኑት 'መሬት ሳራሹ' የሚለውን አብዮታዊ መፈክር በመቃወም 'ገበሬው መሬት ካገኘ ፋሺስት ይሆናል' ወይም 'በአዋጁ / በደርጉ/ በጣም የተደበለ መደብ ደሀው ገበሬ ነው:'/ ታገል ግርቻ 1975 ገጸ 29/ በማለት የሚነዙት ፀረ አብዮት ፕሮፓጋንዳ ነው:: የኢ.ሕ.አ.ፓ ከነዚሁ ፀረ አብዮታዊ በውነት ፋሽስታዊ ሃይሎች ጋር እስከተባበረ ድረስ፣ በተመለካቹ ዘንድ የኢ.ሕ.አ.ፓ 'መሬት ሳራሹ ' የሚለውን መፈክር መቀበሉን በጣም ይጠፈጥራል::

የኢ.ሕ.አ.ፓ ፕሮግራም ወደ መተቸቱ እንመለስ። ከፍ ብለን ከኢ.ሕ.አ.ፓ ፕሮግራም በወሰድነው ጥቀስ ለማየት እንደቻልነው፣ 'ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግስት' መሬት የሕዝብ ያደርጋል / **nationalize** / ካለ በኋላ ተገሸ ወረድ ብሉ የሚከተለውን የምሥራች ይቸረናል::

'ሶስት ዓይነት የመሬት ይዞታ ሥርዓቶች ይኖራሉ:: ይኸውም፣በግለ ሰብ በሕብረትና በሕብረተ ሰብ የሚታረስ ብሉ ይጠራል' / የኢ.ሕ.ፓ ፕሮግራም ገጸ 10/

በአንገለዘና በወጣው ፕሮግራም ደግሞ
"A. On Utilization of land: There shall be three types of land ownership -- private individual ownership, cooperative forms of ownership, and state ownership which in turn give rise to private farms, cooperative farms and state farms." (EPRP's programme p.6)

ባገሬ በኩል መሬት የሕዝብ ማለትም የመንግስት ንብረት ይሆናል ይባልና፣ ተገሽ ወረዶ ብሎ ደግሞ በተዓምር ሦስት ዓይነት የመሬት ይዞታዎች /three types of landownership/ይወጡታል። እኛም በጠማሪ ሌለኛ ቀ የሠበቱ ሥሳቢያች ቀቅባይ ምሥጢር ባትሆን አትቀርም።

መቼም ሎጂክ በተከተለ መንገዱ ሳስበ መሬት የሕዝብ ከሆነ፣ ናሽናሳይዝዶ ወይም ንብረትነቱ የመንግስት ከሆነ፣ የመሬት ይዞታ ጥያቄ ፍጹም ሊነሣ እንደ ማይችል እንደቀን ብርሃን ገልጸ ነው። ባገሬ በኩል ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ጠቅላላ መሬት የመንግስት ነው ከተባለ፣በሌለኛው አፉ ደግሞ የግል መሬት ንብረት / private landownership / የሕብረት መሬት ንብረት/ collective landownership / እና የሕብረተ ሰብ መሬት ንብረት / state landownership / ይኖራል ብሎ መናገሩ፣ የፖለቲካ ደደብነት ማጋለጥ፣ የሉጂክ ድህነትን ማስመስከር ነው።

እንዲሁም ይህ አባባል ፀረ አብዮታዊ ይዘት አለው። ባሁኑ ወቀት ደርጉ መሬት የሕዝብ አደርጋለሁኝ የሚል አዋጅ ካወጣ ወደሀ፣ የግል መሬት ንብረትነት አስመልሳለሁኝ ብሉ ፕሮግራም ውስጥ ማስቀመጥ / የኢ.ሕ.አ.ፓ በዚሁ ጥያቄ ያለው አቋም ደግሞ ሌላ ፍቺ ሊኖረው አይችልም/ የኢትዮጵያ አርሶ በሉ የሚያደርገውን አብዮታዊ እንቅስቃሴ ወደኋላ ለመቀልበስ እንደሚሞክር ይቀጠራል። ባሁኑ ወቀት ሕዝቡ መሬት የሕዝብ ይሁን እያለ በሚታገለበት ጊዜ፣ <u>የግልም</u> መሬት እንዲኖር እታገላለሁኝ ማለት፣ ወደ ዝቀተኛ የትግል ደረጃ መውረድ፣ ለቸግሉ እንቅፋት መሆንና፣ ጉልተኞችን መርዳት ማለት ነው። የኢትዮጵያ አርሶ አደር በመሬት የግል ንብረትነት ለማጥፋት በሚያደርገው አብዮታዊ ትግል /ሌኒን እንደሚያስተምረውም ናሽናላይዜሽን የነቃውና የአብዮታዊ ገበሬ ጥያቄ ነው/ አብሮት ከመሰለፍና የአርሱንም ትግል ከመምራት ይልቅ፣ የኢ.ሕ.አ.ፓ ፕሮግራም ንዑስ ከበርቴው ያለውን የግል ንብረት ፍላጎት ለማርካት የተነደፈ ይመስላል።

የኢ.ሕ.አ.ፓ ላይ በጠቀስነው ማጥ ውስጥ የገባው <u>በመሬት ይዞታና</u>፣ በአስተራረስ ዘይቤ መሀል ያለውን ትልቅ ልዩነት ባለመረዳቱም ነው። መሬት የሕዝብ መሆን ኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን የመሬት ይዞታ ጥያቄ ቢፈታው፣ አርሶ አደሮች በምን ዓይነት፣ ዘይቤ መሬትን ይረሱት የሚለውን ጥያቄ አይመልስም። አርሶ አደሮች መሬትን በግል ወይም በሕብረት ይረሱት የሚለው ጥያቄ የሚወሰነው በአርባታ ሀይሎች በተዩም በጎንበስና ቴክኖሎጂ እድገት፣ በአርሶ አደሩ ፖለቲካ ንቃት ደረጃ ወዘተ.. ነው። እነዚሁን ሁለት ነጥቦች በማማታቱ የኢ.ሕ.አ.ፓ ፕሮግራም ከፍተኛ ውዥንብር ውስጥ ይዋኟታል፣ በይዘቱም አድሀሪያንና ጉልተኞችን የሚጠቅም አቋም ያስወስደዋል።



ባጠቃላዩ ለማመዛዘን የኢ.ሕ.አ.ፓ ፕሮግራም በመሬት ጥያቄ ላይ ያለው አቋም፣ 'ኮሚኒስት ነን' ከሚለድርጅት የማይቀርብ፣ እንዲያውም በብዙ አፉ ከደርጉ የመሬት አዋጅ ወደኋላ የቀረ ነው። ባሁኑ የኢትዮጵያ ሕልውና የገጠር ትግሉን ወደፊት የሚያራምዱ ሳይሆን፣ እንዲያውም ምናልባት ለቀለበሽ ሀይሎች ምሚያመች ሳይሆን አይቀርም።

<u>ስለጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግስት ጥያቄ</u>

የጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት ጥያቄ በአውርባይ ንዑስ ከበርቴያችና በተወናበዱ 'ተራማጆች' ከተነሣበት ወቀት ጀምሮ በኢትዮጵያ ገራ ውስጥ ከፍተኛ ውዥንብር ፈጥሯል። ሕዝቡ ሳይደራጅና ሳይታጠቅ፣ እንዲሁም የኢትዮጵያ ሕዝቦች ጠላቶች የሆኑት ፊውዳሊዝም፣ኢምፔሪያሊዝምና የቢሮው ከበርቴ መደብ ሳይደመሰሱ 'ሕዝቡ' የፖለቲካ ሥልጣን መጨበጥ እንደሚቻል በማስመሰሉ፣ ለዘሳቂው ትግልና ድል የሚደረገውን ዝግጅት በማደናቀፍ የኢትዮጵያ ሕዝቦች ጠላቶችን የጠቀመ መፈክር ነው። ይህን ለማሳየት የጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት መፈክርን የሚያነሱትን ሕብረተ ሰባዊ ክፍሎች መጠቆም ይበቃል። በተቀዳሚ ደረጃ 'የጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግስት' ይቋቋም የሚሉት እነ አስፋው ጋሰን ሀይለ ስላሴ፣ / 31/75 መግለጫውን ተመልከት/ ፋሺስቶች፣ ፊውዳሎቶች፣ እና ቢሮ ከበርቴያች የተጠራቀሙበት የኢትዮጵያ ዲሞክራቲክ ማህበር /Ethiopian Democratic Union / የተባለው ፀረ አብዮታዊ ድርጅት፣ ወዘተ ናቸው። የኢ.ሕ.አ.ፓ ምናልባት የዚህ አድሀሪ ስብስብ ገራ ጥግ ቢይዝ ነው። እነዚሁ አድሀሪያች 'ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግስት' ይቋቋም የሚሉት ጥቅማቸውን ስለሚጠብቅ፣ መሳሽ ሤራቸውን ስለሚያመቻችላቸው ካልሆነ በስተቀር ሌላ ምክንያት ፈጽሞ ሊኖራቸው አይችልም።

ባሁኑ ወቀት ሁለት ፀይነት ፀር ደርገባት አለ። ከቅኝና ከገራ፣ ከድሮው ሥርዓት ተጠቃሚያችና ከሰፊው ሕዝብ። ሰፊው ሕዝብ ደርጉን ከገራ ሆና በተራማጅነቱ ሳይሆን በፀረ ዲሞክራቲክነቱ፣ በሚወስዳቸው ፀረ ሕዝብና ፀረ አብዮት እርምጃዎች ይታገለዋል። የኢ.ሕ.አ.ፓ ፀረ ደርግነት ግን 'ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግስት በምትለዋ መፈክር አማካኝነት ከቀኝ ሀይሎች፣ ከፊውዳሎቶች፣ ከኢምፔሪያሊስቶችና ከእውነተኛ ፋሺስቶች ጋር አብሮ የሚያሰለፈው ነው።

ለሰፊው ሕዝብ የቆሙ ተራማጆች ግን እውነተኛ ሕዝባዊ መንግስት የሚመጣበትን መንገዱና የዚሁ መንግስት መደብ ይዘት ጠንቅቀው ያውቃሉ። የሚታገሉት ከጉልተኞች ጋር አብሮ ለሚያሰልፋቸው ተመራጭ 'ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግስት' ሳይሆን፣ በአዲሱ ዲሞክራቲክ አብዮት ነዳና፣ ኢምፔሪያሊዝም፣ ፊውዳሊዝምና ቢሮክራሲ በአብዮታዊ አመጽ ተደምስሰው፣ በነርሱ መቃብር ለሚመሠረተው የመደብ ይዘቱ የወዝ አደሩና የአርሶ አደሩ ዲሞክራቲክ ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ ለሆነው ሕዝባዊ መንግስት ነው። ይህ ዓይነቱ እውነተኛ ሕዝባዊ መንግስት፣ ጉልተኞችና ኢምፔሪያሊስቶች፣ የሚታገሉት እንጂ እንደ ተመራጭ 'ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግስት' የሚታገሉለት አይደለም።

በማርክሲስት ሌኒኒስት ቲዎሪ አንጻር ሰፊው ሕዝብ ፖለቲካ ሥልጣን ሊጨብጥ የሚችለው ለገዢዎቹ በሉ ከሥልጣን ክርቻ ውረዱልንና፤ እኛም በተራችን ተመራርጠን እንፈናጠጥበት በማለት አይደለም:: አንድ ሕዝብ ነጻ እንዲወጣና፤ የራሱን ነጻ መንግሥት ለመመሥረት ከፈለገ የሚጨቁነውን ሠንሠለት አስቀድሞ መበጣጠስ አለበት:: ምናልባት ራሱን በማታለል፤ ጠፍሮ ያሠረውን ሰንሰለት በቅዠት ዓለም የለም ብለን ካልቀረጥን፤ በባርነታችን አርነት የሚሠማን ካልሆነ በስተቀር ሌላ ነጻ ሊወጣ የሚችልበት መንገድ የለም:: የኢትዮጵያ ሕዝቦችም በእርግጥ ነጻ ለመውጣት የሚችሉት ጨቋኙ የያዟቸውን የኢምፔርያሊስትና የፊውዳሊስት ሰንሰለቶች በጣጥሰው አሽቀንጥረው ሲጥሏቸው ብቻ ነው:: ነጻነት ያለ ተደራጀ ጦር ትግል፤ ነጻነት ያለ አብዮት አይገኝም::

'ፖለቲካ ሥልጣን ከጠበመንጃ አፈ ሙዝ ይፈልቃል' ይላሉ ሊቀ መንበር ማኦ ቤ ተንግ:: ይህ ለኢትዮጵያም የሚበጅ ሀቅ ነው:: ለምሳሌ ደርጉ የፖለቲካ ሥልጣን ለመጨበጥ የበቃው የተደራጀና የታጠቀ ሃይል ሆኖ በመገኘቱ ነበር:: የኢትዮጵያ ሕዝብም የፖለቲካ ሥልጣን ለመጨበጥ የሚችለውም ተደራጅቶና ታጥቆ ጠላቶቹን ማለትም ኢምፔርያሊዝምን፤ ጉልተኛውን ሥርዓት ቢሮክራሲውን ሲደመስስ ብቻ ነው:: ይህ እስካልሆነ ድረስ፤ የሰፊው ሕዝብ ድምፅ እንደሚለው፤ የኢትዮጵያ ሕዝቦች ሚሊዮን ጊዜ 'መንግስታቸውን' ይምረጡ፤ የሚቆመው መንግሥት እነርሱን የሚረግጥ እንጂ የሚወክል አይሆንም:: ይህ ደግሞ ያልገባው ስለ ማርክሲዝም ሌኒኒዝም አንዳች ቅንጣትም አያውቅም::

'የጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግስት' ጥያቄና በዚሁ ጥያቄ የዲሞክራሲያ /የኢ.ሕ.አ.ፓ ልሳን/ አቋም ራሱን የቻለ ታሪክ ነው:: ይህን ታሪክ ለማሳጠር አጼ ሀይለ ሥላሴ ከአልጋው እንደፈረጠ፤ 'የጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት' ጥያቄ የዲሞክራሲያ ዋና ጥያቄ ነበር:: የመሬት አዋጁ በወጣበት ሰሞንና ከዚያም በኋላ ለጥቂት ጊዜ ፈጽሞ እንዳልተነሣ መፈክር ድምጽ ጠፋ:: ለጥቆም 'እንደገበያው ሁኔታ' ብቅ ጥፍት የሚል ሸቀጥ ሆኖ መጥቶ፤ የኢ.ሕ.አ.ፓ ፕሮግራም ከተበተነ ወዲህ ጀርባ በማደንቀር ሳይገኛል:: አንድ ተራማጅ ነኝ የሚልና የዚሁም ሀላፊነት የሚሰማው ድርጅት እንዳሻው፤ መፈክር ሲያነሣና ሊጥል አይችልም:: በሁኔታው መቀየር የተነሣ መፈክር እንዲቀይር ቢገደድም፤ ለሰፊው ሕዝብ ይህ መፈክር ለምን መቀየር እንዳለበት፤ አዲሱ መፈክርና የትግል አቅጣጫ ለሕዝቡ ማሳየትና በዚሁ አዲስ መፈክር ሥር ሕዝቡን ለማሰለፍ መታገል አለበት:: እንደመጣለት ግን መፈክር ማንሣትና መተው፤ ይህ ያዙኝ ልቀቁኝ የልጅ ጨዋታ እንጂ የአንድ አብዮታዊ ፓርቲ ታክቲክ መሠረት ሊሆን አይችልም::

## <u>የብሔር ጥያቄና የሸቪኒስቶች አቋም</u>

ኢትዮጵያ የብሔር ጭቆና የነገሠባት፤ ብሔሮች የሚማቀቁበት ወህኒ ቤት ናት:: ከ60 የማያንሱ የተጨቆኑ ብሔሮች ይገኙበታል:: እነዚሁ ጭቁን ብሔሮች በተለያዩ



ደረጃዎች፤ አቅጣጫዎችና መጠኖች ብሔራዊ መብቶቻቸው ተገፈው፤ እንደሁለተኛ ደረጃ ዜጎች በመቆጠር ከፍተኛ ሶሺያል፤ ፖለቲካልና ኢኮኖሚ ጭቆና ሲካሄድባቸው ቆይተዋል:: 'ጭቆና ባለበት ተቃውሞ እንደሚኖረው' ሁሉ የሚጫነባቸውን ድርብ ጭቆና ለመቋቋም የኢትዮጵያ ጭቁን ብሔሮች አያሌ ትግሎች አካሂደዋል:: በተለይም የኤርትራ ሕዝቦች ይህን ትግላቸውን በመግፋት፤ የሚወርዱባቸውን የቦምብና የጥይት ናዳ በመቋቋም፤ ከፍተኛ ደረጃ ላይ አድርሰውት ይገኛሉ::

በዚሁ የዲሞክራቲክ አብዮት አንዱ አካል በሆነው የብሔር ጥያቄ ላይ በፕሮግራሙ እንደተለጸው የኢ.ሕ.አ.ፓ የወሰደው አቋም ፀር ማርክሲስት ሌኒኒስት፤ ትምክህትነት የሚያበረታታ የለዘብተኛው ከበርቴ / liberal bourgeoisie / አቋም ሆኖ እናገኘዋለን:: ይህን ወደ ማሳየት እናምራና በሚከተለው ጥቅስ እንጀምር::

'ብሔሮች የራሳቸውን እድል በራሳቸው ለመወሰን ያላቸውን ገደብ የማይደረግበት መብት ያውቃል፤ ከሥራም ላይ ይውላል::' / የኢ.ሕ.አ.ፓ ፕሮግራም ገጽ 16/

በመጀመሪያ ነገር ኢትዮጵያ ውስጥ ላሉት ለተጨቆኑት ብሔሮች የራሳቸውን ዕድል በራሳቸው የመወሰን <u>መብት</u> ከሰማይ እንደገጸበረከት የሚሠጣቸው፤ የሚታደሉት ነገር አይደለም:: እነፊውዳሎች በአዋጅ የምንገዛት ካልሆነ በስተቀር፤ እኛ ተራማጆች የምንታገለው ለጭቁን ብሔሮች መብታቸው <u>እንዲታደሉቸው</u> ሳይሆን፤ የብሔራዊ መብቶቻቸው በገቢር እንዲታወቅላቸው ነው:: ይህ የቋንቋ ልዩነትም ብቻ ሳይሆን በዚሁ ጥያቄ አፈታት ያሉትን የተለያዩ ግምቶችን ያመለክታል:: እንዲሁም ጥቅሱን ልብ ብሎ ለተመለከተው የተሳሳተና ፀረ ጭቁን ብሔሮች መሆኑን በቀላሉ ሊረዳው ይችላል:: ምክንያቱም በዓረፍተ ነገሩ ውስጥ ለተጨቆኑ ብሔሮች የራሳቸውን ዕድል በራሳቸው የመወሰን መብት የሚያውጁላቸው መሆኑን ካበሠረለን በኋላ፤ በሚከተለው "ከሥራም ላይ ያውላል" በሚለው ሃረግ ይህን 'መብት'/ዓረፍተ ነገሩን ልብ ብሎ ለተመለከተ ሌላ ትርጉም የለውም/ እርሱ ራሱ ሥራ ላይ እንደሚያውለው ይናገራል:: ማለትም ለተጨቆኑት ብሔሮች የራሳቸውን ዕድል ያለገደብ የመወሰን መብት ታውጀላቸው /መብት ይበለውና/ ይህንንም መብት ሥራ ላይ የሚያውሉት <u>የተጨቆኑት ብሄሮች ባይሆኑ</u>፤ ሰጪው የኢ.ሕ.አ.ፓ <u>ሆኖ ቁጭ</u> ይላል:: አንድ መብት "ከታወጀ"/በኢ.ሕ.አ.ፓ ቋንቋ ለመናገር/ ይህን መብት ሥራ ላይ የሚያውሉት፤ የሚገለገሉበት የተጨቆኑት ብሄሮች ናቸው እንጂ 'ሰጪው' ራሱ መብቱን ሥራ ላይ አውላለሁኝ ካለ ከ'መብቱ' ምን እንደተረፈ የህብተ ሥላሴዎች ምሥጢር ሆና ትቀራለች:: ያም ሆነ ይህ ከዚህ ዓረፍተ ነገር ምርመራ ለማየት እንደሚቻለው የኢ.ሕ.አ.ፓ በብሔር ጥያቄ ላይ ያለው አቋም በአባታዊነት / paternalism / የተበከለ፤ በዚህም አንጻር ትምክህተኛነትን የሚያፀባርቅ ነው:: በአውሮፓ ሽር ጉድ የሚሉት የኢ.ሕ.አ.ፓ ግልገሎች ማለትም በፌዴሬሽን አካባቢ የተደራጁት የቋንቋ ጉድለት ይሉታል:: የማይመስል ዘባዝንኬ:: በየጊዜው በተለያዩ ጽሑፎቻቸው በ'ዲሞክራሲያ' 'ላብ አደር' ወዘተ በተባባ አማርኛ የሚጽፉ ሰዎች በዚህ አብይና አንገብጋቢ ጥያቄ 'አንዳጋጣሚ' ቋንቋው ይኮላሸባቸው! የተጋደለው ቋንቋው ሳይሆን የዲሞክራቲክ ስሜቱ ቀልቶና ዘለቄ የሚረብው ሾቪኒዝሙ ነው::

ወደሚቀጥለውና ወደ ዋናው የሂሳችን ነጥብ እንሸጋገር — ከላይ የተጠቀሰውን እንደገና በሰፊው እንመለከተው::

'ብሔሮች የራሳቸውን እድል በራሳቸው ለመወሰን ያላቸውን ገደብ የማይደረግበት መብት ያውቃል፣ በሥራም ላይ ያውላል::

1. የኢትዮጵያ ብሔሮችን ሕዝቦች ሁሉ የራሳቸውን እድል በራሳቸው ፈቃደ መዋህድ በተባለው መርሕ መሠረት የሚፈልጉትን ዓይነት የሕብረት መንገበት በእኩልነት በወንድማማችነት እንዲያደርጉ በሰላማዊ የፖለቲካ ትግል ያካሄዳል::'
/የኢ.ሕ.አ.ፓ ፕሮግራም ገጽ 16 /

በእንግሊዝኛ ትርጉም ደግሞ

"IV. To declare and safeguard the unrestricted Right of nations to self-determination.

1. a) To give full rights to the peoples' of the various Ethiopian nationalities to determine their own destiny, and at the same time carry out a peaceful struggle for a voluntary union of the type they choose on the basis of equality and the feeling of brotherhood" (EPRP programme, p. 13).

ባሁኑ ወቅት ኢትዮጵያ ውስጥ ማርክሲስቶች ብቻ ሳይሆኑ፣ ንዑስ ከበርቴዎችም፣ ከበርቴዎች ወዘተ::. የብሔር ጥያቄእንዳለና ይህም ጥያቄ መፈታት እንዳለበት ያምናሉ:: በመሰረታቸው ያለው ልዩነት ግን የብሔር ጥያቄ እንዴት ይፈታ በሚለው ነጥብ ላይ ነው::

ለምሳሌ የንዑስ ከበርቴ አድርባዮች ብሔሮች የራሳቸውን እድል በራሳቸው የመወሰን መብት እንዲያውቁ ቢገደዱም፣ ይህ የአገሪቷን አንድነት ሳይጻረር እንዲከናወን ይሻሉ:: እንደ ጦር የሚፈሩት ስለ መገንጠል መብት መናገር፣ የሚመርጡት ስለ 'አንድነት' ማውራት:: የሆነ ነገር ይምጣ፣ የተፈለገው ነገር ይነገር፣ መገንጠሉ ጉዳይ ብቻ አይነሣባቸው:: የኢ.ሕ.አ.ፓ ፕሮግራም ደግሞ እውነተኛ ኢንተርናሽናሊስቶችን ከሸቤኒስቶች የሚለየውን መገንጠል ጥያቄ አያነሣም:: 'ያለ ገደብ' / የብሄሮችን መብት ያውቃል፡ የሚለውን አሻሚ ሐረግ ወርውር አድርጎ፣ ወዲያውኑ ስለ 'ፈቃደ መዋህድ' / በእንግሊዝኛ voluntary union/ በማውራት ይገደግደዋል::

በማርክሲስት ሌኒኒስት ቲዎሪ መሠረት ስለ መገንጠል መብት ያልተናገረ፣ ለዚሁም በተግባር ደረጃ ቅስቀሳ ያላደረገ፣ ስለመዋሀድ ፈጽሞ ሊያወራ አይችልም:: እነዚሁ ጥምረ ተቃራኒያች / pair of contradictions / ማለት መገንጠልና አንድነት ሊነጣጠሉ የማይችሉ ሕብረት ናቸው:: የኢ.ሕ.አ.ፓ ፕሮግራም በግልጽ ስለ መዋሀድ፣ ስለ አንድነት / union / እንደተናገረው ሁሉ፣ ስለ መገንጠል መብት ማውሳት ነበረበት:: ሌኒን ስለ መገንጠል መብት ማግኘት አስፈላጊነትን ሲናገር::

"If in our political agitation, we fail to advance and advocate the slogan of the right to secession, we shall play into the hands, not only of the bourgeoisie, but also of the feudal lords and the absolutism of the oppressor nation." (Coll. Works, Vol. 2o, p. 413)



ሌኒን እንደሚለው የመገንጠል መብትን ካላነሣን የብሔር ጨቋኞች መሣሪያ፣ ከነርሱ ጋር የምንሰለፍ እንሆናለን ይላል:: ወደድነውም፣ ጠላነውም ልክ እንደነርሱ ተምክህተኞች ያደርገናል:: ስለዚሁም ጉዳይ የዛሬ ሦስት ዓመት 'ታጠቅ' ሲጽፍ የሚከተለውን ይላል::

'ኢትዮጵያ ማለት እኔ ብቻ ነኝ' ብሎ ካከተመው ተምክህተኛ ብሔራዊ ስሜት ለእንዲት ሲከንዴእንዷን ወርሳ ባለተቆራረጠ እንደበተ ለእንዲት ሲከንዴ እንዷን ባለተፍታታ ሀሳናው ማንም ቢሆን ስለአንድነት ለመስበክ መብት የለውም:: በዛሬው ወቅት አስቀድመን በፕሮፓጋንዳና በአጊቴሽን የመገንጠል መብት እንዲታወቅ ሳንታገል 'ለአንድነት' እንታገላለን ብንል ከነሃይለ ሥላሴ የምንለይበት ምንም ዓይነት ፈሊጥ የለም' ታጠቅ ቁጥር 1 1965

ለምንድር ነው ስለ መገንጠል መብት ማንሣት የሚያስፈልገው? ቀላል ምሳሌ በግፍ አንድ እሥር ቤት ለማቀቀ እሥረኛ በመጀመሪያ ደረጃ መታገል ያለበ ነጻነቱ፣ ከዚያ እሥር ቤት ለመውጣት መብቱ ነው:: እርግጥ እሥር ቤቱን አፍርሰን፣ በተበበር ለሁላችንም የሚበጅ ቤት እንሥራ ለማለት ይቻላል:: ሆኖም ይህ ሃሳብ ሊቀርብ የሚችለው፣ በመጀመሪያና በተቀዳሚ ደረጃ በግፍ ከሚማቀቅበት እሥር ቤት ነጻ እንዲለቀቅ ስንታገል ብቻ ነው::በብሔር ጥያቄም እንዲሁ::

በተለይ በአንድ መደበኛ ማርክሲስት ፕሮግራም ውስጥ የመገንጠል መብት ጥያቄ አስፈላጊና ተገቢ ቦታ አለው:: 'ያለ ገደብ' በሚለው በተደበዘበዘ ሐረግ ሊተካ አይችልም:: ይህንንም የኢ.ሕ.አ.ፓ ፕሮግራም ነዳፊዎች አጥተውት አይደለም:: የኢትዮጵያ ገዥ ከተማሪው ንቅናቄ የተወለደ እንደመሆኑ መጠን፣ የኢ.ሕ.አ.ፓ ሰዎች በተማሪው ንቅናቄ ውስጥ በዚሁ ጥያቄ ላይ የተደረጉት ውይይቶች፣ የመገንጠል መብት በማወቅ የተወሰዱትን አቋሞች በደንብ አድርገው አጠናቀው ያውቃሉ:: በፕሮግራማቸው የመገንጠልን መብት ያላነሡበት ምክንያት ቢኖር ተምክህተኛነታቸውና አድርባይነታቸው ብቻ ነው::

በተለይ 'ያለ ገደብ' መብት እናውቃለን የሚለው አባባል አቀዱ፣ ሁለቱንም ማለትም ጨቋኙን ብሔርና ተጨቋኙን ብሔሮች፣ ተምክህተኛውንና ጭምከራቱን ሳለማስከፋት በሁለቱም ርካሽ ተወዳጅነት ለማትረፍ ነው፣ ለተጨቋኙ ብሔር የመገንጠሉ መብት 'ያለ ገደብ' በሚለው ሐረግ ተጠቃሏል አትስጋ፣ ግልጽ ድንቋ እኮ ነው ተብሎ ይነገረዋል:: ለማስረዳትም የኢ.ሕ.አ.ፓ እጅ ወደ መዝገበ ቃላት ይቃጣዋል:: ለጨቋኙ ብሔር ተምክህተኛ ደግሞ፣ 'ያለ ገደብ' የምትለዋ ትንሽ ብታጠራጥረውም፣ በግልጽ 'ፈቃደ መዋህድ' የምትለው መገፈሩን ታረጋጋዋለች::

ያም ሆነ ይህ የኢ.ሕ.አ.ፓ ከነሌኒን ወዲህ እና እስከምናውቀው ድረስ በታሪክ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ አንድ ኮሚኒስት ፓርቲ ነኝ የሚል / ከቻይና በስተቀር፣ ይቻይና ሁ[illegible] ነበር/ የመገንጠልን መብት ፕሮግራሙ ውስጥ ያለማንሣቱ ከበር ተጎናጽፏል:: ለምሳሌ እንደ የኢ.ሕ.አ.ፓ ፕሮግራም ሳይሆን ሌኒን ያቀረበው የፕሮግራም ማሻሻያ ንድፍ የሚከተለውን ይላል::

"a) the right of all member nations of the state to freely secede and form independent states. The republic of the Russian nation must attract other nations or nationalities not by force, but exclusively by voluntary agreement on the question of forming a common state. The unity of fraternal alliance of the workers of all countries are incompatible with the use of force, direct or indirect, agianst other natioanlities" (Coll. Works, Vol. 24, p. 472-3)

ሌኒን ስለ አንድነት ከማውራቱ በፊት፣ በመጀመሪያ ስለ መገንጠል መብት ይናገራል:: በመጀመሪያም ስለ መገንጠል መብት ማንሣቱ፣ በፕሮግራሙ ውስጥ ይህ ጥያቄ ያለውን ተቀዳሚ ቦታ ያመለክታል::

ባጠቃላይ ለመናገር የኢ.ሕ.አ.ፓ በብሔር ጥያቄ ላይ ያለው አቋም በብሔርተኝነት የተበከለ ለመሆኑ ምንም ጥርጥር የለውም:: ይህም በመሆኑ የተጨቆኑ ብሔሮችን ቁጣና ተቃውሞ አስነስቷል:: ለምሳሌ በአሜሪካ የኤርትራ ተማሪዎች ማኅበር በዚሁ ቡርዧ ሾቪኒስት ፕሮግራም ያለውን ተቃውሞ አሰምቷል እንዲሁም የኦሮሞና የሌሎችም ጭቁን ብሔሮች ተራማጆች የተቃውሞ ድምጻቸውን በማሰማት ይገኛሉ:: በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር ከተጨቆኑ ብሔሮች ጎን በመሰለፍ ይህን ቡርዧ ሾቪኒስት ፕሮግራም በጥብቅ ያወግዘዋል፣ ይታገለዋልም::

<u>የወዝ አደር ጥቅም ጥያቄ</u>

የወዝ አደሩና እንዲሁም የጠቅላላው ሳብ አደር / **labouring masses** / ጥቅም የሚመለከተው ክፍል፣ በአንድ ማርክሲስት ሌኒኒስት ፓርቲ ዝቅተኛ ፕሮግራም ከፍተኛ ቦታ አለው:: እነዚሁ ወዝ አደሩ የሚያቀርባቸው ጥያቄዎች የካፒታሊስት ሕብረ ሰብን የሚሽሩ ሳይሆን፣ በካፒታሊስት ሕብረተ ሰብ ውስጥ ወዝ አደሩ የሚያርፍበትን ጭቁና በመመጠን፣ ወዝ አደሩን ከሞራል፣ ቡርዧልና አካላዊ ውድቀት በማዳንና በዚሁም ባቢያ ወዝ አደሩለቡርዧሊዝም በሚያደርገው ትግል በሕሊናም ሆነ በሰውነት ብቁ እንዲሆን የሚያስችሉት ናቸው:: ይህም ሲሆን፣ በዚሁ ክፍል ውስጥ የሚነሡ ጥያቄዎች ለወዝ አደሩ ትግል ከፍተኛ ጥቅም ስላላቸው፣

በዙንጊዜ የሞትና የሕይወት ጥያቄዎች ስለሆኑ፣ በጅምላ በአጠቃላይ ተጠይቀው የሚታለፉ ባይሆኑ፣በዝርዝር አንዱም ነገር ሳትቀር መጠቀስ አለባቸው:: መደበኛም የሆኑት የማርክሲስት ፕሮግራሞች ሙሉ ይህን ዱንብ ተከትለው እናገኛቸዋለን:: የኢ.ሕ.አ.ፓ ራሱን እንደወዝ አደር ፓርቲ መቁጠሩ አለቀረምና፣ የወዝ አደሩን ጥቅም የሚመለከቱ ጥያቄዎች ማንሣቱ ስለሚናርበት፣ በዚሁ ከፍተኛና አቢይ ጉዳይ የኢ.ሕ.አ.ፓ አቋም፣ የሚያነሣቸውንና የማያነሣቸውን ጥያቄዎች መመልከቱ ይበጃል:: በመጀመሪያ የኢ.ሕ.አ.ፓ ፕሮግራምበሌሎችበአጫፋሪ ጥያቄዎች አስከሚያስለች ድረስ ጥያቄን ነገርች



አያነሳ ሲረባረብ፣ የወዝ አደርን ጥቅም መጠበቅን በሚመለከተው በኩል ግን 'የሚዘነጋቸውን' አቢይ ነጥቦች ወደ መመልከቱ እናምራ:: ባሁኑ ወቅት የወዝ አደሩ ተጨባጭ የሆኑ፣ ነገር በኢ.ሕ.አ.ፓ ፕሮግራም የማይጠቀሱ ጥያቄዎች እንደሚከተለው እንዘረዝር

1/ በፋብሪካዎችና በኢንዱስትሪዎች በሥራ ሠዓት ልክ ሳይሆን 'በሥራ መጠን ክፍያ'/ **piece work wage** / የሚባለው ፈሊጥ እንዲወገድ መጠየቅ ይህ የደሞዝ አከፋፈል ዘዴ፣ ወዝ አደሩን የሚከፋፍል፣ በወዝ አደሮች መሀል ያለውን ውድድር የሚያጠናክርና፣ እንዲሁም ወዝ አደሩን የበለጠ ተበዝባዥ ስለሚያደርገው ኮሚኒስቶች በየቦታው የሚታገሉት ነው::

2/ የሌሊት ሥራ፣ በቴክኒካል ምክንያቶች ካላስፈለገ በስተቀር በሕግ እንዲከለከል መጠየቅ:: የሌሊት ሥራ ወዝ አደሩን የሚከፋፍል በመሆኑና፣ ሌሊት የሚሠሩት ወዝ አደሮች በቀን መተኛት ስለሚገደዱ፣ የዚሁ ዓይነት ሥራ ሕብረተ ሰቡ የሚነጥሳቸውና ሕሊናዊ ጤንነታቸውን የሚጎዳ በመሆኑ ኮሚኒስቶች ይቃወሙታል:: ይህ ጥያቄ በጀርመን ሶሺያል ዲሞክራቲክ ፓርቲ ኤርፉርተር ፕሮግራም / **Erfurter program** / ከገባበት ጊዜ ጀምሮ፣ በዓለም አቀፉ ወዝ አደር ትግል ሰንደቅ ላይ የሰፈረ ነው:: እንዲሁም ስመ ጥሩው ፓሪስ ኮምዩን እንደተደነገገው /1871/ ከመጀመሪያዎቹ እርምጃዎች አንዱ የሌሊት ሥራን መከልከል ነበር::

3/ የተጨማሪ ሰዓት ሥራ / **overtime work** / እንዲከለከል መጠየቅ:: የሥራ ሰዓት በሕግ ቢወሰንም፣ ብዙን ጊዜ ወዝ አደሩ 'በፈቃዱ' ተጨማሪ ደሞዝ ለማግኘት በሕግ ከተወሰነው የሰዓት ክልል በላይ ይሠራል:: ምንም እንኳ በዚሁ የሰዓት አሳፊ ሥራ የሚያገኘው ደሞዝ ከመደበኛው ደሞዝ ከፍ ቢለውም፣ በዚሁ የትርፍ ሰዓት ሥራ የሚጠቀመው ካፒታሊስቱ፣ የሚጎዳው ወዝ አደሩ ነው:: ወዝ አደሩ አንበል በቀን ስምንት ሰዓት ከሥራ ወዲህ በተጨማሪ መስፋቱ በሰውነቱ ላይ ያለው ተጽዕኖ ከፍተኛ ነው:: የሥራ ቀኑ ወደ ፍጻሜ ሲያደላ፣ ወዝ አደሩ በበለጠ እየደከመው እንደሚሄድ ሁሉ፣ ማናቸውም ተጨማሪ የሥራ ሰዓት የድካሙን በተፈጠነ አኳኋን መባባስ፣ የጉልበቱም መዛልና የሰውነቱ መበሳትን ያስከትላል:: በዚሁም የሰዓት አሳፊ ሥራ የሚያገኘውም ተጨማሪ ደሞዝ፣ ብዙውን ጊዜ ለዚሁ ሰዓት አሳፊ ሥራ ያወጣውን ተጨማሪ ጉልበት ለመተካት / የበለጠ ለመሥራት፣ በበለጠ መብላት ፣ ማረፍ ወዘተ.. ይናርበታል/ እንኳን አይበቃም:: በመጨረሻው ደረጃ ወዝ አደሩ ምናልባት ያለ ጊዜ ከማርጀትና መቃጠት በስተቀር ከዚሁ የሰዓት አሳፊ ሥራ የሚያተርፈው አንዳችም ነገር የለም:: ለካፒታሊስቱ ግን የሰዓት አሳፊ ሥራ፣ የእርባታ መሣሪያዎቹ ሥራ የሚፈቱበት ጊዜ ይቀንስለታል፣ ባንድ በተወሰነ ጊዜ ውስጥም በበለጠ ለማምረት፣ ለመነገድና በተፋጠነ አኳኋን ካፒታል ለማጠራቀም **/accumulation** / ያስችለዋል:: የካፒታሊስቱን በዝበዛ ለመመጠን ብቻ ሳይሆን፣ የወዝ አደሩን ጤንነት ለማጠበቅና እንዲሁም በትርፍ ጊዜው በቡርዧልና በፖለቲካ መስኮች መሳተፍ እንዲችል ኮሚኒስቶች በያሉበት የሰዓት አሳፊ ሥራን ለማስወገድ ይታገላሉ::

4/ የደሞዝ ክፍያ በገንዘብ እንጂ፣ ዕሽቀጥ መሆኑ እንዲቀር።የኢትዮጵያ ውስጥበተለይ በአነስተኛ ማፍሪያ ሥፍራዎች ወዝ አደሩ ለጉልበቱ ብዙን ጊዜ በንዋይ ሳይሆን፣ ለኑሮው ይሆኑታል፣ በሚባሉ ሸቀጦች ይገባል:: ይህ አይነቱ አከፋፈል ዘዴ ኢትዮጵያ ውስጥ በጣም የተስፋፋ ቢሆን፣ ከፊውዳል ርዝራዦች ያልተላቀቀው የኢትዮጵያ ካፒታሊዝም መደበኛ ጠባዮች ከሆኑት አንዱ ነው:: የዚሁ አከፋፈል ዘዴ ጉዳት ሁለት አይ ነው::

ሀ/ ወዝ አደሩን በበለጠ ከቀጣሪው ጋር ያስተሳስረዋል፣ ተንቀሳቃሽነትም በመቀነስ የከበርቴውን ጭቆና ብዝበዛ ለመቋቋም ያለውን ችሎታ ያገባል::

ለ/ እንደ ደሞዙ የሚሠጡት ሸቀጦች ቀባቀቦች ብዙውን ጊዜ ከዋጋቸው በላይበለሚገመቱ፣ ወዝ አደሩ ላወጣው ጉልበት ተመጣጣኝ ካሳ አይገኝም:: ይህ የአከፋፈል ዘዴ ወዝ አደሩን በበለጠ ለመበዝበዝ የሚያስችል መሣሪያ ነው::

5/ ለመቀጫም ሆነ በሌሎች ምክንያቶች ከወዝ አደሩ ደሞዝ መቆረጥ የሚባለው ፈሊጥ በፍጹም እንዲወገድ መጠየቅ::እቃ ሰብረሃል፣ አጥፍተሃል ወዘተ.. በማለት የወዝ አደሩን ደሞዝ መቀነስ፣ ካፒታሊስቶች ወዝ አደሩን ለማንበረከክና ለመበዝበዝ የሚጠቀሙበት ዘዴ ነው::

6/ በሥራ መስክ ለወዝ አደሩ ጤንነትና አካል ጠንቅ የሆኑት ነገሮች በሕግ እንዲወገዱ፣ ለወዝ አደሩ ጤንነት አስፈላጊውን መከላከያ እንዲደረግ መጠየቅ:: በቅጥር ቦታ የጤንነት ጉዳይ የሚመለከቱ ነገሮች በሙሉ ከወዝ አደሩ መሀል በተውጣጣ ተቆጣጣሪ ቡድን ሥር እንዲሆኑ::

የኢትዮጵያ ወዝ አደር በሚሠማራበት ሥራ መስክ ላይ፣ ለጤንነቱና ለአካሉ ከፍተኛ ጠንቅ ያዘለ ሁኔታ ውስጥ ይገኛል:: ከመርዘኛ እንፋሎት ጭስ ወዘተ.. እስከ በሞተር ውስጥ መጨፍለቅ የመሳሰሉ አደጋዎች እንዳሳደዱት፣ እንዳከሳሹትና አካለ ስንኩል እንዳደረጉት ነው:: ባሁኑ ቴክኒክ ደረጃ የተመለከትነው እንደሆነ ግን ከ100 አደጋዎች አስፈላጊው ጥንቃቄና መከላከያ ቢደረግላቸው ዘጠና ዘጠኙ ሊታገዱ የሚችሉ ናቸው:: ለቀጣሪዎች ግን ጥንቃቄ ማድረግ ትርፋቸውን የሚቀንስ ተጨማሪ ወጪ ስለሚሆንባቸው ከዚሁ ይቆጠባሉ:: አንዱ ወዝ አደር አካለ ስንኩል ቢሆንባቸው አባረውት ቁጥር ስፍረ ከሌለው የሥራ አጡ ሠራዊት መሀል ሊተኩት ስለሚችሉ፣ ስለ ወዝ አደሩ ደህንነት ፍጹም ግድ የላቸውም::

7/ የእንስታይ ጾታ ሠራተኞች፣ ለጤንነታቸው አደገኛ የሆኑ ጠንቅ ያላቸው ሥራዎች እንዳይሠሩ እንዲሆን መጠየቅ:: ብዙውን ጊዜ ካፒታሊስቶች ሴት እንደ ወንዱ አትደፍረንም፣ ጭቆና የበለጠ ትችላለች፣ አነስተኛም ደሞዝ ይበቃታል በማለት የሥራውን ዓይነት ሳይመለከቱ በወንዶች ፈንታ ሴቶችን መቀጠርን ይመርጣሉ:: ሴቶች በፊውዳልና በካፒታሊስት ሕብረተሰብ ውስጥ በነርሱ ላይ ከሚደርሰው የጾታ ጭቆና የተነሣ ሰውነታቸው እንደ ወንዱ ያልዳበረ በመሆኑና እንዲሁም የእናት ሚናቸው በሰውነታቸው ላይ ተጨማሪ ሸክም ስለሚሆን ሊሠሯቸው የሚችሉት የሥራ ዓይነቶች የተወሰኑ ናቸው::



8/ በኢንዱስትሪናዎች ውስጥ ተቀጥረው በሚሠሩትና በመንግስት መሥሪያ ቤት ውስጥ ተቀጥረው በሚሠሩት ወዝ አደሮች መሀል በሕግ የሚደረገው ልዩነት እንዲወገድ መታገል:: ለመንግስት መሥሪያ ቤት፣ እንደ ቴሌኮሚኒኬሽን፣ አውራ ጎዳና ባለሥልጣን፣ ወዘተ.. ሠራተኞች ሙያ ማኅበራት የመደራጀትና የሥራ ማቆም መብት በሕግ እንዲታወቅ ማድረግ::

አላይ የዘረዘርናቸው ነጥቦች በሙሉ፣ የወዝ አደሩ ወገን ነኝ ለርሱም እቆረቆራለሁኝ በሚለው የኢ.ሕ.አ.ፓ ያልተነሡ፣ ያልተጠየቁ ጥያቄዎች ናቸው:: በጠቅላላው ፕሮግራሙ ውስጥ ለነጋዴው ይህን አደርጋለሁኝ፣ ለገበሬው ያን አደርጋለሁኝ፣ አዲስ ባላመሬት ፈጥራለሁኝ፣ ብሔራዊ ካፒታል አልነካም ወዘተ.. በማለት በገቢር የተለያዩትን መደቦች ጥቅም ለመጠበቅ ቆርጦ የተነሣው የኢ.ሕ.አ.ፓ የወዝ አደሩን ጥቅም መጠበቅ በሚመለከተው 'ጠበቃነቱ' ያንገዳግዳል:: ለወዝ አደሩ የሕይወት ጥያቄ የሆኑትን እያሉ ነጥቦች ይዘላቸዋል፣ ከመጤፍ አይቆጥራቸውም:: መቼም በዚሁ የሰባት ዓመት 'አንደር ግራውንድ' / underground / ከወዝ አደሩ ጋር ተቀሳቅሶ፣ ብስትግና ተግሎን ቢካፈለው ኖሮ፣ እነዚሁ ነጥቦች ባላመለጡት ነበር:: አፍንጫም ነፍቶ፣ ወዝ አደሩን 'ነጻ ሳወጣህ መጣሁኝ' የሚለውም ጉራ በቀረብን ነበር::

ደግሞስ በየኢ.ሕ.አ.ፓ ፕሮግራም ውስጥ የወዝ አደሩን ጥቅም መጠበቅ በሚለው ረገድ የተነሡት ነጥቦችእንዴት ናቸው? አጥጋቢስ ናቸው ወይ? እስቲ እንመልከታቸው በየኢ.ሕ.አ.ፓ ፕሮግራም የሚከተለውን ጥያቄ ሠፍሮ እናገኘዋለን::

'ከ16 ዓመት በታች የሆኑ ሕጻናት በፋብሪካዎችና በማዕድኖች ውስጥ ተቀጥረው እንዳይሠሩ በሕግ መከልከል'/ገጽ 17/

ከ16 ዓመት በታች የሆኑት ሕጻናት አይሠሩ ሲባል፣ ከ16 ዓመት በላይ የሆኑ ሕጻናትና ለጋ ወጣቶች በፋብካዎችና በማዕድኖች ይሠሩ፣ ሊሠሩ ይችላሉ ለማለት ነው ወይ? የፋብሪካና የማዕድን ሥራ ምን እንደሆነ የማያውቅ ይህን ቢናገር ዝም ብለን ባለፍነው ነበር:: ነገር ግን በማርክሲዝም፣ ሌኒኒዝም ስም ለካፒታሊስቶች ለጋ ወጣቶች በቀን ስምንት ሰዓት በማዕድን ውስጥ እንዲያሠሩ ፈቅጃለሁኝ የሚሉትን በሙሉ እንደ ወዝ አደሩ ጠላት እንታገለዋለን:: የፋብሪካ ሥራ በተለይም የማዕድን ሥራ ለለጋ ወጣቶች ቀርቶ በዚሁ መስክ ለቆዩት ወዝ አደሮች በጣም ከባዱ ሥራ እንደመሆኑ መጠን፣ ወጣቶች በዚሁም መስክ ይሠማሩ ማለት ካፒታሊስቶች አዲሱን የወዝ አደሩ ትውልድ ከማበቡ በፊት ይቀጩት ማለት ነው::ሌላ ትርጉም ሊኖረው አይችልም:: በኛ ግምት እነ ሌኒንም እንደጠየቁት / የዛሬ 60 ዓመት / ቢያንስ እስከ ሀያ ዓመት ዕድሜ ድረስ ያሉት ወጣቶች በቀን ከራት ሰዓት በላይ / በማዕድንከ2 እስከ 4 ሰዓት / መሥራት ያለባቸውም:: ሌኒን በፕሮግራም ንድፉ ስለዚሁ ሲጽፍ የሚከተለውን ይላል::

"5) Prohibition of the employment of children of school age (under sixteen), restirction of the working day of adolescents (from sixteen to twenty) to four hours, and prohibition of the employment on night-work in unhealthy industries and mines." Coll. Works, Vol. 24, p.474)

ምናልባት የፋብሪካንና የማዕድን ሥራ ከውስጥ ሳይሆንከውጭ ያዩትእንደ የኢ.ሕ.አ.ፓ ሰዎች ከ16 ዓመት በላይ የሆኑ ወጣቶች እንደሌላው ሰውሉ ይሥሩ ይሉ ይሆናል:: ለዚሁ መድሁኒት የኢ.ሕ.አ.ፓ ፕሮግራም ነዳፊዎች እንዳሉት፣ በቀን ስምንት ሰዓት ማዕድን ውስጥ ማሠራት ነበር:: አራት ሰዓት መቻላቸው እንኳ ያጠራጥራል!! ወረድ ብለንም በየኢ.ሕ.አ.ፓ ፕሮግራም ውስጥ የወዝ አደሩን ጥቅም በሚመለከተው ረገድ የሚከተለውን ነጥብ እናገኛለን::

"ማንኛውም ሠራተኛ በዓመት ውስጥ ቢያንስ የ100 የሥራ ቀን እረፍት እንዲኖረው ማድረግ::" ገጽ 17

ለማወናበድ ያሀል ደግሞ ይኸው ዓረፍተ ነገር በእንግሊዝኛው ትርጉም፣

**To ensure that every worker has an annual leave of at least 25 working days** ይሆናል እንዱ መቶ /100/ በእንግሊዝኛ ሲጻፋት ሃያ አምስት /25/ ይሆናል፣ ሃያ አምስት /25/ በአማርኛ ሲተጻፍ መቶ /100/ ትሆናለች:: ጉራም ማወናበድ! ፕሮግራሙ ከወጣ እነሆ 4-5 ወራት ሊሞላው ነው፣ ነገር ግን እስከሁን ድረስ የኢ.ሕ.አ.ፓ በየትኛው እንደረጋ ገና አላበሰረልንም::መቶ ወይም ሃያ አምስት? እስከዛን ድረስ በእነበባችሁት ቋንቋ ተረዱት ነው ነገሩ!

በኛ ግምት የኢ.ሕ.አ.ፓ እውነትም የወዝ አደሩ ፓርቲ ቢሆን ኖሮ በዚሁ አቢይ የመደብ ትግል ጥያቄ እንዳቸም ውዥንብር እንዳይፈጠር በጣረ ነበር። ይህ ቀራኒ እውነትም የአትም ስህተት ከሆነ ያኔውኑ ማስተካከል ነበረበት:: ይህም ውለታ ለፕሮግራሙ አንባቢ ብቻ ሳይሆን፣ በተቀዳሚ ደረጃ ጉዳዩ ለሚመለከተው ለኢትዮጵያ ወዝ አደር እንዳለበት በተሰማው ነበር::

አንድ ሌላ ጥያቄ ደግሞ አለን::ለምንስ መቶ ቀናት ለምንስ ሃያ አምስት ቀናት ተባለ? የኢ.ሕ.አ.ፓ ከምን ተነሥቶ እነዚሁን የቀናት ቁጥር እንደመረጠ ገልጾ አይደለም:: መቶ ቀናት በአከታታይ ወዝ አደሩ ይረፍ ብሎ መጠየቁ፣ ባሁኑ የእርባታ ሀይሎች እድገት ደረጃ እንዴር ፈጽሞ እንደማይቻል ለኢ.ሕ.አ.ፓ ሰዎች ቀርቶ፣ ለማንም ሕጻን እንኳ ገልጾ ይመስለናል::እንዲያውም በሰሙት ካፒታሊስት አገሮች እንኳ ቀርቶ በሶሺያሊስት አገሮችም ያለው ወዝ አደር ብዛ ቢል በዓመት ከ4 ሳምንት በላይ እረፍት የለውም:: ባሁኑ ወቅት በአሜሪካና በአውሮፓ ውስጥ የሚካሄደውንም የመደብ ትግል ስንመለከት፣ የነዚሁ አሀጉራት



ወዝ አደር የስምንት ሳምንት እረፍት የሚለውን ጥያቄ ካነሳ ገና ጥቂት ዓመታት ቢያስረው ነው:: የኢ.ሕ.አ.ፓ እዲስ እንደመሆኑ መጠን በሶሺ አገሩ እነዚሁን ሁሉ ቀድሞ በዓመት የ14 ሳምንት /ያው መቶ ቀናት ማለት ነው/ እረፍት ይጠይቃል::

በፕሮግራሙ እንግሊዝኛ ትርጉም የተጠየቀው የሀያ አምስት ቀናት እረፍት የትኛውን የቀን አቆጣጠር እንደተከተለም ገልጾ አይደለም:: ሀያ አራት፣ ሀያ ስድስት፣ ሀያ ሰባት ወዘተ.. ቀናት ሊሆን አይችልም ነበር ወይ? በምን ፕርንሲፕል በመመሥረት ነው ሃያ አምስት ቀናት የተመረጠው? ወዝ አደሩ ይጠይቃል ወይ?

በኛ ግምት የዓመት ሥራ እረፍት ጥያቄ በሚነሳበት ወቅት ሁለት ነገሮችን መያዝ ያስፈልጋል፣

ሀ/ በዚህ ጥያቄ ወዝ አደሩ የሚለውና የሚፈልገው መስማት አለበት
ለ/ የእረፍት ጊዜም አቆጣጠር በቀን ሳይሆን፣ በሚኒስቶች በየቦታው እንደሚያደርጉት በሳምንት መመጠኑ ይሻላል::

በዚሁ ጥያቄ ሃሳባችን ገለጹ ከተባለን፣ የኢትዮጵያን ኤኮኖሚ እድገት ደረጃ፣ የሥራ ፍጥነቱ ወዘተ.. እንዲሁም የወዝ አደሩን ጥቅም በመመልከት ምናልባት የአራት /4/ ሳምንታት እረፍት ለጊዜው ባይበዛ አይቀርም፣ ሆኖም ለፀዓለነው እዚህ ላይ መወሰን ያለበት ወዝ አደሩ ራሱ ነው::

ከዚህ ለጥቆ ወዝ አደሩ በዓመት 100 ቀናት ኦረፍ ይል የነበረው የኢ.ሕ.አ.ፓ በመቀጸበት ለሥራቀልጥፍና ተቆርቋሪ በመሆን "ጊዜ እንዳይጠፋ" የሚከተለውን ይጠይቃል::

"ሠራተኞች እንዳይጉላሉ፣ በሥራውም ቀልጥፍና እንዲኖራቸው በፋብሪካዎቻቸው ወይም በሚሠሩባቸው አካባቢዎች የመኖሪያ ቤቶችን እያዘጋጁ ሠራተኞችን ማስፈር" /ገጽ 18/በውነቱ፣ የኢ.ሕ.አ.ፓ ፕሮግራም ነዳፊዎች ወ'ሚ ሄደው የወዝ አደሩን ኑሮ እንዲያቁ ከሆነም እዛው እንዲኖሩ እንመክራለን:: በለወዝ አደሩ ኑሮ ገና ብዙ የሚማሩት ነገር አለና! የፋብሪካው ጋጋታ፣ የሽንከራ ቀረጭ ግማት፣ የፋብሪካው መርዝና ጭስ ወዘተ... እንደ ወንጂ ወዝ አደሩ ፋብሪካውውስጥ ወይም በአካባቢው ይኑር ማለት፣ ወዝ አደሩን ከመቅሳሳው ሕብረቱ ሰብ መነጠል በሥራው ጊዜ ብቻ ሳይሆን፣ በእረፍት ወቅቱም የፋብሪካው እስረኛ ይሁን ማለት ነው:: በእኛ ግምት ካፒታሊዝም ሙሉ በሙሉ ተደምስሶና ኮሚኒዝም እስኪመሠረት፣ በሥራና በኅብረተሰብአዊ ኑሮ መሐል ያለው ልዩነት ጨርሶ እስኪጠፋ፣ በከተማና በገጠር መሐል ያለው ልዩነት እስኪስተካከል ድረስ የወዝ አደሩ መኖሪያና ሥራ ቦታ አንድ ይሁኑ ማለት ስህተኛ እንደውም ፀረ ወዝ አደር ነው::

በአሁኑ ጊዜ ኢትዮጵያ ውስጥ ሊጠየቅ የሚችለው ወዝ አደሩ ከሕብረተሰቡ ሳይነጠል ከፋብሪካው ገለል ብሎ ገጠራቂ ባለ ቦታ በማስፈር ከሥራው ቦታ ሲመለስ እንዲያርፍ፣ እንዲረጋጋና እንዲዝናና ማስቻል ነው:: የኢ.ሕአ.ፖ.ን ያስጨነቀውን

“የሥራ ቀለቶናና” በሚመለከተው በኩል በሥራ ቦታውና በመኖሪያ ሠፈሩ መጠለ ፈጣንና ነፃ የሆኑ መገናኛ መስመሮችን በመዘርጋት / ከሆነ ወዝ አደሩ ለመጓጓዝ የሚያጠፋውን ጊዜ እንዲከፈለው ማድረግ/ ይህ ችግር ሊቃለል የሚችል ይመስለኛል::

በአጠቃላይ ስንመለከተው፣ፕሮግራሙ እንደሚያንፀባርቀው ማለታችን ነው፣ የኢ.ሕ.አ.ፓ የወዝ አደሩ ፖለቲካ ድርጅት መሆኑ ቀርቶ የወዝ አደሩን ምሬት፣ ብሶትና መሠረታዊ ችግሮችእንኳ ገና አጠናቆ አላወቀም:: ይህም ፈጽሞ ሊያስገርም አይገባም:: የንዑስ ከበርቴ ደገፊዎችና አድርባዮች በወዝ አደሩ ስም ለመነገድ ለመመጻደቅ ቁጢ ነሱበት ወቅት ሁሉ ጊዜ የሚያባቁት /የሚያጋልጡት/ ጉድለት ነው::

<u>የቤት ጥያቄና የንዑስ ከበርቴው አቋም</u>

የኢ.ሕ.አ.ፓን ንዑስ ከበርቴነት በበለጠ ለማሳየት በቤት ጥያቄ ላይ ያለውን አቋምና የሚያቀርበውን መፍትሔ መመልከቱ ይጠቅማል:: በፕሮግራሙ ውስጥ የሚከተለውን ሰፍሮ እናገኛለን፣

“የቤት ኪራይ በየጊዜው ይቀነሳል ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ተከራዩ የቤቱ ባለቤት ይሆናል::” ገጽ13

ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ተከራዩን የቤቱ ባለቤት ማድረግ ምን ፍች እንዳለው፣ ማን ገስ እንደሚጠቀም ከማርክሲዝም ጋር ያለውን ግንኙነት ፍጹም ስውር ነው:: በማርክሲዝም ሌኒኒዝም አንጻር የቤት ጥያቄ የሚፈታው ተከራዮችን የሚከራዩትን ቤት ባለቤት በማድረግ አይደለም:: እንዲያውም ተከራዮችን የቤቶቻቸው ባለቤት ማድረግ በፍሬዴሪክ ኤንግልስ እንደ አድሃሪ እርምጃ ይቆጠራል::

"How little revolutionary Prodhoun's proposal to make the workers owners of their dwellings was can be seen from the fact that bourgeois socialism even before him tried to carry it out in practice and is still trying to do so. Here Sax (bourgeois philanthropist- anthor.) also declares that the housing problem can be completely solved only by transferring property in dwellings to the workers..." (Engels , the Housing Question, p44-45)



ኤንግልስ ለጥቆ

"The whole conception that the worker should buy his dwelling rests again on the reactionary basic outlook, already emphasized, of Prodhounism, ... which... is nothing but an idealized restoration of small scale enterprise, which has gone and is still going to rack and ruin." (ibid. p, 29)

በኤንግልስ አስተሳሰብ ወዝ አደሩን፣ ተከራዩን ወዝ አደር የመኖሪያ ቤቱን ባለቤት ማድረግ፣ ባንድ የተወሰነ ቦታ ስለሚያሥረውና ተንቀሳቃሽነቱን ስለሚቀንስ፣ ከከበርቴው ጋር በሚያካሂደው ትግል እንቅፋት ይሆነዋል:: ለምሳሌ ወዝ አደሮች ከቀጣሪያቸው ከበርቴ ሲጣሉ፣ ጥለውት ሌላ ቦታ ሄደው ሊቀጠሩ ስለሚችሉ ከበርቴው ሠራተኞቹን እንዳያጣ ሥጋት ያድርበታል:: ነገር ግን በተቀጠሩበት አካባቢ የመኖሪያ ቤቶቻቸው ገበረተኞች ከሆኑ ከቀጣሪያቸው ጋር በሚጣሉበት ወቅት ወዝአደሮቹ በቀላሉ ወደ ሌላ ቦታ ሊፈልሱ አይችሉም:: ወደዱትም ጠሉትም፣ በተለይ በአካባቢው ሌላ ቀጣሪ ከሌለ፣ ለእለት ጉርሳቸው ሲሉ ወደ ተጣሉት ቀጣሪያቸው ተሸገፈው መመለስ ይኖርባቸዋል:: በቤት የግል ገበረትነት አንገታቸው ላይ የተሸከሙት ድንጋይ እንጂ የኑሮ መሻሻልን አያመለክትም:: ስለዚህም ኤንግልስ ሲጽፍ፣

"For our workers in the big cities freedom of movement is the prime condition of existence, and landownership can only be a fetter to them. Give them their own houses, chain them once again to the soil and you break their power of resistance to the wage cutting of the factory owners." (ibid. p. 45)

በእኛ አስተሳሰብ በአዲሲቷ ዴሞክራቲክ ኢትዮጵያ ውስጥ የተራማጆች ጥረት ወዝ አደሩ፣ ማለት ሰፊው ላብ አደሩ ሕዝብ፣ የሚኖርበት ቤት ባለቤት እንዲሆን መታገል ሳይሆን /ይህ እንኳ ንዑስ ከበርቴነት ነው::/ ለእያንዳንዱ ቤተሰብ በርካሽ ዋጋ ዋጋ የሚከራይ ንጹሕ፣ በቂና ሰብዓዊ መኖሪያ ቤት እንዲኖር መታገል ነው:: እንዲያውም ሰፊውን ላብ አደር የመኖሪያ ቤቱ ባለንብረት ማድረግ ሌላ ተጨማሪ ጉዳት አለው:: አለው:: እንደሚታወቀው በማርክሲስት ቲዎሪ መሠረት የወዝ አደሩ ደሞዝ፣ ለኑሮው በሚያስፈልጉት ሸቀጦችና አገልግሎቶች ዋጋ ይወሰናል:: እነዚሁ የኑሮ ወጭዎች እንደ ለምግብ፣ ቤት ኪራይ ወዘተ. የመሳሰሉት ናቸው:: ወዝ አደሩ የመኖሪያ ቤቱ ባለ ቤት ከሆነ፣ የቤት ኪራይ መክፈል ስለሚቀርበት የኑሮው ዋጋ ረከሰ ማለት ነው፣ በዚህም መጠን ደሞዙ ይወርዳል:: ኤንግልስ ይህን ነጥብ ሲያብራራ የሚከተለውን ይላል

"Let us assume that in a given industrial area it has become the rule that each worker owns his little house. In that case the working class of that area lives rentfree;,housing expenses no longer enter into the value of its labor power. Every reduction in the cost of production of labor power, that is to say, every permanent reduction in the worker's necessities of life is equivalent on the basis of the iron laws of the doctrine of natioanl economy to a depression of the value of labor power and will therefore finally result in a corresponding drop in wages. Wages would thus fall on an average as much as the average sum saved on rent, that is, the worker, would pay rent for his own house, but not, as formerly, in money to the house owner, but in unpaid labour to the factory owner for whom he works." (ibid. p46)

ለማየት እንደተቻለነው፣ በቤት ጥያቄ ላይ የኢ.ሕ.አ.ፓ አቋም የንዑስ ከበርቴ እንግልስ የቡርዧ በጎ አድራጊዎች /bourgeois philanthropist/ ከሚላቸው ከላቸው አቋም የማይለይ ሆኖ እናገኘዋለን::



## በኢትዮጵያ ውስጥ የወዝ አደሩ ፓርቲ መደራጀት ጥያቄ

ባሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ የማርክሲዝም፣ ሌኒኒዝም ርዕተ ዓለም በተቀበሉ ምሁራን መሀል የማርክሲስት ፓርቲ መደራጀት አንገብጋቢና ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው ጉዳዩ ተግባር እየሆነ ሄዷል:: ለዚህም ሁለት ምክንያቶች አሉት::

ሀ/ ባሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ ሕዝቦች የሚያካሂዱት ፀረ ፊውዳል፣ ፀረ ኢምፔሪያሊስት አብዮታዊ ትግል ግቡን እንዲመታ በወዝ አደሩ ፓርቲ አማካኝነት የወዝ አደሩ አመራር ስለሚያስፈልገው፣

ለ/ የወዝ አደሩ ፀረ ካፒታሊስት ትግል፣ ባሁኑ ወቅት ይህ ትግል በሁለተኛ ደረጃ ቢካሄድም፣ መደራጀት ስላለበት::

የኢትዮጵያ ወዝ አደር ፓርቲ የሚፈጠረው በመቀጸበት፣ ስለ የቤት፣ ጋይም ገለ ሰቦች ተደራጅተው ራሳቸውን 'ኮሚኒስት ፓርቲ' ብለው በመጥራት ቢሆን፣ ከፍተኛ የፖለቲካና ርዕተ ዓለማዊ ትግሎች ተደርገውለትና አስፈላጊ የሆኑት ሁኔታዎች ሲሟሉለት ነው:: ለነዚሁ አስፈላጊ የሆኑ መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎች ባንድ በኩል የወዝ አደሩ እንቅስቃሴና የሳይንሳዊ ሶሺያሊዝም ቲዎሪ መዋሃድ በሌላ በኩል ደግሞ በሚካሄዱት ርዕተ ዓለማዊ ትግሎች የአብዮታዊ ማርክሲስት ምሁራን ስምምነትና አንድነት መመሥረት ናቸው:: ይህም የሚከናወነውና ሊከናወን የሚቻለው አሁን በወዝ አደሩ እንቅስቃሴ ውስጥና እንዲሁም በተራማጅ ምሁራን መሀል የሰፈነውን ውጉንበር በማስወገድ፣ እንደ የኢ.ሕ.አ.ፓ በወዝ አደሩ የሚገዚትን ንዑስ ከበርቴ አድርባዮችና ፀረ ወዝ አደር ሀይሎች በመታገልና በማጋለጥ ነው::

የአደረጃጀቱን ጥያቄ በተሟላው ለማገናዘብ፣ የአንድ ኮሚኒስት ፓርቲ መገንቢያ ጡቦች የሆኑትን የወዝ አደሩ እንቅስቃሴና ማርክሲስት ምሁራን ኢትዮጵያ ውስጥ ባሁኑ ወቅት የሚገኙበትን ሁኔታ መመልከት ያስፈልጋል:: ስለቀደመን የወዝ አደሩን እንቅስቃሴ እንመልከት:: የኢትዮጵያ ወዝ አደር እንቅስቃሴ እስካሁን ድረስ ሁለት የታሪክ ደረጃዎች አሉት ቢባል የተሳሳተ አይመስለንም:: የመጀመሪያው የእድገት ደረጃው ከተወለደበት ጊዜ አንስቶ እስከ የካቲቱ እንቅስቃሴ ሲዘረጋ፣ ሁለተኛው የእድገት ደረጃው ደግሞ ከየካቲት እንቅስቃሴ መጀመሪያ ወዲህ ያለውን ጊዜ ያጠቃልላል:: የመጀመሪያው የእድገት ደረጃ ወዝ አደሩ የተወለደበት፣ ምንጩ ከሆኑ ከገበሬው መሳቀቅ የጀመረበት፣ ያበበት፣ ህይሎቹን የሰበሰበበት ወቅት ነበር:: በዚሁ ስጋነት ዘመኑ፣ ወዝ አደሩ ተበዝባዥ መደብ ከመሆን አልፎ፣ የበሺያልና የኢኮኖሚ መብቶቹን ለማስከበር የተሰበጣጠረ ቢሆንም አያሌ የሙያተኛ / trade unionist/ ትግሎች አካሄዷል:: ነዚህ የተለያዩ ትግሎች የጎረመሰው ወዝ አደር መደብ፣ ከጠላቶቹ ጋር ትንቅንቅ የሚለካከቡትና የሚያኮበርባቸው ትግሎች ነበሩ:: በሁለተኛው የእድገት ደረጃው፣ በተለይ በየካቲት እንቅስቃሴ አፍላ ላይ በተካሄደው አጠቃላይ ሥራ ማቆም አድማ /general strike / እንደታየውም፣ ወዝ አደሩ ራሱን እንደ አንድ መደብ

ዩሮፕ በፖለቲካ መድረክ ውስጥ በመደብ ደረጃ መጣቱና መታገል ጀመረ:: ይህም የወዝ አደሩ በተበጣጠሩ አካባቢያዊ ትግሎችፕ ወደ ተጠቃለለ በሄር አቀፍ ትግሎችፕ መሸጋገር በጠባቡ ትርጉም / strict sense / የመደብ ትግሉን ለመጀመሪያ ጊዜ በሚገባ እንዲያካሂድ ያስቻለዋል:: እንደዚሁ ባንዱ ፋብሪካ ውስጥ ያሉት ወዝ አደሮች በቻቸውን የሚሪያቸው የሆነውን ካፒታሊስት ግለሰብ መታገል ቀርቶ፣ በየካቲቱ እንቅስቃሴ ውስጥ ወዝ አደሩ በሙሉ በአንድነት እንደ አንድ መደብ በመነሳት መቶሳሰውን የከበርቴውን መደብና እርሱን የሚደግፈውን መንግስት ተዋጋ:: ትግሉ በየቋት ወዝ አደሮችና በአንዱ ካፒታሊስት መሀል ብቻ መሆኑ ቀርቶ፣ በወዝ አደሩ መደብና በከበርቴው መደብ መሀል የሚካሄድ ሆነ::ትግሉ በውነትም የመደብ መለከ ጀ::

የኢትዮጵያ ወዝ አደር በየካቲቱ እንቅስቃሴ እንደ አንድ መደብ ቢነሳና ቢታገልም ያሳየው ንቃት የመደብ ንቃት እንጂ ፖለቲካዊ የመደብ ንቃት አይደለም:: /እዚህ ላይ ፓለቲካዊ የመደብ ንቃት ስንል በማርክሲስት ሌኒኒስት ፍቺው በመቀርጸ በሶሺያሊስት የመደብ ንቃት ማለታችን ነው::/ በየካቲቱ እንቅስቃሴ ወዝ አደሩ ዲሞክራሲያዊ ፖለቲካ ጥያቄዎች በሠነዘርም፣ እነዚህን ጥያቄዎች ከሶሺያሊስት አብዮት አንጻር፣ ለሶሺያሊዝም ከሚደረገው ትግል ጋር በማያያዝ አላነሣም:: የትግሉን አቅጣጫና ግብ የሚያበራለት ማርክሲስት ፓርቲ አስከሌለ ድረስ፣ ይህንም ሊያደርግ አይችልም:: እንዲሁም በየካቲቱ እንቅስቃሴ የኢትዮጵያ ወዝ አደር ታላቅ ሚና በጫወተም፣ እንቅስቃሴውን ሊመራ አልበቃም:: ምክንያቱም ይህ ማርክሲስት ሌኒኒስት ፓርቲ ባለመኖሩ ነው:: እንዲያውም ሌኒንም እንደሚለን ወዝ አደሩ ሶሺያሊስት ንቃት እስከሌለው ድረስ የሚኖረው ንቃት በግድ የከበርቴው ስለሚሆን፣ /ሌላ ሦስተኛ ንቃት ሊኖረው አይችልም ይላል ሌኒን/ በዚህ የተነሣ በየካቲቱ እንቅስቃሴ ወዝ አደሩ ንዑስ ከበርቴውን ተከታይ ነበር:: ሲጠቃለል በየካቲቱ እንቅስቃሴ የወዝ አደሩን ትግል ስንመለከት፣ የዚሁ ትግል ጥንካሬ የወዝ አደሩ ዲሲፕሊን፣ ቆራጥነትና መስዋዕትነትና ታጋይነት ቢሆን፣ ድክመቱ የፖለቲካ ንቃት ጉድለት ነበር:: ይህን ስንል አንዳንድ ባይ አድርባዮች፣ የወዝ አደሩን ትግል ታንቋሸሻችሁ ይሉን ይሆናል:: አንደኛ ነገር፣ የወዝ አደሩ እንቅስቃሴ ጉድለቶች የሚደብቁ የወዝ አደሩ ጠላቶች እንጂ ወዳጆች አይደሉም:: ወዝ አደሩ የተላሉን ጉድለቶች እንዲያውቅ፣ አውቆም እንዲያርማቸውበማድረግ ከአሥር ሰንሰለቶች በስተቀር የሚያጣው አንዳች ነገር የለም:: በወዝ አደሩ ትግል ዱሉ ኀገ የሚያሙ፣ ይህንም ትግል ለማደናቀፍ የሚፈልጉ 'የጥጋብ' ጠላቶች ብዙ አሉ::

ሁለተኛ ነገር ደግሞ፣ የወዝ አደሩ ትግል ያለበትን ሁኔታና ችግሮች የዘረዘርነው የነዚህን ችግሮች መፍትሔ የሆነውን የወዝ አደሩ ፓርቲ መደራጀት አስፈላጊነትን ለማሳየት እንደሆነ ግልጽ ይመስለናል::

ባሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ ወዝ አደር በሰፋ ውስጥ ከፍተኛ ውዥንብር አለ:: ይህ ውዥንብር ላይ የጠቀስነው የፖለቲካ ንቃት ጉድለት ውጤት ብቻ ባይሆን፣



ሌሎች ምክንያቶችም አሉት:: ከነርሱም ዋናዎቹ

ሀ/ ደርጉ ሥልጣን ላይ ከወጣ ወዲህ ባከታታይ የተጠሩት ሁለት አጠቃላይ የሥራ ማቆም አድማዎች /general strikes/ መክሸፍ:: የአንዱ ሥራ ማቆም አድማ መክሸፍ በወዝ አደሩ ሞራልናትግል ዝግጁነት ከፍተኛ ተፃራሪ ተፅዕኖ እንዳሳደረ፣ ተከፋ አብዮታዊ እንደሆነ ለመገመት አስቸጋሪ አይደለም:: ከሌሎች አገሮች ወዝ አደር ትግሎች ሊበስ፲ ያንስ የምንማረውም ነገር ነው::

ለ/ በወዝ አደሩ ስም የሚነግዱትና የሚጠቀሙት ንዑስ ከበርቴ አድርባዮች ባሁኑ ወቅት በወዝ አደሩ መሀል የሚያደርጓቸው ቅስቀሳዎች የሚነዙት ውዥንብር አለ:: ባሁኑ ወቅት 'ሁሉም' ማርክሲስት ነኝ ባይ፣ 'ሁሉም' ለወዝ አደሩ ቀዋሚ ጠሪ ሆኗል:: የወዝ አደሩ መደብ ከነዚሁ ሀይሎች የተከለለ፣ በአጥር የተለየ፣ እንዳልሆነ ሁሉ /ሊሆንም አይችልም/ የሚነዙት ውዥንብር በወዝ አደሩዘንድ ማስተጋባት አልቀረም::

በዚሁ አንጻር አብዮታዊ ማርክሲስት ምሁራን፣ ለኢትዮጵያ ወዝ አደር ያስገባው የሶሺያሊዝም እውቀት በማስተላለፍ፣ በዚሁም ባቢያ የወዝ አደሩ ፓርቲ እንዲደራጅ በመታገል ይህን ውዥንብር ማስወገድ ይኖርባቸዋል:: በወዝ አደሩ ያለውን ውዥንብር የማስወገዱ ተግባር፣ ባሁኑ ወቅት በወዝ አደሩ ጋር የመቀሳቀሱና ፓርቲውን የመገንባት ተግባር ሊነጠል አይችልም::

በምሁራን መሀል ያለውን ሁኔታ ስንመለከት ባሁኑ ወቅት በተለይም ከፍተኛ የፖለቲካና የርዕዮተ ዓለም ትግል በካሄድ ላይ ነው:: በተለይም 'ሳይንሳዊ ሶሺያሊስታዊ ርዕዮተ ዓለሞች' መድረክ ቀጥው ሃይለ ስላሴን ይታገሉ በነበሩ ምሁራን መሀል የከረረ ርዕዮተ ዓለማዊ ትግል በመካሄድ ላይ ይገኛል:: ይህ በተለይ 'የሰፊው ሕዝብ ድምፅ' በተባለው አብዮታዊ ጋዜጣና በኢ.ሕ.አ.ፓ ልሳን በሆነው 'ዲሞክራሲያ' የሚካሄደው ትግል አስፈላጊም ብቻ ሳይሆን የማይቀርም ነው:: ምሁራን መደብ የለሽ እንደመሆኑ ሁሉ፣ ከተለያዩ መደቦች የሚመጡና የተለያዩ መደቦች ጥቅም ጠባቂዎች እንደ መሆናቸው መጠን፣ በሃይለ ስላሴ ጊዜ የተለያዩትን መደቦች በአንድ መድረክ ያሰለፈው ፀረ ኢምፔሪያሊስት፣ ፀረ ፊውዳል ትግል ወደፊት ሲራመድ [illegible] ሁሉ፣ በዚሁም መጠን ቀደም በምሁራን መሀል የነበረው አንድነት በመፈረካከስ ላይ ይገኛል:: እነዚሁ በመለያየት ላይ ያሉ ምሁራን በመሀላቸው በሚያደርጉት ትግል፣ ባሁኑ ወቅት በነቃውና ከተማረው ንዑስ ከበርቴ የበላይነትን ለማግኘትና በርሱም አማካኝነት የአብዮቱን አቅጣጫ / ወደፊት ወይም ወደ ኋላ/ ለመወሰን ይጥራሉ::

በዚሁ ርዕዮተ ዓለማዊ ትግል አብዮታዊው ማርክሲስት ምሁር ድሉን መቀዳጀትና የአድርባዩ አወዳድ ባይ ንዑስ ከበርቴውን ጡዱን መፋቀት ለኢትዮጵያ አብዮትና ለወዝ አደሩ ትግል መሠረታዊ ጉዳይ ነው:: ለወዝ አደሩ ማርክሲስት ሌኒኒስት ቲዎሪ ማስተላለፍ፣ ማለትም የወዝ አደሩ እንቅስቃሴና ሳይንሳዊ ሶሺያሊዝምን ለማዋሀድ፣ እንዲሁም የአብዮታዊ ማርክሲስቶችን አንድነት ለመፍጠር የሚቻለውም ይኸው አብዮታዊ ምሁሩ ብቻ ነው::

የኢትዮጵያ ወዝ አደር እንቅስቃሴ ያለበትን ሁኔታና በምሁሩ ወሀል የሚቀሄደውን ትግል ባጭሩ አየን:: የወዝ አደሩ እንቅስቃሴና አብዮታዊ ማርክሲስት ምሁራን መዋሀድ አስፈላጊነትም በገመገብም፤ ይህ ተዋህዶ ምን ዓይነት መልክ መያዝ እንዳለበት በበለጠ ለማሳየት በወዝ አደሩና በምሁሩ ወሀል ሊፈጠሩ የሚችሉትን በመሠረቱ የተለያዩ ሁለት ዓይነት ግንኙነቶች መመልከቱን ይጠቅማል::

ስለነዚሁ አማራጭ ግንኙነቶች ምንነት ሲጽፍ አክስልሮድ /1892 ማርክሲስት በነበረበት ጊዜ/ የሚከተለው ይላል:: /በዚሁ ጥያቄ ላይ ሌኒን ከአክስልሮድ ጋር ሙሉ በሙሉ በመስማማት ይጠቅስዋል Vol.4. ገጽ 178–179 ተመልከት:: ከበታች የምናገኛቸው የአክስልሮድ ጥቅሶች ከዚሁ ሌኒን ጽሁፍ ነው የተወሰዱት/

የመጀመሪያው አማራጭ

"The working-class movement keeps to the narrow rut of purely economic conflicts between the workers and employers and, in itself, taken as a whole, is not of a political character, while in the struggle for political freedom the advanced strata of the proletariat follow the revolutionary circles and groups of the so-called intelligenstia."

ወዝ አደሩ በአጠቃላይ በኤኮኖሚ ትግሎች ይወሰናል፤ የፖለቲካ ትግል ለሚመለከተው በኩል ደግሞ የወዝ አደሩ የተራመደው ክፍል የአብዮታዊ ምሁራን ጥናት ክበቦችን ይከተላል ማለት ነው:: በሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ ውስጥ በምሁራንና በወዝ አደሩ ወሀል ያለው ግንኙነት በመጠኑም በሆነ የዚህን ዓይነት መልክ የወሰደ ይመስላል:: በሌኒን ግምት በዚሁ ዓይነት ሁኔታ ላይ የሶሺያል ዴሞክራቶች ጦር ማወጅ፤

"Russian Social Democrats must declare determined war.upon ... this prospect." (Coll. Works, Vol. 4, p. 179)

በወዝ አደሩና በአብዮታዊ ምሁር ወሀል ያለው ግንኙነት የዚህን አይነት መልክ እንዳይወስድ መታገል አለባቸው::

ሌላኛው አማራጭና አክስልሮድ የተዋሀደው ገጽ፤ እንደሚከተለው ነው::

"The other prospect: Social-Democracy organizes the Russian proletariat into an independent political party which fights for liberty, partly side by side and in alliance with the bourgeois revolutionary groups (if such should exist), and partly by recruiting directly into its ranks or secmring the following of the most democratic-minded and revolutionary elements from amongt the intelligentsia."



ማለትም አብዮታዊው ምሁራን ሙሉ በሙሉ ከወዝ አደሩ ጋር በመዋሀድ፤ ወዝአደሩን ለብቻው በአገዛዝ ፖለቲካ ጋርቲ በመደራጀት፤ ለዴሞክራቲክ ነጻነቶች ለሚደረገው ትግል በቀና እንዲሁም በሌሎች ዴሞክራቲክ ሀይሎች ጋር ጎን ለጎን ሊሰለፍ ከሆነም ለመራቸው፤ የሚችል ኃይል እንዲሆን መታገል ያስፈልጋቸዋል:: ወዝ አደሩ ራሱ በቂ የሆነ አብዮታዊ ኃይል እንዲሆን በሚያደርጉት ጥረትም አብዮታዊ ምሁራን ለወዝ አደሩ የሶሺያሊስት ቲዎሪ በማስተሳሰፍና በኦርጋናይዜሽን ከወዝ አደሩ ጋር በመቀላቀል፤ ወዝ አደሩን የሚመሩት የተለዩ "ምሁራን" አስፈላጊነትን ይሽራሉ:: ሆኖም የሶሺያሊስት ቲዎሪን ከወዝ አደሩ ጋር መዋሀድ ቀላል ነገር አይደለም:: በተለይ እንደ ኢትዮጵያ በመሳሰሉት ወደኋላ በቀሩት አገሮች ከተራመዱት ካፒታሊስት አገሮች ይልቅ በወዝ አደሩና በገጠር ከበርቴ ምሁራን ወሀል ያለው ሕብረተ ሰባዊ ርቀት ከፍተኛ በመሆኑ፤ በዚሁ መጠን ሶሺያሊስት ምሁራን ከወዝ አደሩ ጋር ለመዋሀድ በይበልጥ ከፍተኛ ጥረት ማድረግ ይኖርባቸዋል:: እስኪያ ይህን መዋሀድ የሚደናቀፍና የሚያረፍ ሀይሎችን መታገልና ማጋለጥ ያስፈልጋል:: ለምሳሌ የሩስያ ሶሺያል ዴሞክራቲክ ጋርቲ አደረጃጀት ታሪክ በገመለከተ የወዝ አደሩና ሶሺያሊስት ምሁር መዋሀድ በየደረጃው የተለያዩ ወሳኝ አንደነበሩት ለማየት ይቻላል:: እነ ሌኒን ሶሺያል ዴሞክራቲክ ጋርቲ ለመመሥረት የቻሉት ይህን ተዋህዶ በመሠረቱ የተያዙትንና የወዝ አደሩን አብዮታዊ ሚና የካዱትን ናርዶኒኮችን፤ ተዋህደውን በገበር ባቡታዊ ያደረጉትንና የፖለቲካ ትግል ተቀዳሚነት ያልተቀበሉት ኤኮኖሚስቶችንና ተረፈሰቶችን፤ ይህን ተዋህዶ በአፍ ደግፈው ጎን ለጎን አስፈላጊውን ድርጅታዊ ዝግጅት ለመቀበል ዝግጁ ያልነበሩትን ሜንሼቪኮች በመታገል ነው::

የወዝ አደሩን እንቅስቃሴ ከሶሺያሊስት ቲዎሪ ጋር ለማዋሀድ በሚደረገው ጥረት፤ ከሁሉም አስቀድሞ ለሶሺያሊስት አስተሳሰቦች በቀላሉ ተቀባይ የሚሆነው በሕብረተ ሰቡ ውስጥ የተሻለ ቦታ ያለው፤ ይህና የሚከፈለው የወዝ አደሩ ክፍል ነው:: የተሻ ነባቸውን አስቃቂ የኑሮ ሁኔታ ምንነት ለመረዳት ባላቸው ጉጉትና ፍላጎት የተነሣ ከዚሁ ክፍል የሚወጡ ወዝ አደሮች ራሳቸውን በማስተማር የዓለምን ሕልውና ለመለወጥ ለመረዳት ይሞክራሉ:: ለነዚሁ ወዝ አደሮች "የወዝ አደሩን ምሁር" ይሉታል:: በቀላሉም ሶሺያሊስት አስተሳሰቦችንም ሊቀበሉ ይችላሉ::

"The history of the working class movement in all countries shows that the better-situated strata of the working class respond to the ideas of socialism more rapidly and more easily. The From among these come, in the main, the advanced workers that every working class movement brings to to the free, those who can win the confidence of the labouring masses, who devote themselves entirely to the education and organizatio of the proletariat, who accept socialism consciously, and who even elaborate independent socialist theories. Every viable working class has brought to the fore such working class leaders, as its own

Prodhouns, Vaielants, Weitlings, and Bebels... at a time when educated society is losing interest in honest, illegal literature, an impassioned desire for knowledge and for socialism is growing among the workers, real heroes are coming to the fore amongst the workers, who, despite their wretched living conditions, despite the staltifying penal servitude of factory labor, possess so much character and will-power that they study, study, study, and turn themeelves into conscious Social-Democrats - the working class intelligentsia."

ይህ 'የወዝ አደር ምሁር' ምንም እንኳ ጥቂት ቢሆንም ኢትዮጵያ ውስጥ አለ:: ይህን የወዝ አደር ምሁር በሶሺያሊስት ፕሮፓጋንዳ ተበብ የሶሺያሊስት አስተሳሰቦችን ሲቀበል፣ ከርሱ በታች ያለውን ሰፊ ወዝ አደር ከማንም የበለጠ ለሶሺያሊዝምና ለኮሚኒዝም ሊያሸንፋቸው ይችላል:: ስለዚህም የወዝ አደሩን ምሁር በማርክሲስት ሌኒኒስት አስተሳሰቦች ማስታጠቅ ከፍተኛ ግምት ሊሠጠው የሚገባው ተግባር ነው::

ባሁኑ ወቅት ከወዝ አደሩ ጋር ለመዋሀድ፣ ፓርቲ ለመገንባት የሚደረገው ትግል፣ በጠቅላይ ሁለት ፕራክቲካል መልኮች ይዞ ይቀርባል::

ሀ/ በገቢር በወዝ አደሩ ቀን ተቀን ትግሎች መሳተፍ፣ በነዚሁ ትግሎች መሰሐቀ ዐጣል፣ በነርሱም የሶሺያሊስት ቀስቀሳ ማካሄድ::

ለ/ በየቦታው በየናት ክበቦች፣ በግል በበ ደረጃ ወዝተ.. በተቦጣጠሩ ኮሚኒቶች መሀል የርዕዮተ ዓለምና የፖለቲካ አንድነት መፍጠር::

እነዚህን ጥምራ ተግባሮች "ለተም በወዝ አደሩ ትግሎች ሥር መስደድና በየቦታው የተሠባጠሩትን ማርክሲስት ሌኒኒስት ሃይሎች ማዋሀድ በሚገባ ሥራ ላይ ለማዋል ከቻልን የወዝ አደሩን ፓርቲ ለመመሥረት የሚያበረክቱትን ሁኔታዎች እናሟላለን::

ስለዚህም "የኢትዮጵያ ወዝ አደር ለታሪካዊ ሚናው ብቁ እንደሚሆን፣ በእጁሱ ፕሮሌታሪያዊ ሬቮሉሽን አቀጣጫ ወደ ሶሺያሊዝም እንደሚራመድ፣ ከዓለም ዐቀፍ ወንድሞቹ ጋር እጅ ለእጅ ተያይዞ ኢምፔሪያሊዝምን አውድሞ መደብ የለሹን ሕብረተሰብ እንደሚመሠርት የሚያግደው ኃይል እንደሌለ በመወቅ፣ በዚሁ እምነት ፅንተን፣ ገለበናነታችን፣ የሩቡን በማትን፣ ብቁና የንዑስ ከበርቴ ጉድለቶቻችንን ሁሉ አስወግደን የኢትዮጵያን ወዝ አደር ለማደራጀት በየአቅጣጫው እንታገል " / ትግላችን ቁ 2 ኅዳር 1967/ በማለት እንደመድማለን::

መሐመድ ዩሱፍ



## ተጨማሪ መግለጫ ቁጥር 1 / Appendix I /

የኢ.ሕ.አ.ፓ ፕሮግራም በብሔር ጥያቄ ላይ ያለው አቋም ተምህክተኛ፣ ፀረ ጭቁን ብሔሮችና ፀረ ሌኒኒስት መሆኑን ከፍ ብለን በጽሑፋችን አይተናል:: እንዲሁም ይህ የፀረ ጭቁን ብሔሮች ድርጅት የብሔርን ጥያቄ የሚያነሳው በዚሁ ጥያቄ ለመነገድ፣ በጨቋኙም በተጨቋኙ ብሔር ርካሽ ተወዳጅነት ለማትረፍ እንጂ፣ ይህ ጥያቄ በተጓዳሪ ደረጃ ሆነ ለአብዮቱ ወደፊት ግፊት መፈታት ያለበት የፕሪንሲፕል ጉዳይ ሆኖበት እንዳልሆነ ለመረዳት ችለናል:: በዚሁ አንፃር በቅርቡ የኤርትራ ሕዝባዊ ነፃ አውጭ ግንባር / PLF / እና የኢ.ሕ.አ.ፓ ባወጡት ጋራ ኮሚኒኬ ውስጥ የኢ.ሕ.አ.ፓ የወሰደው አቋም የቀን ያህል የተውሸለሸለ ተምክህተኛና ፀረ ሣይንስ ለመሆኑ ተጨማሪ ማስረጃ እንደመሆኑ መጠን ለገመለከተው እንወዳለን:: በዚሁ ኮሚኒኬ የሚከተለውን ሠፍሮ እናገኛለን::

" Hence:

The Eritrean question is not a national question.The controversy whether the term'colonial' could fit the Eritrean question was raised.

The EPLF position is yes it fits.But on the EPRP side it was differd on the point that it was not discussed in the Party and in the future the party will study the question and take a stand accordingly..."

(Joint Statement EPLF/EPRP . 3-3-76)

በመጀመሪያ እዚህ ላይ መመልከት ያለብን፣ የኢ.ሕ.አ.ፓ ፕሮግራም የኤርትራን ጥያቄ እንደብሔር ጥያቄ እንደሚመለከተው ነው:: እንዲያውም የጭቁን ብሔሮችን የመገንጠል መብት መታወቅ በሚያነሳው በተውሸለሸለው አቋም በመመርኮዝ፣ የኤርትራ ጥያቄ በሰላምና በዲሞክራቲክ መንገድ እንዲፈታ ይጠይቃል::/ የኢ.ሕ.አ.ፓ ፕሮግራም ገጽ 16 ተመልከት/ እዚህ ላይ የሚገርመው የኢ.ሕ.አ.ፓ ከስድስት ወር በሚያንስ ጊዜ ውስጥ በኤርትራ ጥያቄ ላይ ያለውን አቋም ቀይሮ የኤርትራ ጥያቄ የብሔር ጥያቄ አይደለም ማለቱ ነው:: መቼም ከእለታት አንድ ቀን በብሔር ጥያቄ ላይ በመሰለ አበይና መሠረታዊ ጥያቄ አቋማቸው በመቶ በማንያ ዲግሪ ለመቀየር የሚችሉት በፖለቲካ የሚነግዱ ብቻ ናቸው:: አሁንም ቢሆን የኢ.ሕ.አ.ፓ በአሁኑ አቋሙ የሚያምንበት ከሆነ በገለጸ ለምን የድሮው አቋሙ ስህተተኛ እንደነበረ ለማስረዳትና የአሁኑ ፖለቲካው ትክክለኛነትን ለማስረዳት እንጓቻም መከራ አላደረገም:: ለዚህም ሁለት ምክንያቶች አሉት፣

ሀ/ ምንም ቢሆን የአሁኑን አቋሙን ትክክለኛነት ለማስረዳት ስለማይችል፣ በዚቸው ኮሚኒኬ ሐማካይነት በሰሜን ኢትዮጵያ አካባቢ የሰቡን ሠርቶች ሳይነቃበት፣ አዉርባዊነቱ ነጋዴነቱ ሳይጋለጥበት እንዲታለፍ ይሻል፣

ለ/ የኢትዮጵያንም ሕዝብ ከመናቅ፣ የፈለጉትን በሠራና በቀባጥር እንደ ተከታዮቹ የኢትዮጵያ ሕዝብ ዓይኑን ጨፍኖ ይገርበልናል የሚለትም አገላ ንቀት አለ::

ሁለተኛ፣ የኤርትሪያ ጥያቄ የብሔር ጥያቄ አይደለም የሚለው አባባል ፈጽሞ ስህተተኛና ፀረ ሳይንስ በሆነ ተለኪሽ ቲዎሪ የተመሠረተ ነው:: እናስረዳ:_ ብዙውን ጊዜ የኤርትሪያ ጥያቄ ለውይይት ሲቀርብ፣ የብሄር ወይስ የኮሎኒ ጥያቄ ነው እየተባለ ይጠየቃል:: ሆኖም ጠለቅ ብሎ ላየው የጥያቄው አቀራረብ" የብሔር ወይስ የኮሎኒ" ትክክለኛ አንዳልሆነ፣ በብሔርና በኮሎኒ ጥያቄ መሐከል ያለውን ግንኙነት በሚገባ እንደማያስቀምጥ ይረዳል:: ምክንያቱም በማርክሲስት ሌኒኒስት ቲዎሪ አንፃር በብሔርና በኮሎኒ ጥያቄ መሐከል ያለው ግንኙነት ስንመለከት፣ <u>የኮሎኒ ጥያቄ ምንም ጊዜ ቢሆን የብሔር ጥያቄ ሲሆን፣ በተገላቢጦሽ ግን የብሔር ጥያቄ ሁሌጊዜ የኮሎኒ ጥያቄ መሆን እንደሌለበት እንረዳለን::</u>ማለትም የኮሎኒ ጥያቄ ሁሌ ጊዜ የብሔር ጥያቄን ሲጠቀልል፣ የብሔር ጥያቄ ግን ሁሌ ጊዜ በግዴ የኮሎኒ መልክ መውሰድ የለበትም::" የብሔር ወይስ የኮሎኒ ጥያቄ " ብሎ የሚጠይቁ ሰዎች ይህን በሁለቱ መሀል ያለውን ግንኙነት ዘንግተው፣ ነጣጥለቀቸው ያስቀምጧቸዋል:: ጥያቄውም የተሟላ ጥያቄ መሆኑ ቀርቶ፣ የእምነት መሆን ይጀምራል::

የኢ.ሕ.አ.ፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ የኤርትራ ጥያቄ የምን ጥያቄ ነው ብለው ሲጠይቁት የሚሰጠው መልስ " የብሔር ጥያቄ አይደለም " የሚለውን መልስ ነው:: ከዚህ መልስ የምንረዳው፣ ወየ የኢ.ሕ.አ.ፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ በብሔር ጥያቄና በኮሎኒ ጥያቄ ማህል ከፍ ብለን የጠቀስነው ግንኙነት ዘንግቶታል፣ ማለትም ማንኛውም የኮሎኒ ጥያቄ በግድ የብሔር ጥያቄ መሆን እንዳለበት ያውቃል፣ ይህ ከሆነ ደግሞ የኤርትራ ጥያቄ " የብሔር ጥያቄ አይደለም " ሲል የብሔር ጥያቄ ካልሆነ የኮሎኒ ጥያቄ ሊሆን ስለማይችል በኤርትራ ህዝቦች ላይ የብሔር ጭቆና የለም ማለቱ ነው:: <u>ስለዚህም ኢ.ሕ.አ.ፓ ግልጽ የሆነ ፀረ ኤርትራ ሕዝብ አቋም አለው</u>:: ወይ ደግሞ በብሔር ጥያቄና በኮሎኒ ጥያቄ ማህል ያለው ግንኙነት ኢ.ሕ.አ.ፓን ለመሰለ "ማርክሲስት" ፓርቲ አልገባውም ማለትም የኤርትራ ጥያቄ የብሔር ጥያቄ ሳይሆን የኮሎኒ ጥያቄ ሊሆን የሚችል ይመስለዋል:: <u>ይህ ደግሞ ለንዱ ማርክሲስት ሌኒኒስት ነኝ ለሚል ፓርቲ ፍጹም የሚያሳፍር ስህተት ነው::</u>

አፍረት ለኢ.ሕ.አ.ፓ እንግዳ ነገር አይደለምና ኢ.ሕ.አ.ፓ ይህ በብሔርና ኮሎኒ ጥያቄ ማህል ያለው ግንኙነት አልገባውም እንበል:: ይህ ከሆነ በኢ.ሕ.አ.ፓ ግምት የኤርትራ ጥያቄ የብሔር ጥያቄ አይደለም ግን የኮሎኒ ጥያቄ ሊሆንም ላይሆንም ይችላል ማለት ነው:: ይሁንና የኮሎኒ ጥያቄ ነው ወይስ አይደለም ለሚለው ጥያቄ ኢ.ሕ.አ.ፓ የሚሰጠው መልስ አላጠናሁም የሚል ነው::



ግን ኢ.ሕ.አ.ፓ የኤርትራ ጥያቄ የብሔር ጥያቄ አለመሆኑን ደርሶበታል:: እንዴት? ወይም ኢ.ሕ.አ.ፓ በኤርትራ የብሔር ጭቆና የለም ብሎ ያምናል /የኤርትራ ጥያቄ የብሔርም የኮሎኒም ጥያቄ አይደለም ማለት ነው/ ስለዚህም በኤርትራ ሕዝብ ላይ ያለው ጭቆና ከብሔር ጭቆና የተለየ ጭቆና ነው የሚል እምነት አለው:: ነገር ግን ይህ ከብሔር ጭቆና የተለየ ታይቶ የማይታወቅ ጭቆና ምን አይነት እንደሆነ ኢ.ሕ.አ.ፓ አልተገለጸለትም::

እርግጥ ኢ.ሕ.አ.ፓ ብዙ ነገር የተገለጸለት ፓርቲ አይደለም:: ነገር ግን እቺኛዋ "አልተገለጸልኝም" ካለማጥናት ወይም ካለማወቅ ሳትሆን ከቀጥፈት ናት:: ነገሩ ቀላል ነው::

" የብሔር ጥያቄ አይደለም" በማለት ኢ.ሕ.አ.ፓ ከኤርትራ ግንባሮች የምትመሳጠርበት አቋም ይዛ ተቀርባለች::ማለትም ለግንባሮች ተስፋ ትሰጣለች ማለት ነው::

" የኮሎኒ ይሁን አይሁን አላጠናሁም በተለ " የኮሎኒ ጥያቄ አይደለም ብለው ከሚያምኑት ተከታዮቿ ጋር እንዳትቀራረብ ታደርጋለች:: በሌላ አነጋገር ለነዚህም ተስፋ ትሰጣለች ማለት ነው::

ገሬም ንግዴ ገሬም አደርባይነት::

የኢ.ሕ.አ.ፓ የኤርትራ ጥያቄ <u>የብሔር ጥያቄ</u> አይደለም፣ የኮሎኒ ጥያቄ መሆኑን አላውቅም፣ ገና አላጠናሁትም ያለውን እስከሁን አየን::እንግዲህ ታዲያስ የኤርትሪያ ጥያቄ ምንድነው ብለን የኢ.ሕ.አ.ፓን ብንጠይቅ፣ <u>የማያናግር የማያጋግር ዱዳ ሆኖ</u> ቁጭ ይላል:: ምንም ዓይነት መልስ አይሰጥም::እንዴስ አድርጉ ይችላል ?

ይህ ሆኖ ሳለ በጋራ ኮሚኒኬው የኢ.ሕ.አ.ፓ የሚከተለውን ይላል፤

" The EPRP unconditionally supports the Eritrean peoples struggle for there independence.It as well support the political and armed struggle waged by the EPLF for the independence and liberation of the Eritrean people..."

እንደዚ፣ የኤርትሪያ ጥያቄ ምንነት አላውቅም፣ ሆኖም የኤርትሪያን መገንጠል ደግፋለሁኝ ማለት በኤርትሪያ ሕዝቦች ትግል ማላገጥና ማፌዝ አይደለምን? የብሔር/ኮሎኒ ጥያቄ መሆኑን ሳያጣሩ፣ የአንድን ብሔር መገንጠል እንደግፋለሁኝ ማለት አንዱን በጠተኛ ሳይመረምሩ መዶኗነት እንደማዘዝ አይሆንምን ?

ሁለተኛ፣ በኢሕአፓ ፕሮግራም ውስጥ የኤርትራ ጥያቄ በሠላምና በዲሞክራቲክ መንገድ ይጠየቃል::እንዲያውም በፕሮግራሙ ውስጥ የመገንጠል መብት ጥያቄ አይነሳም ታዲያስ በኤርትራ ውስጥ ባለፉት ጥቂት ወራት ምን አዲስ ሁኔታ ተፈጠረና ነው የኢሕአፓን የኤርትራ ጥያቄ በዲሞክራቲክና በሰላማዊ መንገድ እንዲፈታ እንዳይታገል ያደረገው? ኤርትራ ተገንጠል የሚያሰኘው?

ምርምራችንን ለማጠቃለል የኢሕአፓ በተጨቆኑት ብሔሮች ብሶት ለመነገድና እንጀራውን ለማብሰል የሚፍጨረጨር ቡድን እንጂ፣በሀቅ ለተጨቆኑት ብሔሮች መብትና አርነት የሚታገል ፣ ከነርሱም ጋር የተሰለፈ ዲሞክራቲክ ሃይል እንዳልሆነ ለማየት ይቻላል::



ተጨማሪ መግለጫ ቁጥር 2 /Appendix II/

ከጥቂት ወራት በፊት አንድ የኢ.ሕ.አ.ፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ አባል፣ ሲሞን ማሌ ከተባለው የአሜሪካን ሰላይ፣ የሲ.አይ.ኤ. ወኪል ጋር ተገናኝቶ፣ ይኸው ሲሞን ማሌ ለሚያወጣው "አፍሪክ አዚ" ለተባለው መጽሔት ቃለ መጠይቅ /February-1976/ ሰጥቶ ነበር:: የዚሁ ቃለ መጠይቅ አቅዱ የኢትዮጵያን አብዮት በዓለም አቀፍ ደረጃ ለማጥላላት ብቻ ሳይሆን፣ የኢ.ሕ.አ.ፓን በአካባቢያችን ከሚገኙት አድሀሪ የጎረቤት መንግሥታት አገር ለማስታዋወቅም ነበር:: በዚሁ ቃለ መጠይቅም የሸው የኢ.ሕ.አ.ፓ ወኪል፣ የኢትዮጵያን ሕዝቦች ትግል ሲያንቋሽሽ፣ የመሬት አዋጁን ሥራ ላይ ለማዋል የሚደረገው ትግል መቀጥን፣ /እንደውነቱ ከሆነ ገድለነዋል ለማለት ነበር የፈለገው ደራሲው/ ወዘተ...ኢትዮጵያ የኢምፔሪያሊስቶች ዋና ተገን ናት በማለት ያልዘባረቀው ነገር አልነበረም::

እዚህ ላይ ለማንሳት የምንፈልገው፣ የቃለ መጠይቁን ይዘት ሳይሆን፣ በተቀዳሚ ደረጃ የኢ.ሕ.አ.ፓ ከኢምፔሪያሊስቶች ወኪሎች ጋር መተሣሰርና መቀላለፍ መጀመሩን ነው:: ይህንንም በተጨባጭ ማሥረጃ ለማሳየት እንሞክራለን:: "አፍሪክ አዚ" የተባለው በፓሪስ የሚታተም ዓለም ዐቀፍ መጽሔት የኢትዮጵያ አብዮት ከመጀመሪያውም የበለጠ ሥር ነቀል እየሆነ ከሄደበት ጊዜ አንስቶ፣ ይህን አብዮት ለማንቋሸሽና ለማጥላላት ያልነዛው ሃሰተኛ ወሬ፣ ያልገለበጠው ድንጋይ የለም:: የዚሁ ጋዜጣ ዋና ኃላፊና አዘጋጅ የሆነው <u>ሲሞን ማሌ</u> የተባለው ሰው ለአረብና ለሰሜን አፍሪካ ጉዳይ በC.I.A የተሾመ ሰው እንደሆነ የአደባባይ ምሥጢር ነው:: ባለፈው ዓመት የአሜሪካን ሴኔት ባደረጋቸው ምርመራዎች / Senate Hearings / ሲ.አይ.ኤ በየቦታው የሚያወናብዱ <u>ተራማጅ</u> መሰል ጋዜጠኞች እንደሚተክል እንደታወቀው ሁሉ፣ የዚሁ ግራ መሰል ተግባር እንደዚሁ ተራማጅ መሳይ ፀረ አብዮት ተግባሩን ማካሄዱ ነው ይህ ወኪል ወደ ኢትዮጵያ ጉዳይ ከመመደቡ በፊት፣ የሌሎች ሕዝቦች ትግል በማደናቀፍ በማወናበድ ዝና ያተረፈ ነበር:: ለምሳሌ የቬትናም ሕዝቦች የገናና ትግላቸውን በሚያካሂዱበት ወቅት፣ ትግላቸውን ለማደናቀፍ፣ የቻይናንና የቬትናም ሕዝቦችን ትግል አንድነት ለማፋለስ ቀንደኛ እንደነበረ ይታወቃል:: ይህን ማስረጃ እና ሳይ::

እ.አ.በ1967 ይኸው ሲሞን ማሌ የተባለው ሰላይ፣ የቬትናምንና የቻይና ሕዝብ ለማጣላትና በዚህም ሳቢያ የቬትናምን ሕዝቦች ትግል ለማደናቀፍ ባደረገው ጥረት፣ በሃሰት የቻይና ጠቅላይ ሚኒስቴር የነበሩት ቹ ኤን ላይ ቃለ መጠይቅ ሰጥተውናል በሎ፣ የቬትናም ሕዝቦችን ትግል የሚያጥላላ የፈጠረውን "ቃለ መጠይቅ" በመጽሔቱ አወጣ፣ በዓለም አሠራጨ:: ፔኪንግ ሪቪዩ የተባለው የቻይና መጽሔት ስለዚሁ ጉዳይ ሲጽፍ፣

"...This 'interview' was a fabrication of Simon Malley... Judging from the process by which the alleged 'interview' was produced, from its contents, and from comments made by the imperialist...propaganda machinery in connection with it, this was a political plot of the U.S. imperialists... Their despicable motive was to...disrupt the fraternal relations between China and Vietnam...Milt Froudenheim of Chicago Daily News admitted that he had discussed whith Malley his projected 'trip' to China before he left. It was also reported that after his return to the United States, Malley submitted to the U.S. government a report on his fake 'interview' and handed the 'interview' and other related articles to U.S. officials. The U.S. State Departement then instructed that all of them be published...Malley was in Peking only two days, from March 27 to 29, while passing through the city. During his stay there, neither Premier Chou nor any other chinese leaders received him. He told the lie that he stayed in China for three weeks. A responsible person of the Chicago Daily News said that Malley stayed in Peking for 19 days. Malley also sayed that Premier Chou received him at 8 a.m. in the 'people's palace' in the 'Forbidden City'. It is well known that there is no 'people's palace' in the 'Forbidden City' and Premier Chou has never received any foreign guest at 8 a.m...." / ጀንበጎ ሪፖርት ቁጥር 21/1967/

የኢ.ሕ.አ.ፓ የገጠመዉ ከእንዲህ ዓይነቱ የCIA ወኪልና ፀረ ሕዝብ ግለ ሰብ፣ እንዲሁም በስተጀርባዉ ከቆሙት ኢምፔሪያሊስት ኃይሎች ጋር ነዉ:: "አፍሪክ እዥ" የተባለዉ የCIA ጋዜጣ ከመቅጸበት የኢ.ሕ.አ.ፓ ፀረ የኢትዮጵያ አብዮት ፕሮፓጋንዳ ቧንቧ ሆኗል:: ለምንድነዉ፣ በተለይም ዉጭ አገር በሚገኙ ተራማጅና ሀቀኛ ክፍሎች የተጠላዉና የኢምፔሪያሊስቶች መሣሪያ የሆነዉ ይኸዉ "አፍሪክ እዥ" የተባለዉ መጽሔት የኢ.ሕ.አ.ፓ ፕሮፓጋንዳ ለማስተጋባት የፈቀደዉ? ምንስ ቢያተርፍበት ነዉ? የኢ.ሕ.አ.ፓ ደግሞስ ከዚሁ "አንድነት ግንባር" ምን ያገኛል ?



በበኩላቸዉ የኢትዮጵያ ሕዝቦችና ተራማጆች አብዮታቸዉን ወደፊት በሚገፉበት ወቅት፣ መፈናፈኛ በማጣት ላይ የሚገኙት ጠላቶቻቸዉ ግራ መስሎም ሆነ የይፋ ፋሺስት ወበባበጣቸዉ እንደማይቀር አዉቀዉ ፣ ይህ በኢትዮጵያ ዉስጥ በመገበራት ላይ ያለዉን "የአብዮታዊያን የአንድነት ግንባር" እንደሚጠረፈሉት ምንም ጥርጥር የለዉም:: በቅርብም የተመታዉ፣ የአሜሪካን ኢምፔሪያሊስቶች፣ የሲዓይ ሀብቱና የኢ.ሕ.አ.ፓ ፋሽስታዊ መፈንቅለ መንግሥት ሙከራ የዚህን አባባል ታሪካዊ ሀቅ የሚያስመሰክር ነዉ::

የሲ.አይ.ኤ እና የኢ.ሕ.አ.ፓ ትብብር ይዉደም !

የኢትዮጵያ ሕዝቦች ያሸንፋሉ !

መስከረም 25 ቀን 1969 ዓ.ም.

## በአናርኪስቶች በለተገደሉት ጓድ ፍቅሬ፣ ጓድ አበበ ከርሰ በቀለ፣ ጓድ ከገሬ፣ ጓድ ገብረእግዚአብሔርና ጓድ ጌታቸው በአብዮታዊ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር የተሰጠ መግለጫ

በማንኛውም አብዮት አድሃሪያቸና አናርኪስቶች አብዮቱን ለመቀልበስ፣ ሰፊው ጭቁን ሕዝብና ተራማጆች ደግሞ አብዮቱን ወደፊት ለማራመድ ይታገላሉ ። በዚህ ዓይነት ፀረ—አብዮታዊና አብዮታዊ ትግል ውስጥ ቀለባሾች የለየለት አድሃሪና አድርባይ የፖለቲካ መስመሮችን በመከተል የቀለበሳ አላማቸውን ለመምታት ልዩ ልዩ የትግል ዘዴዎችን ይጠቀማሉ ።

የለየለት አድሃሪ የፖለቲካ መስመር የሚከተለው ቀልባሽ ቡድን አብዮቱን በለየለት አድሃሪ የትግል ዘዴ ሲዋጋ አድርባይ የፖለቲካ መስመር የሚከተለው ቀልባሽ ቡድን ደግሞ ለሰፊው ጭቁን ሕዝብ የቆመ በመምሰል የቀለበሳ ትግሉን ያካሂዳል ። በሰፊው ሕዝብ ስም እየተገዘተ፣ በማርክሲዝም—ሌኒንዝም እየተሸፋፈነ ሰፊውን ሕዝብ ኃይል ለመከፋፈል፣ ውዥንብር ለመፍጠር፣ የትግሉን አቅጣጫ ለማሳት፣ ወዘተ... በዚያውም ሰፊውን ሕዝብ የራሱን አድሃሪ ዓላማ በሚመታበት የፖለቲካ መስመር ላይ ለማደራጀት ይጥራል ። አድርባይ የፖለቲካ መስመሩን ለማስተጋባት ከፍተኛ የፖለቲካ ትግል ያደርጋል ። የፖለቲካውም ትግል ሳይሳካለት ሲቀር የመጨረሻ አስተንፋሹን ለመተንፈስ ያለ ሞት ባይ ተጋዳይ ገበገቡን ከሰፊው ሕዝብና ሃቀኛ ታጋዮች ጋር ለማድረግ ይቃጣዋል ። ገበገቡም ታጋይ ግለሰቦች ላይ የስም ማጥፋት ዘመቻ ማድረግ፣ ክትትልና ስለላ ማካሄድ የውንብድና የግድያ ተግባሮችን ማካሄድ፣ በየቦታው ሽብሮችን መፍጠር፣ በጠቅላላው ቴሮሪዝምን በሰፊው ማካሄድ ይሆናል ።

ይሁን እንጂ ትግሉ የወሰደውን ጊዜ ወስዶ፣ በበዙሃኑ ታጋዮች ደምና መስዋዕትነት ለጭቁኖች ድልን በማጎናጸፍ ያልቃል ።

ኢትዮጵያ ውስጥ አሁን ባለንበት ወቅት ከፍተኛ አብዮታዊና ፀረ—አብዮታዊ ትግል እየተካሄደ ነው ።

.../ 2



በኢሕአፓ ሥር የተሰበሰቡት የቀድሞ መሳፍንቶች፣ ፊውዳሎቶች፣ የቢሮ ከበርቴዎችና ኢምፔሪያሊስቶች አብዮቱን ለመቀልበስ ዛሬ በየቦታው የሚያካሂዱት የቀለበሳ ትግል በቀላሉ ሊገመት የሚችል አይደለም ። ግልጽ የሆኑ አድሃሪ የፖለቲካ መስመር በመከተል አብዮቱን ግልጽ በሆኑ አድሃሪ መንገድ በጥብቅ እየታገሉ ናቸው ።

የእነዚህም ዋነኛ ወሳቶች አገልጋይ ለመሆን የተፈጠረው ኢሕአፓ አድርባይ የፖለቲካ መስመሩን አንግቦ በማርክስና በሌኒን ስም እየማለና እየተገዘተ የኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝቦች የተቀዳጁ ድሎችና የሆኑትን ለመቀልበስ የሚያጣጥፈትን ፊውዳሊዝምንና ኢምፔሪያሊዝምን መልሰው እንዲያነግሱለት መታገል ከጀመረ ትንሽ ጊዜ አይደለም ። በወዛደሩ፣ በገበሬው፣ በውይይት ክበባት፣ በቀበሌ ማኅበራት፣ በሴቶች ማኅበራት፣ በወጣቶች ማኅበራት፣ ወዘተ ... ሰርጎ በመግባት ለፀረ—አብዮት ዓላማው አድርባይ ፖለቲካውን በማስፋፋት ኃይሎችን ለመከፋፈል፣ ለማወናበድ፣ የትግላቸውን ዓላማ ለማሳትና ትግላቸውን ለማበረታት ያላደረገው ጥረት የለም ።

ይሁን እንጂ አድርባዮች ለጊዜው ውዥንብርና የኃይል መከፋፈል ቢያደርሱም በሃቀኛ ተራማጆችና በሰፊው ጭቁን ሕዝብ ጽኑ ትግል የተከናነቡትን አድርባይ የፖለቲካ መስመር አውልቀው ከትግሉ እንዲወጡ ይደረጋሉ ።

በኢሕአፓ ላይ ዛሬ የደረሰው አደጋ ይህ ነው ። ሃቀኛ ተራማጆች ትክክለኛ የፖለቲካ መስመር ለማስፋፋትና በዚያውም የኢሕአፓ አድርባይ የፖለቲካ መስመር እንዲጋለጥ ባደረጉት ከፍተኛ ትግል ኢሕአፓ የፖለቲካውን ትግል በመሸነፍና በሃፍረት ለቆ የተጠጋበት ደረጃ ላይ ደርሷል ። የፖለቲካውን ትግል በማለስቱ በኩል "ማሩኝ የለሁበትም" ወደሚለው አዘማሚያ ተጠግቷል ። ተበቀ ፍሏል ። በዚህም ምክንያት "ከመሞቴ በፊት ገድዬ ልሙት" በሚል ፈሊጥ አድርባይ ፖለቲካው የፊውዳሎቶች፣ የቢሮክራቶችና የኢምፔሪያሊስቶች የፖለቲካ መስመር መሆኑን ገላልጦ አድርገው ለሕዝብ በማሳወቅ ተጋልጦና ተዋርዶ እንዲበረር ባደረጉት ታጋይ ተራማጆች ላይ የግድያ ተግባር በማካሄድ ላይ ይገኛል ።

.../ 3

ኢህአፓ በፊውዳሊስቶች፣ ቢሮክራቶችና ኢምፔሪያሊስቶች ትብብር ሰሞኑን ከፈጸሟቸው የማፊያ ገድያዎች አንዱና ትልቁ በጓድ ፍቅረ መርዕድ ላይ በመስከረም 21 ቀን 1969 ዓ.ም. ከምሽቱ 12 ሰዓት ገደማ ያደረሰው ገድያ ነው።

ኢህአፓ በጓድ ፍቅረ መርዕድ ላይ ለምን የአድሃሪ ቦንቡን ሰነዘረ? አጭሩ መልስ ጓድ ፍቅረ ከረጅም ጊዜ አንስቶ ሰፊው የኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝብ በፊውዳሊዝም፣ ኢምፔሪያሊዝም፣ ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊዝምና አናርኪዝም ላይ የሚያካሂደውን ቀጥታ ትግል መስመር በማስያዝ ግቡን እንዲመታ ለማድረግ ሳይታክቱ፣ ተስፋ ሳይቆርጡ ባለማቋረጥ ከታገሉት ጽኑ ታጋዮች አንዱ በለነበረ ነው። ከዚህ ቀጥለን ጓድ ፍቅረ ለኢትዮጵያ ሕዝቦች ያበረከታቸውን አብዮታዊ አስተዋጽኦዎች ከጥሊ ጉዳል ለመዘርዘር እንሞክራለን።

ጓድ ፍቅረ ተወልዶ በመሳፍንትና ከንጉሣውያን ቤተሰብ ነበር። ይሁን እንጂ ይህን መደቡን ከድቶ ከኢትዮጵያ ጭቁን መደቦች ጋር በመሰለፍ የራሱን መደብ ለበዙ ዓመታት ሲዋጋ ቆይቷል። በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲም ይማርበት ወቅት በዩኒቨርሲቲው ተማሪዎች ይዘጋጅ ለነበረው "ህውክ አንድ ሽውክ" ለተባለው ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ በመሆን የተማሪውን እንቅስቃሴ አገልግሏል። በ1956 ዓ.ም. ወደ አውሮፓ ለትምህርት ሄዶ ፈረንሳይ አገር በሚማርበት ወቅት በፈላጭ ቆራጩ የኃይለሥላሴ ፀረ-ዲሞክራቲክ አገዛዝ ምክንያት በኢትዮጵያ ሊገኝ የማይችለውን የማርክሲዝም-ሌኒንዝም ትምህርት በመቅሰም የወረኛኝ ማኅበርና የጥገና ለውጥ ዝንባሌ ያጠቃው የነበረውን በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር ተራማጅ የፖለቲካ መስመር እንዲከተልና ታጋይ የተማሪዎች ማኅበር እንዲሆን ከታገሉት አንዱ ነበር። ማኅበሩ የወረኛኝና ለጥገና ለውጥ ታጋይ ሆኖ እንዲቆም የታገሉትን ወጣት መሳፍንቶች በቆራጥነት ታግለው በ1957 ዓ.ም. በተደረገው ታሪካዊ የሺፍ ጉባዔ ላይ አድሃሪ ምሽጋቸው ውስጥ እንዲገኩታቸው ማኅበሩ በፀረ-ፊውዳሊስና ፀረ-ኢምፔሪያሊስት መድረክ ላይ በመመስረት ከኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝብ ጋር እንዲቆም ካደረጉት ታጋይ ወጣት ኢትዮጵያውያን አንዱ ነበር። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ጓድ ፍቅረ በተለያዩ ጊዜያት የታጠቁና የትግላችን ዋና አዘጋጅ በመሆን፣ በፈረንሳይ ቅርንጫፍ ማኅበርም ሆነ በአውሮፓው የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር ደረጃ ለቀ





ለቀ ኃላፊነቶችን በመሸከም በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር የጠራ የፖለቲካ መስመር እንዲከተልና እንዲጠነክር ያለተቆጠበ አብዮታዊ ጥረት ያደረገና ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረከተ ታጋይ ወጣት ማርክሲስት-ሌኒኒስት ነበር።

በፈረንሳይ አገር የከፍተኛ ሕግ ትምህርቱን ጨርሶ ወደኢትዮጵያ ከተመለሰ በ1964 ዓ.ም. በኋላ ጓድ ፍቅረ የኢትዮጵያን አብዮት በከፍተኛ ደረጃ ለመርዳት አሁንም ያለተቆጠበ አብዮታዊ ጥረት አድርጓል። በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በሚያስተምርበት ወቅት የዩኒቨርሲቲ መምህራን የውይይት ክበብ አባል በመሆን፣ ክበቡ አብዮታዊ የፖለቲካ መስመር እንዲከተልና የኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝቦች ከፊውዳሊዝም፣ ከኢምፔሪያሊዝምና ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊዝም ጋር በሚያካሂዱት አብዮት ውስጥ አብዮታዊ አስተዋጽኦ እንዲያበረክት ለማድረግ ታግሏል። በዚህም ምክንያት በእነ እንዳልካቸው መኩንን መንግሥት መታሠሩ ይታወሳል።

ሌላው የጓድ ፍቅረ አብዮታዊ አስተዋጽኦ የኢትዮጵያ ሕዝቦች ከፊውዳሊስቶችና ከኢምፔሪያሊስቶች ጋር ከፍተኛ የሞትና የሽረት ትንቅንቅ በሚያደርጉበት ወቅት፣ አድርባዮችና አድሃሪዎች አገር እየለቀቁ ጓዛቸውን እየጠቀለሉ በየጠረፉ እየሾለኩ ወደ ውጭ አገር ሲኮበልሉ ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት ለሃገሩ ተራማጆች የእናት አገር ጥሪ ባቀረበበት ወቅት የዚህን ጥሪ አብዮታዊ ይዘት በመረዳት እንደሌሎቹ አድርባይና አድሃሪ ምሁራን "ራሴን ከዚህ ማጥ ውስጥ ላውጣ" ሳይል ጥሪውን ያለንዳች ማመንታት ተቀብሎ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ያደረገው አብዮታዊ ተጋድሎ ነው። ጓድ ፍቅረ ይህን ሰፊውን ሕዝብ ለማደራጀት ለማንቃትና ትክክለኛ የትግል መስመር ለማስያዝ አመቺ ሁኔታ የፈጠረውን ጥሪ ሲቀበል አስከነቤተሰቡ በፈረንሳይ አገር ሙሉ አስኮላርሽፕ አግኝቶ ነበር። ዳሩ ግን እውነተኛ ታጋይ ከግል ጥቅሙ የሕዝቡን ጥቅም በለሚያስቀድም ጓድ ፍቅረ ወደ ፈረንሳይ ከመሄዱ ትግሉ የተፋፋመበት ኢትዮጵያ ውስጥ ቆይቶ የኢትዮጵያን ጭቁን ሕዝብ ማገልገልን መረጠ። ይህ እርምጃ የጓድ ፍቅረ ከጭቁኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ለመቆሙ ሌላው ምስክር ነበር። የጥሪው ውጤት አንዱ የሆነው የሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽሕፈት ቤት ከተቋቋመ ጊዜ አንስቶ በመስከረም 21 ቀን ዲጨረሽ ደም መጣጭ በአድሃሪዎች ጥይት እስከረሰበት ድረስ በጽሕፈት ቤቱ ውስጥ የጊዜያዊ ጉዳዮች ኮሚቴ ሊቀመንበር በመሆን ጓድ ፍቅረ የኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝቦች እንዲደራጁ፣ እንዲነቁና እንዲታጠቁ ከዚያም በኋላ ፊውዳሊዝምን፣

ምፔሪያሊዝምንና ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊዝምን ደምስሶ በመቃብራቸው ላይ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክን እንደሚመሠረት በፅኑነት ታግላለች ። ለዚህም ነው የሰፊውን ሕዝብ ተደራጅቶ፣ ነቅቶና ታጥቆ ሦስቱን ጠላቶች በመደምሰስ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክን እንዳይመሰርት የሚታገሉት አናርኪስቶች ጓድ ፍቅሬ መርዕድ ላይ አውሬያዊ ጥቃታቸውን የከፈቱት ።

ቀልባሽ አናርኪስቶች ጓድ ፍቅሬን የገደሉት የኢትዮጵያ አብዮት ሂደት በጣም እየገፋ በመሄዱ ተደናግጠው እንደአባት በሚያገለግላቸው ጓድ ፍቅሬን በመግደል አብዮቱን የሚገቱ መስሏቸው ነው ። ይህ አውሬዎች ለሕዝብ ካላቸው ንቀትና ሕዝባዊ ኃይል በቀልባሾች ኃይል ሊበገር የማይችል ታሪካዊ ሐቅ መሆኑን ካለማወቅ የተነሳ የሚያደርጉት ቅዠት ነው ።

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር የአሁን ግፈኞች በጓድ ፍቅሬ ላይ ያደረሱትን ፋሽስታዊ የረከሰ ግድያ በጥብቅ እያወገዘ ለአናርኪስቶች የሚያስተላልፈው መልዕክት አናርኪስቶች ከአንገብጋቢ ሺህ ጊዜ ቢገድሉን በሚሊዮን ሺህ ጊዜ ተወልደን ገለስ ብቻን ቢገድሉ አራት ሺው በአብዮቱ ነበልባል እየተቃጠሉ እንደ አመድ ይበናሉ እንጂ ከአንገብጋቢ የኢትዮጵያን አብዮት ለመቀልበስ ቢቶ አንደማይችሉ ነው ።

የጓድ ፍቅሬ በአናርኪስቶች መገደል እርግጥ ጓድ ፍቅሬ ለሚኖር ዋርላተኛ ጓድ ፍቅሬ ለቆጠቡት አስተካክሎ ገቡን እንዲቀጥል ለታገለለት የኢትዮጵያ አብዮት ታላቅ ጉዳት ነው ።

ለዚህም በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር የተሰማውን ከፍተኛ ሃዘን ይገልጻል ። ነገር ግን በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር ከሌሎች ጠቅ ተራማጆችና ከሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ሆኖ ጓድ ፍቅሬን " የአንተ መሞት የአንተ ቀጥሎ መስዋዕት መሆን ለእኛ ተገቢና ትምህርት ይሰጠናል ። በአንተ በአውሬዎች መገደል የሚያቆመው ትግል በሚተካም የጀመርከውን ገቡን እንግፋ እናበቃለን ። በዚም የአንተን የተቀደሰ ደም አንበቀለዋለን " ይለዋል ።

.../6



አናርኪስቶቹ ቀልባሾች በመስከረም 16 ቀን አብዮቱን ለማገልገል ቆርጠው በተነሱ ሦስት ጓዶች ላይ የፈጸሙት ግድያ በኢትዮጵያ አብዮት ላይ የፈጸሙት ሌላው ወንጀል ነው ። አናርኪስቶቹ ጓድ አሙበከር አበጊል ወንድሙ ጓድ ከንፈ አበተፋውና ጓድ ገብረእግዚአብሔር ተበፋ ፀን የገደሏቸው ጓዶች ሌሎች በመቃብሉ ዚሬው ሆስፒታል ከሚገኙት ሁለት ጓዶች ጋር ተሰብስበው አብዮታዊ ጥናት በሚያካሂዱበት ወቅት ነበር ። አናርኪስቶቹ በር ከፍተው በሽጉጥና በመትረየስ ሦስቱን ገድለው ሁለቱን አቁስለው ሊሄዱ ችለዋል ።

ሦስተኛው የአናርኪስቶች ወንጀል በመስከረም 21 ቀን በጓድ ጌታቸው እንግዳ ላይ የፈጸሙት ግድያ ነው ። አናርኪስቶቹ ጓድ ጌታቸውን የገደሉት በቤቱ አጠገብ ተው አቤቱ በር ላይ ነበር ። ጓድ ጌታቸው አብዮቱን ለማገልገል ቆርጦ የተነሳ፣ በሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽ/ቤት በአዲስ አበባ ቀርንጫፍ ውስጥ ይሰራ የነበረና በሥርቦት ሰፈር የቀበሌ ማኅበር ሊቀመንበር ሆኖ በመሥራት አናርኪስቶችን በማጋለጥ የቀበሌውን ማኅበር አብዮታዊ መስመር ለማስያዝ የታገለና በማኅበሩ አባሎች ታላቅ ተወዳጅነትን ያተረፈ አብዮታዊ ወጣት ነበር ።

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር የነዚህ ጓዶች በአናርኪስቶች መገደል የተሰማውን ጥልቅ ሃዘን ይገልጻል ። መስዋዕት ከሆኑት ጓዶች ትምህርትንና ቆራጥነትን በመማር በዙ ታጋይ ኢትዮጵያውያን እንደሚያፈሩና ከሰፊው ሕዝብ ጎን በመሰለፍ አናርኪስቶች ለመቀልበስ የሚጥሩትን አብዮት አውነው ከግቡ እንደሚያደርሱ በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር ቅንጣት አይጠራጠርም ።

ጓዶች ፍቅሬ፣ አሙበከር አበጊል፣ ከንፈ፣ ገብረእግዚአብሔርና ጌታቸው
ለታጋይ ተራማጆች አርአያ ይሆናሉ!

የጓዶቹ ገዳዮችና ተባባሪዎቻቸው በአስቸኳይ ለአብዮታዊ ፍርድ ይቅረቡ!

የ CIA ና የአናርኪስቶች ፀረ—አብዮት ሴራ ይውደም!

የነቃ የተደራጀና የታጠቀ ትግል ያሸንፋል!

ስለ ሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ

(signature)

ወርቁነን ገሙ

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር
መጽሔት አዘጋጅ ቦርድ
The Ethiopian Students' Union in Europe
Editorial Board

## ማሳሰቢያ

ውድ አንባቢያችን፣

የውጪን ንቅናቄ ከውስጥ ሆኖ ቦርቦሮ ለማደከም ያደረገው ሙከራ ስላልተሳካለት እርሱን ከንቅናቄያችን ያገለለው ፀረ ሕዝብ ቡድን ከቅርብ ጊዜ ጀምሮ፣ከአስር ዓመት በላይ ሰፊው ሕዝብ ጐን በመሰለፍ ያለማቋረጥና ያለመታከት ፀረ ኢምፔሪያሊስትና ፀረ ፊውዳሊስት ትግል ሲያካሂድ በኖረው ማህበራችንና በነዚህም አስር ዓመታት ያለተሰጣቸውን ነፃነት በሙንጠቅ የሰፊውን ሕዝብ ድምፅና ትግል ሲያስተጋቡ በኖሩት ፲ከ የተናውም የተማሪ ማህበራት መጽሔት በላይ የሰፊው ሕዝብ ማስተማሪያና መቀስቀሻ ሆነው በቆዩት በ<u>ታጠቅና</u> በ<u>ትግላችን</u> ስም መጠቀም ጀምረዋል:: የዚህ ፀረ ሕዝብ ቡድን ዓላማ ማህበራችን እንዲሁም <u>ታጠቅና</u> <u>ትግላችን</u> በአስር ዓመት ቁራጥ ትግል ባተረፉት ስም ተጠቅሞ ፀረ ሕዝብ ፖለቲካውን ለመሸፈን ነው::እንዲሁም ከውስጥ ሆኖ ያቃተውን የኢትዮጵያ ተማሪዎችና ተራማጆች አንድነት የማፍረስ ሙከራ ከውጭ ሆኖ ወንጀገበር በመገዛት ለማፋፋም ነው::ይህም እንደማይሳካ የተረጋገጠ ነው:: ለማገናዘብ፣የተለመደው የመጽሔት አዘጋጅ ቦርድ አድራሻ/ማለትም P.O.BOX 3198 10364 STOCKHOLM - SWEDEN ያለያዙ፣የዓለም ዓቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪያች <u>ማህበር</u> አባልነትን የማያመለክት ግን የማህበራችን መጽሄቶች ስም የያዙ መጽሄቶች ወዘተ በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪያች ማህበር መጽሄቶች አለመሆናቸውን እንድታውቁልንና እንድታስታውቁልን እንጠይቃለን::ለእነዚህ አይነት መጽሄቶች ተጠያቂው ''ዓለም ዓቀፍ ፌዴሬሽን'' በሚባል ስም የታወቀው የነ አስፋወሰን — ወንገሻ ሥዩም የወጣቶች ድርጅት ነው::

ከፋፋዮችና አወናባጆች ከፊውዳሊዝምና ከኢምፔሪያሊዝም ጋር ይውደሙ!
የእውነተኛ አብዮታዊያንና ተራማጆች አንድነት ይኑር!
ድሉ የሰፊው ሕዝብ ነው!

በአኢተማ የመጽሄት አዘጋጅ ቦርድ